አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3551 | ቅዳሜ ታህሳስ 4 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# የስማርት ሲቲ ግንባታው እርሾዎች

“ስማርት የአገልግሎት መስጫ ሕንፃዎቹ ከተማችንን ስማርት ለማድረግ የጀመርነው ሥራ አካል ናቸው”

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ



3

ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ስማርት የአገልግሎት መስጫ የወረዳ አስተዳደር ሕንፃዎችን መርቀው ወደ ስራ ባስገቡበት ወቅት

## “ወደ ኋላ የቀረንባቸውን ጊዜያት በሚያካክስ መልኩ መፍጠን ይጠበቅብናል”



6

ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር)

## በልኩ ያልተጠቀምንበት ሀብት




9

ግራፊክስ፡- በዳንኤል ተስፋይ

ቆሻሻን በየመልኩ በማደራጀት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የማድረጉ ተግባር ከሁሉም ይጠበቃል

## የባለቅኔው የምጥቀት አክናፍ




11

ፎቶ- ከገፀ ድር

የሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህንን የህይወት ታሪክ የሚዳስሰው መፅሐፍ

# የጋራ ጥረትን የሚሻው የባሕር በር ጥያቄ

- ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ለማስጠበቅ በጋራ መስራት ይገባናል ሲሉ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ተናግረዋል



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ (አዴኃን) ሊቀ መንበር አቶ ተስፋሁን አለምነህ

የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት (ኢዴህ) ሊቀ መንበር ገብሩ በርሄ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በዓለም ላይ ከሚገኙት 195 ሉዓላዊ ሀገራት መካከል 44ቱ የባሕር በር የላቸውም ይላል ዓለም አቀፉ የንግድ ድርጅት ይፋ ያደረገው መረጃ። ከእነዚህ ውስጥ 31ዱ ደግሞ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ናቸው፤ ካዛኪስታን በቆዳ ስፋቷ ትልቅ ሆና ወደብ የሌላት ሀገር ስትሆን ኢትዮጵያ ደግሞ ትልቅ የሕዝብ ብዛት እና ሠፊ ግዛት ይዛ የባሕር በር ከሌላቸው የዓለም ሀገራት ተርታ ትመደባለች፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ጉባኤው የሚፈጥረው ዕድልና የቤት ስራዎች

- የኮፕ32 ጉባኤ በርካታ እንግዶችን ስለሚያሳትፍ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ምሁራን ገልፀዋል

**በስንታየሁ ምትኩ**

አዲስ አበባ በዲፕሎማሲ ማዕከልነቷና እያሳየች ባለው ሁለንተናዊ ለውጥ የዓለምን ዓይንና ቀልብ የሳቡ ትላልቅ ጉባኤዎችን በስፋት በማስተናገድ ላይ ትገኛለች፡፡ በህዳር ወር 2018 ዓ.ም በብራዚል ቤሌም በተደረገው የኮፕ-30 የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ ከሁለት ዓመት በኋላ በሺህዎች የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች የሚታደሙበትን የ“ኮፕ-32” የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ኢትዮጵያ እንድታስተናግድ ተመርጣለች።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል



# ርዕሰ አንቀፅ




## ለኮፕ 32 ጉባኤ ስኬት ሁሉም ኃላፊነቱን ከወዲሁ ይወጣ!

አዲስ አበባ ስምና ግብሯ እንዲጣጣም ሰባቱንም ቀናት ቀን እና ማታ እየሰራች ትገኛለች፡፡ በዚህም ገጽታዋ ተቀይሯል፣ መሰረተ ልማቶቿ ደረጃቸውን እየጠበቁ፣ የመዝናኛ አማራጮቿ እየሰፉ ነው፡፡ እነዚህና መሰል ተግባራት ኮንፍረንስ ቱሪዝምን ጨምሮ በዘርፉ አመርታዊ ለውጥ እንድታመጣ እያስቻሏት መሆኑ በርከት ባለ ቁጥር እየተካሄዱ ያሉ ዓለም እና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች የተግባር አስረጂዎች ናቸው፡፡ የተሰሩት እና እየተሰሩ ያሉት ሁሉን አቀፍ የልማት ስራዎች የኮንፍረንስ ማዕከልነቷ ከዚህም በላይ እየፈካ እንደሚመጣ ከሁለት ዓመት በኋላ የምታስተናግደው የኮፕ 32 የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤን በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ አረንጓዴ አሻራን ጨምሮ የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል የሚያስችሉ ተግባራትን በተጨባጭ በመከወኗ የኮፕ 32 ጉባኤን እንድታስተናግድ ዕድል አግኝታለች፡፡ ጉባኤውን በተሳካ መልኩ ማካሄድ ብሎም ይዞት የሚመጣውን እድል አሟጥጦ መጠቀም ይጠበቅባታል፡፡ ከሚያስገኛቸው ትሩፋቶች መካከል የከተማዋን የኮንፈረንስ ቱሪዝም መዳረሻነት ከፍ ያደርጋል፡፡ በሀገር ደረጃ ከብዝሃ ኢኮኖሚ ዘርፉ አንዱ በማድረግ ማልማት ላይ በትኩረት የተሰራበት የቱሪስት መስህቦችን ማልማት ላይ ከተማዋ የሰራቻቸውን የበለጠ ለማስተዋወቅ ዕድል ይፈጥርላታል፡፡ እንደ ሆቴል፣ ትራንስፖርት፣ አስጎብኚ እና መሰል አገልግሎት ሰጪ ዘርፎችም የጥቅሙ ተቋዳሾች ናቸው፡፡ ለዚህ ግን የቤት ስራዎችን ቆጥሮ በአግባቡ መፈጸም ያስፈልጋል፡፡

መንግስት ከወዲሁ የጀመራቸው ስራዎች አሉ፡፡ ከሀገር ውስጥ የሥራ ኃላፊዎች፣ ከተባበሩት መንግሥታት አካላት እና ዓለምአቀፍ አጋሮች ጋር በመተባበር የኮፕ 32 ዝግጅትን እንዲመሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) ተወካይ ፕሬዝዳንት ተደርገው ተመድበዋል፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት ቁልፍ የዝግጅት

ተግባራትን ለማቀናጀት የሚያስችል የብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ስብሰባም ተደርጓል፡፡ ከሰሞኑ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከኡራኤል ብራስ፣ ቦሌ መድኃኔዓለም ጎላጎል እስከ እንግሊዝ ኤምባሲ የሚዘልቀውን የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት እና የፒኮክ (ማዕከላዊ) ፓርክ ግንባታን በገመገሙበት ወቅት፣ ለእንዲህ አይነት ጉባኤዎች ስኬት የሚያግዙ አስቀድመው የተጀመሩ የልማት ስራዎች በፍጥነትና በጥራት እንዲከናወኑ የማድረግ ስራ ተጠናክሮ እንደቀጠለ ገልጸዋል። ከንግዱ ማህበረሰብ ጋርም ለጉባኤው ስኬታማነት ከማን  ምን እንደሚጠበቅ ውይይት ማድረግ እና የቀጣይ አቅጣጫ ማስቀመጥ ችለዋል፡፡

ይህ ለጉዳዩ የተሰጠውን ትኩረት በግልጽ የሚያመላክት እና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው፡፡ በግሉ ዘርፍ ያሉ ባለድርሻ አካላትም ጊዜ ሳያባክኑ ጓዳቸውን መፈተሽ፣ አቅማቸውን ማጠንከር፣ ወቅቱ በሚመጥነው መንገድ አገልግሎታቸውን ተደራሽ ለማድረግ መሰናዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በጥቅሉ ለኮፕ 32 ጉባኤ ስኬት ሁሉም ኃላፊነቱን አውቆ ከወዲሁ አስፈላጊውን ስራ ሊያከናውን ይገባል!

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## የጋራ ሀብቶቻችንን በጋራ እንጠብቅ!

### ኤግል ከስድስት ኪሎ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማዋን ውብ፣ ጽዱ፣ ለኑሮ ተስማሚ እና ለቱሪዝም ሳቢ እንድትሆን በርካታ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከተማዋን እንደ ስሟ አዲስ፣ ውብና ጽዱ ለማድረግ እየተሰሩ ባሉ ስራዎችም ትልልቅ ውጤቶች ተገኝተዋል ብዬ አምናለሁ፡፡

ከተማዋ ለኑሮ የምትስማማ፣ ዜጎች ሰርተው የሚለወጡባት፣ ሰክነው የሚያስቡባት፣ ፎቅ ብቻ ሳይሆን ዛፍ፣ አስፓልት ብቻ ሳይሆን አረንጓዴ መስክ ተሰባጥሮ የሚታይባት ሚዛኗ የተጠበቀ እንድትሆንም ቀላል የማይባል ጥረት እየተደረገ ነው ቢባል ዋሾ አያስብልም፡፡

በኮሪደር ልማቱ የፒያሳ፣ የአራት ኪሎ፣ የቀበና፣ የካዛንቺስ፣ የመገናኛ፣ የሲኤምሲ፣ የሜክስኮ፣ የሾሮሜዳ፣ ሳርቤት፣ ለቡ፣ የመሳሰሉ አካባቢዎች እንደገና የመወለድ ያህል ለምተዋል። የአረንጓዴ ቦታዎች፣ መዝናኛዎች፣ የህዝብ ፕላዛዎችና መጸዳጃዎች፣ ፋውንቴኖች፣ የልጆች መጫወቻዎች፣ የብስክሌት እና የእግረኛ መንገዶች፣ የመንገድ ዳር መብራቶች ማራኪ በሆነ ሁኔታ ተሰርተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተሰሩ የኮሪደር ልማቶች ላይ በእግረኞችም ሆነ በአሽርካሪዎች ላይ የአጠቃቀም ጉድለት እንደሚታይ መታዘብ ችያለሁ፡፡

በለሙ ቦታዎች ላይ ቆሻሻ መጣል፣ አፈር፣ ጠጠርና ሌሎች የግንባታ ግብዓቶችን መድፋት፣ ያልታጠቡ ተሽከርካሪዎችን ይዞ ወደ ጎዳና መውጣት፣ ለብስክሌት ተብሎ በተሰራ መንገድ ላይ መሄድ፣ አረንጓዴ ስፍራዎችና የመንገድ አካፋይ፣ የመንገድ ዳር መብራቶችን፣ ዘንባባዎችን እና እፅዋትን በመርገጥ ጉዳት አድርሶ መሄድን የመሳሰሉ ጥፋቶች እየተፈፀሙ መሆኑን ታዝቤያለሁ፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በኮሪደር ልማት ላይ የህግ ጥሰት የፈፀሙ አሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል፡፡ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ድረስ የገንዘብ መቀጮ የተጣለባቸው መኖራቸውም የሚታወስ ነው፡፡ ህግ በመተላለፍ የህዝብ ሀብት ላይ ጉዳት ማድረስ በመሆኑ ከቅጣቱ ባለፈ ተጠያቂነትንም ስለሚያስከትል አሽከርካሪዎቹ በህግ ቁጥጥር ስር የዋሉበት ጊዜ እንዳለም ይታወሳል፡፡

ድርጊቶቹ ደንብን መተላለፍ በመሆኑ የተወሰዱ እርምጃዎች ይበል የሚያሰኙ ናቸው፡፡ በእኔ አመለካከት እነዚህ ድርጊቶች ስልጡን ነው ከሚባል የከተማ ማህበረሰብ የሚጠበቅ አይደለምና ሊታረም ይገባል ባይ ነኝ፡፡ የከተማዋ ነዋሪች የተሰራውን የልማት ስራ እንደራሳቸው ሀብት ሊጠብቁት እና ሊንከባከቡት ይገባል እላለሁ፡፡ መሰረተ ልማቶችን በጋራ መጠበቅ ከሁላችንም ይጠበቃል ለማለት እወዳለሁ፡፡

ከፍተኛ በጀት ወጥቶባቸው የተዘረጉ የኮሪደር ልማት መሰረተ ልማቶች በዋናነት ጥቅም የሚሰጡት ለማህበረሰቡ ብሎም ለአጠቃላይ የከተማዋ ነዋሪዎች መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አኳያ የኮሪደር መሰረተ ልማቶችን መጠበቅ፣ መንከባከብና ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ከነዋሪዎች የሚጠበቅ ነውና ሁሉም የከተማዋ ነዋሪዎች ኃላፊነት ወስደው አንዱ ቢያጠፋ ሌላው፣ "ተው ለምን ታጠፋለህ?" ብሎ ማስተማርና መገሰፅ ይገባል ባይ ነኝ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ይግለጡ ጓዴ
ሄለን ጥላሁን
ፋንታነሽ ተፈራ
በሽዋርካብሽ ቦጋለ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# የስማርት ሲቲ ግንባታው እርሾዎች

## “ስማርት የአገልግሎት መስጫ ሕንፃዎቹ ከተማችንን ስማርት ለማድረግ የጀመርነው ሥራ አካል ናቸው”

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

**በመለሰ ተሰጋ**

‘የስማርት ከተማ አብዮት…’ በተሰኘው የማርክ ዴኪን እና ሁሳም አል ዋየር ጥናታዊ መፅሐፍ ላይ እንደሰፈረው 21ኛው ክፍለ ዘመን በዓለም አቀፍ ከተሞች ፈጣን ለውጥ አምጥቷል። በብዙ መልኩ ተራርቀው የነበሩ ከተሞች የተቀራረቡ፣ ዘላቂነት ያላቸው እና በቴክኖሎጂ የሚመሩ ማዕከላት እየሆኑ መጥተዋል። በዚህ ወቅት በከተሞች መካከል ያለው የለውጥ አብዮት ከቴክኖሎጂ ምጥቀት ጋር አብሮ እየፈጠነ ስለመሆኑም በጥናታዊ መፅሐፉ ላይ ሰፍሯል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ተገንብቶ ወደ ስራ የገባ ስማርት የአገልግሎት መስጫ የአስተዳደር ሕንፃ

እንደ መፅሐፉ ከሆነ፣ የቴክኖሎጂ እድገት በከተማ ህይወት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በዚህም ምክንያት የስሉጥ (ስማርት) ከተሞች ዕድገት በእጅጉ እየተፋጠነ መሆኑም ተመላክቷል፡፡ እነዚህ ስማርት ከተሞች፣ ስልጡን የመጓጓዣ ዘዴዎች፣ ዘላቂ የኃይል መፍትሔዎች (የታዳሽ ኃይል አማራጮች)፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዙ የህዝብ አገልግሎት መስጫዎች ያሏቸው ሲሆን፣ በኮሪደር ልማትም ሆነ በሌሎች ዘመኑን የዋጁ ስራዎች የተሻለ በመከወናቸው ለነዋሪዎቻቸውም ሆነ ለእንግዶቻቸው ምቹ ከተሞች መሆን ችለዋል፡፡

እንደ ሲንጋፖር፣ ባርሴሎና እና አምስተርዳም ያሉ ከተሞች የኮሪደር ልማትን በመሳሰሉ ዘርፎች በተለይም በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎትን ቀድመው በመጀመራቸው ሌሎች የዓለማችን ከተሞች የእነርሱን ፈለግ እንዲከተሉ መንገድ ስለመጥረጋቸውም በመፅሐፉ ተመላክቷል፡፡

አዲስ አበባ ከተማም ይህንን የሰለጠነ መንገድ በመከተል ላይ ስለመሆኗም መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ለአብነትም ባሳለፍነው ሐሙስ ታህሳስ 2 ቀን 2018 ዓ.ም ሦስት ዘመናዊ ባለ 10 ወለል ስማርት የወረዳ አስተዳደር ሕንፃዎች ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡ የሕንፃዎቹን ወደ ስራ መግባት አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ባስተላለፉት መልዕክትም፣ “ስማርት የአገልግሎት መስጫ አስተዳደር ሕንፃዎቹ ከተማችንን ስማርት (ስሉጥ) ለማድረግ የጀመርነው ሥራ አካል ናቸው” ብለዋል፡፡

ከተማን ማዘመን ያለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ እና የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ አስመልክቶ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ቆይታ ያደረጉት በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ሙህዲን ሙሐመድ እንደገለፁት በየትኛውም ሁኔታ፣ ከፍታና ዝቅታም ውስጥ ቢሆኑ ከተሞች ለሰው ልጅ ሁለንተናዊ ስኬታማነት ያላቸው ሚና ላቅ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ስማርት መሆን ከከተማዋ ሁለንተናዊ ከፍታ ባሻገር እንደ ሀገር ትልቅ ኢኮኖሚያዊ እምርታ የሚያመጣ ነው፡፡

በዚህ ዘመን ላይ ከተሞች የስልጣኔ፣ የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሚባሉ ነገሮች ሁሉ ማዕከል ናቸው፡፡ በመሆኑም ከተማን ከስልጣኔ፣ ከዕድገት፣ ከልማት እና መሰል ዘመናዊ ነገሮች ልንለይ አንችልም ብለዋል፡፡

እንደ መምህር ሙህዲን ስለ ስማርት ሲቲዎች ስናነሳ ከዚህ ቀደም ባልሄድንበት መንገድ ነው የምንሄደው ብለን ማየት አለብን፡፡ ለአብነትም አዲስ አበባን ብንወስድ የኢትዮጵያ የስልጣኔ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ መስተጋብር፣ የፖለቲካ እና የተለያዩ ጉዳዮች ማዕከል ናት፡፡

እዚህ ላይ ስማርት ሲቲን ስናስብ ብዙ ዕድሎችን ይሰጠናል፡፡ ይህም ከተማዋ ስማርት ስትሆን ዜጎች የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ፣ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው አፈፃፀም እንዲጨምር፣ ብክነት እንዳይኖር እና አገልግሎት በተለያዩ የከተማዋ ክፍሎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን፣ ቀልጣፋ ውሳኔ ለመስጠት፣ ዜጎችንም በተሻለ ሁኔታ ለማሳተፍና ፍላጎታቸውን ለማሟላት ያስችላል፡፡ ከተማዋ ስማርት ስትሆን ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በሁሉም ዘርፍ ለመጠቀም ትችላለች፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የአገልግሎት ተደራሽነት ይሰፋል፤ ቅልጥፍናውም ይጨምራልም ብለዋል መምህሩ በሰጡን ሙያዊ ማብራሪያ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፣ በከተማዋ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ከተከናወኑ በርካታ ተግባራት መካከል አንዱ ለህዝብ ቅርብ የሆኑ የወረዳ አገልግሎት መስጫዎችን ማዘመን፣ በበቂ የሰው ኃይል ማደራጀት፣ በቴክኖሎጂ መደገፍ እንዲሁም ለአገልግሎት ሰጭውና ለተገልጋዩ ማህበረሰብ ምቹ የስራ ቦታን መፍጠር እንደሚገኙበትም ገልጸዋል፡፡

እንደ ከንቲባዋ ገለፃ ወደ አገልግሎት የገቡት ስማርት የወረዳ አስተዳደር ሕንፃዎች አገልግሎትን ወደ አንድ ማዕከል በመሰብሰብ ተገልጋዩ ጊዜና ሀብት እንዳይባክን በማድረግ፣ እንግልትና ውጣ ውረድን በመቀነስ፣ በአንድ ማዕከል ፈጣንና ቀልጣፋ የወረዳ አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲያስችሉ ተደርገው የተገነቡ ናቸው፡፡

ሕንፃዎቹ ዘመናዊ መኪና ማቆሚያ፣ የልጆች ማቆያና መጫዎቻ ስፍራ፣ ውብ ፅዱና አረንጓዴ ቅጥር ግቢ እንዲኖራቸው ተደርገው ተገንብተዋል፡፡ በተጨማሪም አካል ጉዳተኞችን እና አቅመ ደካሞችን ታሳቢ ያደረገ አሳንሰር ወይም ሊፍት የተገጠመላቸው እንደሆነም ከንቲባዋ ገልፀዋል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ያሉ ከተሞችም ስማርት ሲቲ መሆናቸው በቅርባችን ካሉ የሌሎች ሀገራት ከተሞች አንፃር የተሻለ ተወዳዳሪ እንድትሆን እና ከፍ ብላ እንድትወጣም ያደርጋታል ያሉት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር)፣ አዲስ አበባ በምስራቅ አፍሪካ፣ በቀጣናው እና እንደ አህጉር ያላትን ከፍታ ለማስቀጠል ስማርት መሆን ግድ ይላታል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታዩ ያሉ ለውጦች ይህንን የሚያመላክቱ ስለመሆናቸውም ጠቅሰዋል፡፡

አርክቴክት እና የከተማ ፕላነር ሮበርት ሳሙኤል (ዶ/ር) ‘Timeless Cities’ ወይም ጊዜ የማሽራቸው ከተሞች የተሰኘ የምርምር መፅሐፍ አላቸው፡፡ በዚህ ስራቸው ከተሞች ሳያረጁ ከዘመን ጋር እየዘመኑ እና የህዝባቸውን አዳጊ ፍላጎት እያሟሉ ከፍ የሚሉበትን ምስጢሮች ተንትነዋል፡፡

ከተሞች አስደማሚ፣ ሰፊና ምቹ ጎዳናዎች፣ ደማቅ ሰፈሮች፣ በአረንጓዴ ዕፅዋት የታጀቡ እና ከግፊያውና ውክቢያው ገለል ብሎ ሰው ከራሱ፣ ከወዳጁ እና ከተፈጥሮ ጋር የነፍስያ ጨዋታ የሚኮመኩሙባቸው የመዝናኛ ስፍራዎች፣ ትላንትን ከዛሬ አስማምተው የተሰሩ ልዩ ልዩ ግንባታዎች እና በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎትን በመተግበር ዜጎቻቸውን የሚያስደስት አሰራርን ተግባራዊ ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው ሮበርት (ዶ/ር) በጥናታዊ መፅሐፋቸው ጠቅሰዋል፡፡

በመሆኑም ከተሞች እንደዘመኑ ስልጡን፣ ከተፈጥሮ ጋር የተስማሙ፣ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችሉ፣ የትራፊክ መጨናነቅን የሚቀንሱና ከተፈጥሮ ጋር የተዋደዱ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና የህዝብ ማመላለሻ አማራጮች የሚጠቀሙ፣ ያልተጨናነቁ የመኖሪያ አካባቢዎች፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ አማራጮችና ፈጠራዎች፣ አካታች ልማትና ማህበራዊ ፍትሕ የነገሰባቸው፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን የሚከተሉ ለነዋሪዎቻቸው ፍላጎትና ምቾት ቅድሚያ የሚሰጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆን እንዳለባቸውም ገልፀዋል፡፡

የለንደኑ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ጥናትና ምርምር ማዕከል ‘የስማርት ከተማና የምጣኔ ሀብት ተዛምዶ’ በሚል ርዕስ ይፋ ባደረገው የቅርብ ጊዜ ጥናት መሰረት ‘ስማርት ከተማ’ የሚለው ቃል የአንድን ከተማ የህዝብ አገልግሎቶች እና መሠረተ ልማቶችን ለማገናኘት እና ለማመቻቸት የታለሙ ስትራቴጂዎችን ስብስብ ያመለክታል። ስማርት ሲቲ የመጨረሻ አላማቸው የዜጎችን የኑሮ ጥራት ማሻሻል ነው። አንድን ከተማ ስማርት ናት ስንል በፈጠራ የተዋበች፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ ቀልጣፋ አገልግሎት የምትሰጥ፣ ዘላቂ እና እርስ በርስ የተገናኘች ናት ማለታችን ነው ይላል መረጃው፡፡

የስማርት ከተማ ልማት በ10 ዋና ዋና ምሰሶዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ እነዚህም የዘላቂ የከተማ ልማት መርሆዎችም ናቸው። እነሱም ስማርት አስተዳደር፣ ስማርት ኢኮኖሚ፣ ስማርት አካባቢ፣ ስማርት ማህበረሰብ፣ ስማርት ኑሮ፣ ስማርት የትራንስፖርትና መሰል እንቅስቃሴዎች፣ ስማርት አውቶማቲክ የመኪና ማቆሚያ ስርዓቶች፣ ዘመናዊ የኃይል መሙያ ጣቢያዎች፣ ስማርት ኢነርጂ እና የአየር ብክለትን መቋቋም የሚችል ምቹ ስፍራ መኖር እንደሆነ በመረጃው ተመላክቷል፡፡

አዲስ አበባ ከተማም ከዘመኑ ጋር የተስማማው፣ የነዋሪውን ፍላጎት ታሳቢ ያደረጉ የልማት ስራዎችን እያከናወነች ነው፡፡ በተለይም የስማርት ከተማ ልማት ምሰሶዎችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነች ነው፡፡ ባሳለፍነው ሐሙስ ታህሳስ 3 ቀን 2018 ዓ.ም በልደታና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች ተገንብተው ወደ አገልግሎት የገቡትን ሦስት ባለ 10 ወለል ህንፃዎችን ይህንኑ ያመላክታሉ፡፡ በቀሪዎቹ ወረዳዎችም ላይ የማስፋትና የማብዛት ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ መግለፃቸውም ይታወሳል፡፡

## የጋራ ... ከገጽ 1 የዞረ

በኢኮኖሚ ልማት እና በድህነት ቅነሳ ዙሪያ በሚያደርጉት ጥናት የሚታወቁት የኢኮኖሚ ባለሙያው ጄፍሪ ሳክስ፣ ከባሕር በር ርቀው የቆዩት እነዚህ ሀገራት እየተጋፈጡት ያለው ችግር ብዙ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ ከባሕር ዳርቻ መራቅ ማለት ወደ ዓለም አቀፍ ገበያዎች ለመድረስ ረጅም እና ውስብስብ የሆነ የየብስ ጉዞ ይጠይቃል፤ ይህ ደግሞ ለወጪ እና ለገቢ ምርቶች የትራንስፖርት ወጪን በእጅጉ ይጨምራል። በሌላም በኩል ከፍ ባለ የትራንስፖርት ወጪ ሳቢያ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል። በመሆኑም የባሕር በር አለመኖር የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚገታ ትልቅ እንቅፋት ስለመሆኑ ያስረዳሉ፡፡

ተጨባጩ እውነት ይህ ሆኖ ሳለ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ለዓመታት የባሕር በርን ጉዳይ ማንሳት እንደነውር አለፍ ሲልም ለእስር የሚዳርግ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይሁንና አሁን ላይ ቀን ቆጥሮ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት አግኝቷል፤ ሀገራዊ መነጋገሪያም ሆኗል። ጉዳዩ አይነኬ ከመሆን አልፎ አጀንዳ መሆን ችሏል፡፡

ምንም እንኳን አንገብጋቢው የባሕር በር ጉዳይ ለዓመታት ከመወያያ ጠረጴዛው ላይ ርቆ ቢቆይም የኢትዮጵያውያን ህይወት ከባሕር ጋር የተቆራኘ ነበር፡፡ ኢትዮጵያዊ እጣንና የዝሆን ጥርስ ጭኖ ለመካከለኛውና ሩቅ ምስራቅ ገበያ የሚያቀርብ ረጅም ተጓዥ ባህርተኛም ነበር፡፡ ልጆቹንም 'ባሕሩ' እና 'ባሕሯ' ብሎ እየሰየመ ለሺህ ዘመናት ጠረፉን ሲጠብቅና ሲዋደቅ ስለመኖሩም ታሪክ ምስክር ነው፡፡ ይሁንና በክፉ የታሪክ አጋጣሚ በሸፍጥና በሴራ ፖለቲካ ምክንያት ኢትዮጵያውያን ከባሕር ርቀው ቆይተዋል የሚሉት የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ሊቀ መንበር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ናቸው።

በእርግጥ በሴራ ፖለቲካ ምክንያት ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ከባሕር በር እንድትገለል ከተደረገች ጊዜ አንስቶ ሀገር ወዳድ ምሁራን እና የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያየ መንገድ ጥያቄውን ከማንሳት አልቦዘኑም፡፡ በመንግሥት ደረጃ እንዳይነሳ የፖለቲካ ምህዳሩን በማጥበብ ይከላከል የነበረ የፖለቲካ ስርዓት በመሆኑ የሕዝብ ውይይት ሳይደረግበት ቆይቷል። የባሕር በር የማግኘት ፍላጎትን በግልጽ መስማት ከተጀመረበት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን ጉዳዩ የውጭ ግንኙነት፣ የውስጥ ፖለቲካና የሀገሪቱ የረዥም ጊዜ የልማትና ደኅንነት ስትራቴጂ ጉዳይ ማጠንጠኛ ጭምር እየሆነ መጥቷል።

እዚህ ጋር የሚነሳው ወሳኙ ጉዳይ ታዲያ ኢትዮጵያ ቆርጣ የተነሳችበት ይህ አጀንዳ እውን እንዲሆን የብዙ ባለድርሻ አካላት በተለይም የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎና ሚና ወሳኝ ስለመሆኑ እሙን ነው፡፡ ምንም እንኳን በውስጣዊ ፖለቲካ እና አስተዳደር ላይ ልዩነት ቢኖራቸውም አብዛኞቹ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ፍላጎት ህጋዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስፈላጊነት ላይ ይስማማሉ። የባሕር በር የሌላት ሀገር በአብዛኛው የውጭ ንግድ እንቅስቃሴዋ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ (አዴኃን) ሊቀ መንበር አቶ ተስፋሁን አለምነህ



የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት (ኢዴህ) ሊቀ መንበር ገብሩ በርሄ

በጎረቤት ሀገራት ወደቦች ላይ ጥገኛ ነው። ይህም የትራንስፖርት ወጪን ከማናርም በላይ የፖለቲካ ተጋላጭነትን ይፈጥራል። ስለዚህ ፓርቲዎች፣ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማጠናከር እና ከውጭ ጥገኝነት ለመላቀቅ የባሕር በር ወሳኝ እንደሆነ ይስማማሉ።

የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችም የሚሉት ይህንኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት የምታደርገውን ጥረት ለማሳካት ፓርቲዎች ከመንግስት ጋር ተባብረው ሊሰሩ እንደሚገባ ሀሳባቸውን ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያጋሩት የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት (ኢዴህ) ሊቀ መንበር ገብሩ በርሄ ናቸው።

የ'ኢዴህ' ሊቀ መንበር ገብሩ በርሄ እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ በባሕር በር ላይ የመብት ባለቤትነቷን የሚያረጋግጡ ስራዎችን መስራት አለባት፡፡ የባሕር በር ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት ፓርቲያቸው ይደግፋል፡፡ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችም ይህ ጉዳይ ለሀገር የህልውና ጉዳይ መሆኑን በመረዳት ከመንግስት ጋር መተባበር አለባቸው፡፡

በአንዳንድ አካላት "አሁን ወቅቱ አይደለም፣ ኢትዮጵያ ልታስቀድመው የሚገባት ጉዳዮች አሏት" ለሚሉና መሰል ጉዳዮች የተሳሳቱ ስለመሆናቸው የሚያነሱት አቶ ገብሩ፣ የባሕር በር ጥያቄን ለማንሳት ትክክለኛው ጊዜ አሁን ስለመሆኑ ጠቅሰው፣ ጥያቄው የሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለመሆኑ ይገልጻሉ፡፡

በአማራ ክልል የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢው እና የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ (አዴኃን) ሊቀ መንበር አቶ ተስፋሁን አለምነህም በአቶ ገብሩ ሀሳብ ይስማማሉ። ኢትዮጵያ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የባሕር በር አጥታ ስለመቆየቷ የሚገልፁት አቶ ተስፋሁን፣ ጉዳዩ የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ብቻ አለመሆኑን ጠቅሰው፣ አጀንዳውን ማንም ያንሳው የባሕር በር ጥያቄ የሁሉም ኢትዮጵያ ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ እርሳቸው የሚመሩት ፓርቲም ኢትዮጵያ ሀብቷን ተነጥቃ ቆይታለች ብሎ እንደሚያምን፣ ፖለቲካም ቢሆን ከሀገርና ብሔራዊ

> **"የባሕር በር ጥያቄ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ነው። የብሔራዊ ጥቅም በመሆኑ የባሕር በር ጉዳይን አጥብቀን የምንታገልበት አጀንዳ ነው"**

ጥቅም ስለማይበልጥ የባሕር በር ጉዳይን አጥብቀን የምንታገልበት አጀንዳ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የፖለቲካ ልዩነቶች መኖር ጤነኛና የሚጠበቅ ስለመሆኑ የሚያነሱት የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎቹ ልዩነቶቻችን ግን ከሀገር በታች ናቸው ይላሉ፡፡ አያይዘውም ፓርቲዎቹ ጉዳዩን ለዓመታት ሲያነሱት የነበረው ጥያቄ መሆኑንና አሁንም ቢሆን ለተግባራዊነቱ ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡ ተናግረዋል፡፡ ሌሎች የፖለቲካ ልዩነቶቻችንን አስጠብቀን ሁላችንም የቆምነው ለህዝብና ለሀገር መሆኑ መረሳት የለበትም ብለዋል፡፡

የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ (አዴኃን) ሊቀ መንበር አቶ ተስፋሁን ኢትዮጵያ የባሕር በር ያጣችበትን መንገድ አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት በአንድ ህገ ወጥ ቡድን በህገ ወጥ መንገድ የባሕር በሯ ተላልፎ ስለመሰጠቱም ይጠቅሳሉ፡፡ አክለውም ይህ ታሪካዊ ስህተት ሊታረም የሚገባው ጉዳይ ስለመሆኑና ለነገ የሚባል እንዳልሆነም አንስተዋል፡፡

በአቶ ተስፋሁን አስተያየት የሚስማሙት አቶ ገብሩ፣ "የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋነኛ ዓላማቸን ስልጣን ይዞ ፖሊሲዎቻችንን ተግባራዊ ማድረግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በእንደዚህ አይነት አጀንዳዎች ዙሪያ ግን የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተባብረው ሊሰሩ ይገባል" ብለዋል፡፡

የባሕር በር ጉዳይ በዋናነት የሚነሳው እንደ ሀገር መውጫ መግቢያ ስላጣን እና ስለታፈንን አይደለም የሚሉት የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ሊቀ መንበር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ "አሰብን ጠቅሰን የባሕር በር ይገባናል የምንለው አሰብ የኢትዮጵያ አካል ስለሆነ ብቻ ነው።" ይላሉ፡፡ አያይዘውም አላግባብ ከኢትዮጵያ የተወሰደ ስለሆነ፣ ሉዓላዊነትን ያላረጋገጠ የሽግግር መንግስት በተናጥል ውሳኔ አሳልፎ የሰጠው ስለሆነ ነውም ባይ ናቸው፡፡

በለጠ ሞላ (ዶ/ር) በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ ኢትዮጵያ የወደብ ጥያቄ ማንሳቷ የወደብ ኪራይ ክፍያ ስለበዛ ወይም የህዝብ ቁጥሯም ስለጨመረ ብቻ ሳይሆን ተገንጣይና አስገንጣይ ተባብረው በአንድነት የፈጸሙት ታሪካዊ በደል ስለሆነ ነው የአሰብን የኢትዮጵያ አካል አለመሆንን የማንቀበለውና አሰብ ተፈጥሯዊ የኢትዮጵያ የባሕር በርነቱ ዳግም ሊረጋገጥ ይገባል የምንለው ይላሉ። ይህንን ጥያቄ ለማንሳትም ይሁን እንደ ሀገር በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ለመታገልና ጥያቄውን ለማስመለስ ከዚህ የተሻለ ጊዜ የለም ይላሉ፡፡

ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከመንግሥት ጎን እንዲቆሙም የጠየቁት የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ (አዴኃን) ሊቀ መንበር አቶ ተስፋሁን በማጠቃለያ ሀሳባቸው ሊደረጉ ይገባቸዋል ያሏቸውን ጉዳዮች አብራርተዋል፡፡ ማብራሪያቸውን ሲቀጥሉ በብሔራዊ ጥቅም ዙሪያ የሚስተዋሉት ጭቅጭቆች መነሻቸው ፖለቲካው ባለመሰልጠኑ የመጡ እንደሆነ የሚያነሱት የድርጅቱ ሊቀ መንበር ፖለቲካው መሰልጠን እንደሚገባውና ብሔራዊ ጥቅም እና የፓርቲ አጀንዳ ሊቀላቀል አይገባም፣ ችግሮችና የፖለቲካ ልዩነቶች በሀሳብ ሙግት ብቻ ሊፈቱ እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡

የባሕር በር ጉዳይ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጉዳይ መሆኑን በማመን፣ ጉዳዩን ከጠባብ የፖለቲካ ትርፍ አውጥቶ፣ ከምሑራን፣ ከኃይማኖት አባቶች፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ከህዝቡ ጋር ሁሉን አቀፍ እና ግልጽ ብሔራዊ ውይይት ማካሄድ። የጉዳዩን ታሪካዊ፣ ህጋዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ጂኦ-ፖለቲካዊ ገጽታዎች እንዲታወቁ መስራት፡፡ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ዘላቂ የዲፕሎማሲያዊ መፍትሔ እንዲገኝ መጣር እና የባሕር በርን ጉዳይ ለሁሉም የአካባቢው ሀገራት የሚበጅ የጋራ የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት አድርጎ ማቅረብ ከፖለቲካ ፓርቲዎቹ የሚጠበቀው ኃላፊነት ስለመሆኑም የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎቹ ይስማማሉ።

በእርግጥ የተፎካካሪ ፓርቲዎች በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም ሲያሳዩ የቆዩበት ጥሩ ተሞክሮ አለ። ለዚህም የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሂደት ዋነኛው ምሳሌ ነው። ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ ፓርቲዎች ግድቡ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መብት እንደሆነ እና መገንባት እንዳለበት አጥብቀው ደግፈዋል። ይህ በግድቡ ጉዳይ የተፈጠረው የብሔራዊ መግባባት መንፈስ በባሕር በሩ ጥያቄ ዙሪያም ሊደገም የሚገባው ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ ከውዝግብ ወጥቶ የሰላማዊና የዲፕሎማሲያዊ አቀራረብ አሸናፊ እንዲሆን ግፊት ማድረግ በተለይም ፖለቲከኞች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችና መገናኛ ብዙሃን በዚህ ጉዳይ ላይ የድርሻቸውን ማበርከት ይኖርባቸዋል የሚለውም የፖለቲካ ፓርቲዎቹ መልዕክት ነው፡፡

# ጉባኤው ... ከገጽ 1 የዞረ

(ዶ/ር) ይህን አስመልክቶ በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ባሰፈሩት መልዕክት፤ "ኢትዮጵያ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2027 ኮፕ 32ን በአዲስ አበባ ለማስተናገድ ያቀረበችውን ጥያቄ የአፍሪካ ቡድን ተደራዳሪዎች በሙሉ ድምፅ በማፅደቃቸው ልባዊ ምስጋናዋን ታቀርባለች፡፡ በሰው ልጅ ህልውና ላይ ከተጋረጡ ፈተናዎች አንዱ የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል የጋራ ጥረት የሚጠይቀውን የኮፕ ጉባኤን እንድንመራ ለተሰጠን እድል እናመሰግናለን" ብለዋል፡፡

ኮፕ (COP) የሚለው የእንግሊዘኛ ምህፃረ ቃል (Conference of the Parties) የፓርቲዎች ኮንፈረንስ የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1992 የፀደቀውን የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ስምምነት ፈራሚ ሀገራትና በስምምነቱ መሰረት የተደረጉ የኪዮቶና የፓሪስ ስምምነት የአየር ንብረት ለመከላከል የተገቡ ቃል ኪዳኖች ትግበራ የሚገመገምበት፣ተጨማሪ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ድርድርና ውይይት የሚካሄድበት መድረክ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የኮፕ 32 አስተናጋጅ ሆና መመረጧን ተከትሎ ከሀገር ውስጥ የሥራ ኃላፊዎች፣ ከተባበሩት መንግሥታት አካላት እና ዓለም አቀፍ አጋሮች ጋር በመተባበር የኮፕ 32 ዝግጅትን እንዲመሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) የኮፕ 32 ተወካይ ፕሬዝዳንት ተደርገው ተመድበዋል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት ቁልፍ የዝግጅት ተግባራትን ለማቀናጀት የሚያስችል የብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ስብሰባ በተደረገበት ወቅት ጌዲዮን (ዶ/ር) ባደረጉት ንግግር፣ "ይህ ጉባኤ ከሀገርም ባለፈ አህጉራዊ ፋይዳ ያለው፣ ኢትዮጵያ ዓለምን የምታስተናግድበትና ለቀጣይ ትውልዶች የሚዘልቅ አሻራና ትሩፋት የሚገኝበት ነው" ብለዋል፡፡

"A handbook For Hosting United Nations Climate Change Conference" በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ሰነድ እንደሚያመላክተው፣ ጉባኤው በየዓመቱ የሚካሄድ፣ ትልቅና ወሳኝ መንግስታትን የሚያገናኝ መድረክ ነው። በጉባኤው ላይ ከሀገር መሪዎችና ከፍተኛ ባለስልጣናት እስከ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የተለያዩ በይነ መንግስታት ድርጅቶች መሪዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የቢዝነስና የትምህርት ማህበረሰብ፣ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ጨምሮ በርካቶች ይሳተፉበታል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጌዲዮን (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ ኢትዮጵያ የምታዘጋጀው የኮፕ 32 ጉባኤ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም በመሆኑ አፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥና ተያያዥ ችግሮች ተጠቂና ተጋላጭ ብቻ ሳትሆን መፍትሔ አፍላቂና አመራር የምትሰጥ እንድትሆን መስራት ይጠበቃል፡፡

የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር መሐሙድ አሊ ዩሱፍ ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ጉባኤ (ኮፕ 32)ን እንድታስተናግድ መመረጧ ለኢትዮጵያ እና ለአፍሪካ ታሪካዊ ነው፡፡ አፍሪካ የአየር



የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤና ከፍተኛ አመራሮች ከኡራኤል ብራስ እስከ እንግሊዝ ኤምባሲ የሚዘልቀውን የኮሪደር ልማትና የፒኮክ ፓርክ ግንባታን ሲጎበኙ

ፎቶ- ከገፀ ድር

ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመከላከል ያላትን የማይናወጥ ቁርጠኝነት ያሳያል። ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የመሪነት ሚናዋን እየተወጣች ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ሁነቶችን በስኬት በማስተናገድ እምቅ እና ጠንካራ ተቋማዊ አቅም እና ልምድ አላት። የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫ እና የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችው አዲስ አበባ ጉባኤውን እንድታስተናግድ መመረጧ በዓለም አቀፍ ትብብር ያላትን ማዕከላዊ ሚና የበለጠ እንደሚያሳድግ ያነሱት ሊቀ መንበሩ፣ ኮሚሽኑ ከኢትዮጵያ፣ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ስምምነት (UNFCCC) እና አጋሮች ጋር በመሆን ኮፕ 32 ሁሉን አካታችና ውጤታማ በማድረግ የአፍሪካን የአየር ንብረት የቅድሚያ ትኩረቶች የበለጠ ለማራመድና ዓለም አቀፍ አጋርነት ለማጠናከር በቅርበት እንደሚሰራ ጠቁመዋል፡፡

አዲስ አበባ ጉባኤውን በተሳካ ሁኔታ ለማስተናገድ ዝግጅት እያደረገች ትገኛለች፡፡ ከተማዋ በቅርብ ዓመታት ትላልቅ ዓለም ዓቀፍ ኹነቶችን ማስተናገድ የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶችን በሰፊው ገንብታለች፡፡ አዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ በኮሪደር ልማትና ወንዝ ዳርቻ ልማት መንገዶችን የማስፋት፣ ደረጃቸውን የማሳደግ፣ የእግረኛና ሳይክል መንገዶችን የመገንባት፣ አረንጓዴ ስፍራዎችን በማስፋት ፅዱና ውብ ማድረግ ችላለች፡፡

ቆስጠንጢኖስ በርኼተስፋ (ዶ/ር) በተባበሩት መንግስታት በአስተዳደር፣ ድህነትና ዘላቂ ልማት ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የፖለሲ አማካሪ፣ በአፍሪካ ሰብዓዊ ኔትዎርክና የተለያዩ የጥናትና ምርምር ተቋማት ቦርድ ሰብሳቢና አባል በመሆን ሰርተዋል፡፡ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሚሰሩበት ወቅት እንዲሁም በቅርቡ በተካሄዱት የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ፣ ዱባይ እና በቅርቡ ብራዚል በተካሄዱ የኮፕ ጉባኤዎች ላይም ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅረብ ተሳትፈዋል፡፡

ኢትዮጵያ የኮፕ 32 ጉባኤን እንድታስተናግድ መመረጧ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ እንዳለው የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ያስረዳሉ፡፡

ጉባኤውን ለማስተናገድ ኢትዮጵያ የተመረጠችው አንደኛው ምክንያት የአየር ንብረት ለውጥ አጀንዳን ቀዳሚ አድርጋ በመስራቷ ነው፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መሪነት በአረንጓዴ አሻራ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ችግኝ በመትከል የተገኘው ውጤት ነው። ከዚህ ባሻገር አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ማዕከል ብሎም ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን የምትወክል ከተማ በመሆኗ እድሉን እንድታገኝ አድርጓታል ብለዋል፡፡

በቅርቡ በብራዚልም ቤሌም በተካሄደው ጉባኤ ላይ ከ50 ሺህ በላይ እንግዶች ታድመዋል፡፡ ብራዚል በርካታ ሰዎችን ማስተናገድ የሚችል አዳራሽ በመገንባት ጉባኤውን ማካሄድ ችላለች። ከሁለት ዓመት በኋላ የሚካሄደውን ጉባኤ ለማስተናገድም ኢትዮጵያ ሰፊ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባታል። በአንድ ጊዜ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የሚታደሙበት እንደመሆኑ፣ ጉባኤው የተሳካ እንዲሆን ከትራንስፖርት ጀምሮ የመንገድ፣ የሆቴል፣ አዳራሽና ሌሎች አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ያስገነዝባሉ፡፡

በጉባኤው በርካታ እንግዶች የሚሳተፉበት በመሆኑ የሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተሳታፊ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ በአንዳንድ አካላት የሚናፈሰውን "ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም የለም፤ ከከተማ እንዳትወጡ" የሚለውን ትርክት ይቀይራል፡፡ ይህም ቱሪስቶች በስፋት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ይስባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን አመኔታ በማሳደግ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈስሱ ያበረታታል ይላሉ፤ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፡፡

ኢትዮጵያ ለጉባኤው ተሳታፊዎች የተሻለ አገልግሎት ለማቅረብ የምታደርገው ዝግጅት የመንግስት ተቋማት አገልግሎት ዝግጁነትን በማሳደግ በኩልም ጥቅም ያስገኛል። በቀጣይ የአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚሰሩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋሙበትና ጥናትና ምርምር የሚደረግበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የምጣኔ ሀብት ምህሩ ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ አፍሪካ ለአየር ንብረት ለውጥ መከሰት የጎላ ዓይነት አስተዋፅኦ ሳይኖራት የችግሩ ተጠቂና ሰለባ ናት፡፡ ከዚህ አኳያ አፍሪካን ራሷን በመቻል ከችግሩ እንዴት መውጣት ትችላለች? የሚለውን አጀንዳ ኢትዮጵያ መምራት የምትችልበትን እድል ይፈጠራል፡፡

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ምሁር ይንገስ ዓለም (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የኮፕ 32 ጉባኤ ትልቅና በርካታ ሰዎች የሚታደሙበት በመሆኑ በብዙ መልኩ ትርፋማ ያደርጋል፡፡ የአዲስ አበባን የኮንፈረንስ ቱሪዝም መዳረሻነት ከፍ ያደርጋል፡፡ ከተማዋ ያላትን የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለማሳየትና ለመሸጥ ያስችላል፡፡ የኢትዮጵያ ተወካዮችና ተሳታፊዎች ከተለያዩ ሀገራት ተሳታፊዎች ጋር የሚገናኙበት፣ የሚነጋገሩበትና በዚያውም ሀገርን ማሳወቅ የሚቻልበትና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የሚጠናከርበት ዕድል ይፈጥራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለእንግዶች ከትራንስፖርት አንስቶ የምግብና መኝታ አገልግሎቶች በሚቀርብበት ወቅት የሚገኘው ገቢ ለከተማና ሀገር ትልቅ ትርጉም አለው። እንግዶቹ ባገኙት አገልግሎት የሚረኩ ከሆነ የቆይታ ጊዜያቸውን በማራዘም በከተማዋ የሚገኙ የቱሪስት መስህቦችን የሚጎበኙበት ሁኔታ ይፈጠራል" ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ሰሞኑን በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ከኡራኤል እስከ ብራስ፣ ከቦሌ መድኃኔዓለም- ጎላጎል እስከ እንግሊዝ ኤምባሲ የሚዘልቀውን የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት እና የፒኮክ (ማዕከላዊ) ፓርክ ግንባታን እንቅስቃሴ በመስክ በመገኘት በጎበኙበት ወቅት፣ "ኢትዮጵያ የዓለምን ትኩረት የሚስበውን የኮፕ 32 ጉባኤን የምታስተናግድ መሆኗ እድለኛ ናት" ብለዋል፡፡ በኮሪደር ልማቱ የአደይ አበባ ስታዲየም ግንባታ የሚከናወንበት አካባቢ አንዱ ጉባኤው የሚካሄድበት ማዕከል በመሆኑ አስቀድመዉ የተጀመሩ የኮሪደርና ሌሎች መሠረተ ልማት ግንባታዎች በፍጥነትና በጥራት እንዲከናወኑ እየተሰራ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ከንቲባዋ በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ባሰፈሩት መልዕክት፣ "የኮፕ 32 ጉባኤ ከዓለም ዙሪያ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች የሚታደሙበት በመሆኑ፣ ጉባኤው በአዲስ አበባ መዘጋጀቱ ከሀገር መልካም ገፅታ ግንባታ በተጨማሪ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በገበያ ትስስር እንዲሁም መሰል ዓለም አቀፍ ኩነቶችን ወደ ሀገራችን በቀጣይነት ለማምጣት ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብለዋል።

"መላው የከተማችን ነዋሪዎችና የንግዱ ማኅበረሰብ በተሰማራንበት የሥራ መስክ ጉባኤው ይዞት የሚመጣውን መልካም ዕድል አሟጥጠን እንድንጠቀም እና ለጉባኤው ስኬታማነትም ከወዲሁ ሁላችንም ዝግጅት እናድርግ" ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከፍተኛ ታዳሚዎች የሚሳተፉባቸውን ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በማስተናገድ ጥሩ ልምድ አላት የሚሉት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ይንገስ (ዶ/ር)፣ "የኮፕ 32 ጉባኤ የተሳካ እንዲሆን መንግስትና ማህበረሰቡ በተናበበና በተቀናጀ መልኩ እንግዶችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆቴሎችና የተለያዩ አገልግሎት ሰጪዎች ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ የመብራት፣ ውሃ፣ ኢንተርኔት፣ የትራንስፖርት እና ሌሎች አገልግሎቶችን የተቀላጠፈ በማድረግ፣ እንግዳ ተቀባይነታች በተግባር ማሳየታችንን አጠናክረን ማስቀጠል ይጠበቅብናል" ብለዋል፡፡

# “ወደ ኋላ የቀረንባቸውን ጊዜያት በሚያካክስ መልኩ መፍጠን ይጠበቅብናል”

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር)**

**በደረጀ ታደሰ**

መፍጠር፣ መፍጠን፣ ማብዛትና ማጥራት የሚሉት እሳቤዎች የመደመር መንግሥት ዋነኛ ማጠንጠኛዎች ናቸው፡፡ የእነዚህን እሳቤዎች ምንነት እና አስፈላጊነት የመደመር ፍልስፍና አመንጪ የሆኑት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጽፈው ለንባብ ባበቋቸው “መደመር፣ የመደመር መንገድ፣ የመደመር ትውልድ እና የመደመር መንግሥት” መጽሐፍት በስፋት እና በጥልቀት ተንትነው አቅርበዋል፡፡ በተለያዩ ሠፋፊ መድረኮች ላይም ሃሳቡን ለማስረፅ ጥረዋል፤ አሁንም በዚሁ ትጋታቸው ቀጥለዋል፡፡ እሳቤዎቹን በንድፈ ሃሳባዊ መልኩ ተንትኖ ከማቅረብ እና ከማስረዳት ባሻገር መሬት በነካ ተግባራዊ የሥራ ውጤት አሳይተዋል፡፡

በዚህ ጽሑፍ ጥልቅ እና ሠፊ ከሆነው የመደመር መንግሥት እሳቤዎች ውስጥ “መፍጠን” የሚለውን ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡ በተለይ በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ካለመችው የዕድገት እና የብልፅግና ማማ ላይ ለመድረስ መፍጠን ግዴታዋ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? የመፍጠን እሳቤን በተግባር እየገለጡ ለመጓዝ እንዴት ይቻላል? የመፍጠንን እሳቤ ተግባራዊ በማድረግ የሚገኘው ተጠባቂ ውጤት ምንድን ነው? የሚሉ ነጥቦችን በማንሳት ከመደመር መንግሥት መጽሐፍ፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች በመጽሐፉ ፀሐፊ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከቀረቡ ገለፃዎች እንዲሁም በጽሑፉ ላይ ምሁራዊ እይታቸውን ያጋሩንን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሠላምና ደህንነት ተመራማሪ ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር) ሃሳብ በማከል እንመለከታለን፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “የመደመር መንግሥት” በተሰኘው መጽሐፋቸው፤ ኢትዮጵያ ያለባትን የልማት ክፍተት ለመድፈን እና ብልጽግናን ለማምጣት የመፍጠርን፣ የመፍጠንን (ፍጥነትን)፣ የማብዛትን እና የማጥራትን እሳቤዎች እንደ ቁልፍ ስልቶች መጠቀም እንደሚገባት አፅንኦት ሰጥተው አብራርተዋል፡፡ መጽሐፉ ኢትዮጵያ ያለባትን የድህነት አዙሪት ለመስበር እና የዓለም ተምሳሌት ለመሆን ከባህላዊ አቀራረቦች ወጥታ፣ በእነዚህ አራት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ሁሉን አቀፍ እና ተጨባጭ የሥራ መመሪያ (blueprint) እንደሚያስፈልጋት ይተነትናል፡፡

ከእነዚህ አራት መሰረታዊ እሳቤዎች መካከል አንዱ የሆነው መፍጠን (ፍጥነት) (Speed/Acceleration): በመደመር መንግሥት መጽሐፍ ውስጥ በስፋት እና በጥልቀት ተተንትኗል፡፡ ጭብጡም፤ እጅግ በፈጠነው ዓለም አቀፍ ውደት ውስጥ የኢትዮጵያን አዝጋሚ እንቅስቃሴ አይጠብቁም። በመሆኑም ሀገሪቱ ከዓለም አቀፉ የዕድገት እና ብልፅግና ጉዞ በተፎካካሪነት ለመሳተፍ በዘርፈ ብዙ የልማት መስኮች በፍጥነት



ፎቶ-ከፋይል
በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር)

መንቀሳቀስ አለባት። ለዚህ ደግሞ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ግድ ይላል፡፡ “ዛሬ” ላይ በማተኮር ብቻ ወደፊት መገስገስ እንደሚያስፈልግ የሚገልፅ ነው፡፡

የመደመር መንግሥት መጽሐፍ ዋነኛ ጭብጥ የፍጥነትና የፈጠራ ፍኖት ማብራራት እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተለያየ ወቅት አብራርተዋል። በመጽሐፉ የመፍትሔ ፍሊጋ ቀጣይ ጥረት ሌላኛው ውልደት መሆኑንም ደጋግመው ጠቁመዋል። “ፍጥነታችን መስፈንጠር አለብን ብሎ ያምናል፡፡ የተከማቸብን ችግር በቀላል ፍጥነት ብቻ የሚገታ አይደለም። የትላንቱን ችግር ለመፍታት ስንጥር የዛሬው ይቀረናል፣ የዛሬውን ልንፈታ ስንል የነገው ይደርሰናል። ለዚህ ነው ፍጥነታችን መስፈንጠር እንደሆነ የምናምነው።።” በማለትም የፍጥነት እሳቤን አስፈላጊነት በመጽሐፉ ገፅ 24 ላይ አስፍረዋል፡፡

ፍጥነት እና ፈጠራ የሚሉት እሳቤዎች ለሀገር ዕድገት እና ብልፅግና ቁልፍ መሣሪያዎች ስለመሆናቸው በመደመር መንግሥት መጽሐፍ ምርቃት መርሃ ግብር በተዘጋጀ መድረክ ላይ ስለመጽሐፉ ትንታኔ ያቀረቡት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍፁም አሰፋ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡ የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ በመድረኩ ላይ እንዳብራሩት፤ የመደመር መንግሥት እንዴት ወደኋላ ቀረን? ከዓለም ጋር የቱ ጋር ተላለፍን? ለሚሉ ጥያቄዎች ግልጽ መልስ እና መፍትሔ ይዟል፡፡ ከኋላቀርነት በመላቀቅ ዓለም የደረሰበት ደረጃ እንዴት መድረስ እንዳለብን አመላክቷል፡፡ በየዘርፉ አዳዲስ የፈጠራ ውጤቶችን መፍጠር፤ እነዚህን የፈጠራ ውጤቶች ደግሞ በፍጥነት ወደ ሥራ ማስገባት እና እንደአስፈላጊነቱ ደግሞ የዝላይ ስልቶችን በመከተል የሀገራችንን ብልጽግና ማረጋገጥ የዚህ ትውልድ ዋነኛ ኃላፊነቱ እንደሆነም በመጽሐፉ ተዘርዝሯል፡፡ የመደመር እሳቤን በመተግበር እና በመደመር ላይ የተቃኘ መንግሥትን በመመስረት ሀገራችንን ወደነበረችበት የኢኮኖሚ እና የስልጣኔ ከፍታ መመለስ፤ ሕዝባችንን ደግሞ ወደ ሁለንተናዊ ብልጽግና ማሸጋገር ስለመሆኑም አሳይቷል፡፡

በሦስት ክፍሎች፣ በ13 ምዕራፎች እና በ78 ርዕሰ ጉዳዮች የተዋቀረው የመደመር መንግሥት መጽሐፍ እነዚህን አራት መሰረታዊ እሳቤዎች (መፍጠር፣ መፍጠን፣ ማብዛት እና ማጥራት) መሰረት በማድረግ ሁለገብ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና የማህበረሰባዊ ክንውኖችን ሁኔታ ከመሰረቱ ዳስሷል። መነሻውም የኋላ ታሪካችን ነው። የት ነበርን? የሚለው ከነትርክቱ ጭምር ተዳስሷል። በዚህም የቀደመው ዘመን ጥንካሬዎቻችን ምን ነበሩ? ድክመቶቻችንስ? የሚሉ ሀሳቦችን በስፋት አንስቷል።

“የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በመደመር መንግሥት መጽሐፋቸው ውስጥ የጠቀሷቸው በርካታ ጉዳዮች ያሉ ሲሆን፤ በመሰረታዊነት በሦስት አንኳር ነጥቦች ላይ ያተኮረ ሆኖ አገኘዋለሁ” የሚሉት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር)፤ እነዚህን አንኳር ነጥቦች ያብራራሉ፡፡ እንደሳቸው ገለፃ፤ የመጀመሪያው የመደመር መንግሥት አንኳር ነጥብ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ምንነት ላይ ያጠነጠነው ነው፡፡ ትላንትና ምን ነበርን?፣ ዛሬስ የት ነው ያለነው?፣ ነገ ምን ሊሆን ይችላል?፣ ታሪካችን፣ ፖለቲካችን፣ ኢኮኖሚያችን ያለፈበትን፣ አሁን ያለበትንና የቀጣይ መዳረሻው የሚተነተንበት ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ፤ በዓለም ማዕቀፍ ውስጥ ኢትዮጵያን የተመለከቱበት ነው። ዓለም መቼ ነው ያደገው?፣ ዓለም የኢንዱስትሪ አብዮትን ሲያከናውን እኛ ምን ሆንን?፣ ከዓለም ፈጣን ዕድገት ውስጥ እኛ ተነጥለን እንዴት ነው የዘገየነው?፣ የቱጋ ነው የተዘናጋነው?፣ ለምንስ ነው የተዘናጋነው?፣ እንዴትስ ተንሸራተን ጠፋን? የሚሉት ሃሳቦች የተተነተኑበት ነው፡፡ የጊዜ ታላቅነት የተዳሰሰበት በሦስተኛነት ይጠቀሳል፡፡ በመደመር መንግሥት መጽሐፍ ውስጥ የጊዜ ታላቅነት (አስፈላጊነት) አጽንኦት ተሰጥቶት እንመለከታለን፡፡ በዚህ ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች በጊዜ መመለስ፣ ከዓለም ጋር ለመወዳደር አቅም መፍጠር፣ ለመቅደም መፎካከር የሚሉት በጥልቀት ተተንትነዋል፡፡ የመሸጋገሪያ መንገዱ ምን መሆን እንዳለበትም አመላክተዋል፡፡ ለምሳሌ ይዘን የመጣነው የሥራ ባህል፣ ሥራዎችን የመራንበት መንገድ፣ ውጤቱን የመዘንንበት ሂደትን በመቃኘት፤ ከዚህ ሁሉ የተወሳሰበ ችግር ለመውጣት እያንዳንዱን ሥራ በፍጥነት፣ በፈጠራ እና የውድድር መንፈስን በተከተለ አግባብ መሆን እንዳለበት ተጠቁሟል፡፡

“ሥራዎችን ከጊዜና ከወቅት ጋር አቀናጅቶ በፍጥነት እና በጥራት መተግበር ወሳኝ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደጋግመው ሲናገሩ ይደመጣል፤ በመጽሐፍታቸው ላይ አስፍረዋቸው እንመለከታለን” በማለት ምሁራዊ ዕይታቸውን ያካፈሉን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ሙሉጌታ (ዶ/ር)፤ ጥያቄዎች በጊዜና በተገቢው መመለስ እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመደመር መንግሥት መጽሐፋቸው መግለጻቸውን፣ ለዚህ ደግሞ የትውልድ ግንባታ ጉዳይ በቀዳሚነት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ፣ የሀገራችን እጣ ፈንታ በልጆቿ እጅ ላይ እንደሆነ መጠቆማቸውን አብራርተዋል፡፡

ይህንን በተመለከተ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “በመደመር ትውልድ መጽሐፋቸው ክፍል ሦስት ምዕራፍ ሰባት ላይ፤ ‘እኛ ኢትዮጵያዊያን አሁን ላለንበት የድህነት አዙሪት ዋናው ማሳያችን ጊዜውን ያገናዘበ መፍትሔ ባለመስጠታችን የተጋፈጥነው ጦስ ነው፡፡ ይህም ጦርነት ነው፡፡ የእርስ በእርስ ግጭት ነው፡፡’ ይሉና፤ ይህንን ለማስቀረት ‘ከችግሮቻችን ለመላቀቅ መፍጠን አለብን፡፡ አዳዲስ ነገሮችን መፍጠርና መጠቀም ይገባናል፡፡ ዓለም ጥሎን ብዙ ርቆ ሄዷል፡፡ ዓለም በሚጓዘው ፍጥነት መሄድ ከባድ ይሆንብናል፡፡ በዚህ ጊዜ ዓለም የተጓዘባቸውን የዕድገት ሂደት ደረጃዎች መከተል አይጠበቅም፡፡ አንዳንዶቹን በመዝለል ወደፊት መገስገስ አስፈላጊ ይሆናል” በሚል መግለፃቸውን ሙሉጌታ(ዶ/ር) አስረድተዋል፡፡

“የመደመር መንግሥት መጽሐፍ ከቁጭት የሚነሳ ነው፡፡ ዓለም በዚህ ፍጥነት እና በዚህ ደረጃ ሲያድግ ‘ኢትዮጵያ ለምን ወደ ኋላ ቀረች’ የሚለውን ቁጭት አዘል ጥያቄ ያነሳል፡፡ የችግሮቹ አስኳል ከአስተሳሰብ ጉድለት የመነጨ እንደሆነም ያስቀምጣል፡፡ የመፍትሔ አቅጣጫዎችንም ያመላክታል” በማለት ምሁራዊ ዕይታቸውን ያካፈሉን ሙሉጌታ(ዶ/ር) መፍጠን ለኢትዮጵያ ግድ እንዲሆን ያደረገው ምክንያትን አብራርተዋል፡፡

እንደሳቸው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የመፍጠን እሳቤን ተግባራዊ እንድታደርግ አስገዳጅ ከሆኑ ምክንያቶች ዋነኛው ዓለም ያለበት ነባራዊ ሁኔታ ነው፡፡ ዓለም በከፍተኛ የዕድገት ግስጋሴ ላይ ነው፡፡ አሁን ላይ የቴክኖሎጂ ልህቀት ከፍታው ወደ ሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ) ደረጃ የደረሰበት ነው፡፡ እንደ ውቅያኖስ ሰፊ እና ጥልቅ በሆነው ዓለም ውስጥ ቆሞ መጠበቅ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ቆሞ የጠበቀ በውቅያኖሱ ይሰምጣል፤ ይጠፋልም። ስለዚህ እኛ ከቀሪው ዓለም ጋር ለመወዳደር እና ለመፎካከር፤ ለዘመናት ወደ ኋላ የቀረንባቸውን ጊዜያት ቁጭትን በሚያካክስ መልኩ ለመከወን እጅግ በጣም መፍጠን ይጠበቅብናል፡፡ ለምሳሌ የሥራ ባህላችን ላይ መፍጠን የሚለውን መርህ በአግባቡ መተግበር

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የአስተዳደራዊ ውሳኔዎች

## ክፍል ሁለት

ጌታነህ በላይ (ዐቃቤ ህግ)

ውድ አንባቢዎቻችን ባለፈው ዕትም በዋና ርዕስ ስር የአስተዳደር ውሳኔ ምንነት እና የተፈፃሚነት ወሰን፣ አስተዳደራዊ ውሳኔ አጀማመር፤ጥያቄ ማቅረብ እና የአስተዳደር ግዴታዎች እንዲሁም የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት፣ መርሆዎችን የሚፈፅመው አካል በተመለከተ እና ተያያዥ ጉዳዮችን አስነብበናችኋል። ክፍል ሁለትን እንደሚከተለው አዘጋጅተንላችኋል፡፡ መልካም ንባብ።



### 3. የአስተዳደር ውሳኔ የሚታገድበትና ቅሬታ የሚቀርብበት ሁኔታ

#### 3.1. የአስተዳደር ውሳኔ የሚታገድበት ሁኔታ

የአስተዳደር ውሳኔን በፍጥነት መፈፀም መብቱ ወይም ጥቅሙ ላይ የማይቀለበስ ጉዳት የሚያስከትልበት ማንኛውም ወገን ውሳኔው እንዲታገድለት ለውሳኔ ሰጪው ተቋም ማመልከት ይችላል።

ከዚህ በተጨማሪም ማንኛውም ሰው በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ለቅሬታ ሰሚው አካል ካቀረበ በቅሬታው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የውሳኔው አፈጻጸም ይታገዳል። ይሁን እንጂ ለዚህ አጠቃላይ የአፈፃፀም እገዳ ወሳኝ የሆነ ልዩ ሁኔታ ያለው ነው፡፡

ይህም የተቋሙ የበላይ ኃላፊ አፈጻጸሙ በመዘግየቱ ምክንያት በሕዝብ ጥቅም ላይ የማይቀለበስ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ብሎ ካመነ ውሳኔው ወዲያውኑ እንዲፈፀም ሊያዝዝ ይችላል። ይህ ድንጋጌ የዜጎችን የሥነ ሥርዓት መብት ከመጠበቅና የአስተዳደርን ውጤታማ አሠራር ከማረጋገጥ መካከል ያለውን ሚዛን ያሳያል።

#### 3.2. በአስተዳደር ውሳኔ ስለሚቀርብ ቅሬታ

በአስተዳደራዊ ውሳኔ መብቱ ወይም ጥቅሙ የተነካ ማንኛውም ሰው ውሳኔውን በሰጠው ተቋም ውስጥ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው። ቅሬታው ውሳኔው እንዲሰረዝ ወይም ይዘቱ፣ ሕጋዊ መሠረቱና ማስረጃው እንደገና እንዲታይ የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል።

#### 3.3. የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ስለማቋቋም

ሁሉም የአስተዳደር ተቋማት የቅሬታ ሰሚ አካል እንዲያቋቁሙና ለደንበኞቻቸውም ይህን ማስታወቅ እንዳለባቸው በሕግ ግዴታ ተጥሏል። የቅሬታ ማስተናገጃ አካሉ ቅሬታውን በትክክል ከመረመረ በኋላ የውሳኔ ሃሳቡን ለተቋሙ ኃላፊ ወይም ሥልጣን ለተሰጠው ባለሥልጣን ያቀርባል። ይህ ኃላፊ የቅሬታ ማስተናገጃ አካሉን የውሳኔ ሃሳብ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚሰጠው ውሳኔ የተቋሙ የመጨረሻ ውሳኔ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህ ሥርዓት ፍርድ ቤት ከመሄድ በፊት ችግሩ በአስተዳደር አካሉ ውስጥ እንዲፈታ እና አስተዳደሩ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ እድል የሚሰጥ ነው።

**የፌዴራል አስተዳደራዊ ሥነ ሥርዓት አዋጅ በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ የፍርድ ቤት ክለሳ እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት በግልጽ አስቀምጧል። ጥቅሙ የተነካበት ማንኛውም ሰው ውሳኔውን በፍርድ ቤት እንዲታይለት የመጠየቅ መብት አለው። ክለሳውን የማየት ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው**

### በፍርድ ቤት የአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚከለስበት ሥርዓት

የፌዴራል አስተዳደራዊ ሥነ ሥርዓት አዋጅ በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ የፍርድ ቤት ክለሳ እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት በግልጽ አስቀምጧል ። ጥቅሙ የተነካበት ማንኛውም ሰው ውሳኔውን በፍርድ ቤት እንዲታይለት የመጠየቅ መብት አለው። ክለሳው የማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው።

ለፍርድ ቤት ክለሳ መቅረብ የሚቻለው ተቋሙ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ብቻ ሲሆን፤ በሌላ ሕግ ካልተደነገገ በስተቀር ከፍርድ ቤት ክለሳ በፊት አመልካቹ በተቋሙ ውስጥ የሚገኙትን የውስጥ የይግባኝ መፍትሔዎች በሙሉ መጠቀም ይጠበቅበታል። ይሁን እንጂ አስተዳደር ተቋሙ አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት ያላግባብ የሚዘገይ ከሆነ ተገልጋዩ የክለሳ አቤቱታ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ይህ ድንጋጌ ተቋሙ በዝምታ ወይም በመዘግየት የዜጎችን ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳያደናቅፍ ያደርጋል። የክለሳ ጥያቄውም የመጨረሻው ውሳኔ ባለጉዳዩ እንዲያውቀው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።

### ፍርድ ቤቱ የክለሳ አቤቱታውን ሲመለከት መከተል የሚገባው ሥነ ሥርዓትና የሚሰጠው ውሳኔ

ፍርድ ቤቱ የክለሳ ጥያቄው አግባብ መሆኑን ካመነ አስተዳደራዊ ተቋሙ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ምላሽ እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጣል። በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ በክለሳ ላይ ከቀረበው ውሳኔ ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶችን ለአስተዳደር ተቋሙ እንዲያቀርብ የማዘዝ ሥልጣን አለው።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክለሳው ላይ ሊሰጣቸው የሚችላቸው ውሳኔዎች ሰፊ ናቸው። ፍርድ ቤቱ የአስተዳደር ውሳኔውን ሊያጸድቅ፣ ሊሽር ወይም ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይለት ወደ አስተዳደር ተቋሙ ሊመልስ ይችላል። ለፍርድ ቤቱ ውሳኔውን የመሻር ሥልጣን መሰጠቱ፣ ክለሳው የተቋሙን የሥነ ሥርዓት ሂደት በጥልቀት የሚመለከት መሆኑን ያመለክታል።

ከሁሉም በላይ ግን ፍርድ ቤቱ የአስተዳደር ተቋሙ በሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ በጠያቂው ላይ ጉዳት እንዳደረሰ ካረጋገጠ ጉዳት ለደረሰበት ሰው ካሳ እንዲከፈለው ሊወስን ይችላል። ይህ ካሳ የአስተዳደር ተቋሙ ላደረሰው ጉዳት የመንግሥት ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሲሆን፤ አስተዳደራዊ አካላት ሕጉን በጥብቅ እንዲከተሉ የሚያስገድድ ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ ነው። በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔውም የመጨረሻ ሲሆን ይግባኝ አይጠየቅበትም።

ኢኮኖሚ

# ገበያዎቹ የሸማቾችን የኑሮ ጫና ምን ያህል እያቀለሉ ነው?

- በከተማዋ በ227 የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች ግብይት እንዲፈጸም እየተደረገ ነው
- 15 ምርት አቅራቢ ነጋዴዎች ላይ የፅሑፍ፣ 6ቱ ላይ ደግሞ የቃል ማስጠንቀቂያ እንዲሁም 5ቱ ላይ ትስስራቸውን በማቋረጥ በተመደቡበት ቦታ ምርት እንዳያቀርቡ ተደርጓል



ፎቶ-ከፋይል
በቅዳሜ እና እሁድ ገበያ ላይ ሸማቾች ግብይት ሲከውኑ

**በሄለን ጥላሁን**

አዲስ አበባ ማህበራዊ ፍትህ የሰፈነባት ከተማ ትሆን ዘንድ ከተማ አስተዳደሩ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ከዚህ ውስጥ ለኑሮ ውድነቱ መፍትሔ ይሆኑ ዘንድ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉትን የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የዝግጅት ክፍላችንም በእነዚህ ገበያዎች የግብርና እና የፋብሪካ ምርቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ ከማድረግ ባሻገር በተጨባጭ የኑሮ ውድነቱን ከማቃለል አንፃር እያበረከቱት ስላለው አስተዋጽኦ ከሸማቹ ማህበረሰብ፣ ከሻጮች እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ያሰባሰባቸውን መረጃዎች እንደሚከተለው አጠናቅሯቸዋል፡፡

## ሸማቾች ስለግብይቱ ያላቸው አስተያየት

ወይዘሮ ሲፈን ሙሉነህ ይባላሉ፡፡ ነዋሪነታቸው አዲስ ሰፈር አስኮ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሲሆን የቅዳሜና የእሁድ ገበያ ላይ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ሲሸምቱ አግኝተናቸዋል፡፡ በሳምንት አንዱን ቀን ማለትም ቅዳሜን ለአስቤዛ መሸመቻ በሚል አቅደዋል፡፡ በተለይ ትኩስ የግብርና ምርቶችን እንደ ሽንኩርት፣ ድንች እንዲሁም ቲማቲም ያሉ ምርቶችን ይገዛሉ፡፡ በእነዚህ ገበያዎች በመደበኛ ሱቆች ላይ ከሚሸጠው ቢያንስ የ15 ብር ልዩነት እንዳለው የሚናገሩት እኚህ እናት፣ የተረፋቸውን ብር አብቃቅተው ለሌላ ነገር መግዣ ጭምር እንደሚሆናቸው ገልፀዋል፡፡

በእነዚህ ገበያዎች አልፎ አልፎ የሚያስተውሏቸው እንከኖች ባይጠፉም፤ እርሳቸው ግን የተለጠፈውን የሰንበት ገበያ ዋጋን መሰረት ያደረገ ግብይት እንደሚከውኑ ተናግረዋል፡፡ ይህ መረጃ በተጠናቀረበት ወቅት አንደኛው ድንኳን

> “መንግስት ዋጋ ተምኖ ይለጥፋል። ነገር ግን ሸማቹ ማህበረሰብ ዋጋ ስንት ነው? ብሎ የመጠየቅ አዝማሚያ በስፋት አለ። ይህ ደግሞ ሻጩ ዋጋ ጨምሮ እንዲናገር እድል ይፈጥራል”

የተለጠፈው ዝርዝር ላይ አንድ ኪሎ ሽንኩርት 35 ብር እንደሆነ ቢጠቀስም፣ ሻጭው አካል 45 ብር የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህ ጊዜ በተቀመጠው ዋጋ መሰረት እንዲሸጥ ካልሆነ ግን ቅሬታ እንደሚያቀርቡ ሲናገሩ ወዲያው ህጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ ግብይት መፈጸም ችለዋል፡፡ በተመሳሳይም የአንድ ኪሎ ቲማቲም እና ድንች ዋጋ በቅደም ተከተል በ40 ብር እና በ25 ብር እንደሸመቱ ተናግረዋል፡፡

አቶ ታሪኩ አርጋው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ንግድ ጽህፈት ቤት ቡድን መሪ ናቸው፡፡ በቅዳሜ እና እሁድ ገበያ ላይ ለሚደረገው ግብይት ከምርት ጥራት እንዲሁም ከዋጋ ጭማሪ ጋር በተገናኘ ለሚነሱ ቅሬታዎች በቅርበት ሆነው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ በተለይም ለቀረቡ የምርት አይነቶች የተቀመጠውን የዋጋ ዝርዝር ታሳቢ በማድረግ ግብይት በማይፈፅሙ ሻጮች ላይ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ አስታውቀዋል፡፡ በቅዳሜና እሁድ ገበያዎች የግብርና እና የፋብሪካ ምርቶችን በጥራት ብሎም በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ነጋዴዎች የስምምነት ሰነድ ተፈራርመው ወደ ስራ ይገባሉ፡፡ ከዚህ የስምምነት ሰነድ ውጭ ሲነግዱ በተገኙ አካላት ላይ የቃል፣ የፅሑፍ እንዲሁም ከትስስር እንዲወጡ እስከማገድ የደረሰ ስራ ይሰራል፡፡ ከሀምሌ ወር 2017 ዓ.ም እስከ ህዳር ወር 2018 ዓ.ም ድረስ ቁጥራቸው 6 ለሚሆኑ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ ባደረጉ ነጋዴዎች ላይ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ስለመሰጠቱ አስታውቀዋል፡፡

ሌላኛውን ቅኝት ያደረግነው በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 በተለምዶ ጨርቆስ አደባባይ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኝ የቅዳሜና እሁድ ገበያ ላይ ነው። እለቱ እሁድ በመሆኑ በርካታ ሰዎች አስቤዛ ሲሸምቱ ተመልክተናል፡፡ ከእነዚህ መካከል ወይዘሮ ትዝታ ምትኩ አንዷ ናቸው፡፡ ከግብርና ምርቶች ቲማቲም፣ ጥቅል ጎመን እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርት የሆነውን አንደኛ ደረጃ የዳቦ ዱቄት እና ፓስታ ለመሸመት መጥተዋል፡፡ ከዋጋ አንፃር እንደ ቅደም ተከተላቸው አንዱን ኪሎ በ40 ብር፣ በ25 ብር፣ በ115 ብር እና በ92 ብር ሸምተዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ትዝታ ገለፃ፤ በእነዚህ ገበያዎች ያለው ዋጋ በመደበኛ ሱቆች ካለው ጋር ሲነጻጸር በትንሹ የ15 ብር ልዩነት አለው፡፡ በርከት ያሉ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በአንድ ቦታ ላይ ማግኘት ችለዋል፡፡

ከግብይት ሂደቱ ጋር በተያያዘ ትዝብታቸውን፣ “አንዳንድ ነጋዴዎች እንደ ቲማቲም ድንች ያሉትን ምርቶች ከተበላሸው ጋር ቀላቅለው ይሸጣሉ” ሲሉ አጋርተዋል፡፡

አቶ አዲሱ በየነ በአስተያየታቸው፣ “እንደ ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ቃሪያ፣ ጥቅል ጎመን፣ ፎሶሊያ፣ ነጭ ሽንኩርት እና መሰል ምርቶችን እሸጣለሁ። ደንበኞቻችን በምንሰጣቸው አገልግሎት ተደስተው ቀጣይም እንዲመጡና የእኛን ምርት እንዲገዙ እንፈልጋለን፡፡ ያንን ለማድረግ ደግሞ ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማቅረብ እንዲሁም መንግስት እንድንሸጥ ባወጣልን ተመን መሰረት ግብይት መፈፀም ይጠበቅብናል” ብለዋል፡፡

## ክፍተቶችን ለመሙላት የተሄደበት ርቀት

በመዲናዋ ፍትሐዊ የግብይት ስርዓት እንዲኖር ከማድረግ አኳያ በቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለተጠቃሚዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እና ጥራት ተደራሽ የማድረግ ስራ እየተሰራ ስለመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የንግድ ግብይት ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ መከተ አዳፍሬ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል። “የከተማዋን ነዋሪ የኑሮ ውድነት ጫና መቀነስ ያስችል ዘንድ እነዚህ ገበያዎች ሁነኛ መፍትሔ ናቸው። እንደ ከተማ ባሉን አስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች ቁጥራቸው 227 የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎችን በመክፈት ትርጉም ያለው ስራ እየሠራ ይገኛል” ሲሉም አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ መከተ ገለፃ፤ ባሳለፍነው 2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ 219 የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች ነበሩ፡፡ በያዝነው 2018 በጀት ዓመት ቁጥራቸውን ወደ 240 ለማድረስ ቢሮው አቅዶ እየሰራ ይገኛል፡፡ በአንድ ወረዳ ከአንድ በላይ የቅዳሜ እና እሁድ ገበያ እንዲኖር በማድረግ የተደራሽነት አድማሱን የማስፋት ስራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የቅዳሜ እና እሁድ ገበያ ሲመሰረት የራሱ የሆነ የአሰራር ሂደት አለው የሚሉን አቶ መከተ ከአሰራሮቹ አንዱ ምርቶችን የሚያቀርቡ አካላት በሙሉ ከንግድ ተቋም ጋር የውል ስምምነት ይገባሉ። መንግስት በሚተምነው ዋጋ ለመሸጥ ፈቃደኛ የመሆን፣ ምርቶችን በጥራትና ደህንነቱ በተጠበቀ አኳኋን የህብረተሰቡን ጤና በማይጎዳ መልኩ ማቅረብ፣ ሸማቹ ህብረተሰብ ለሚከፍለው ዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ምርት የመስጠት (ሚዛን አለመቀሸብ) የሚሉና ሌሎች በርካታ ህጎችን ያካተተ የውል ስምምነት እንደሚፈጽሙ አስረድተዋል፡፡

ዳይሬክተሩ በማብራሪያቸው፣ “የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በየሳምንቱ አርብ አርብ አጠቃላይ የከተማዋን የንግድ ሁኔታ በመመልከትና የዋጋ ጥናት በማድረግ የቅዳሜ እና እሁድ ገበያ መሸጫ ዋጋ ተመን ያወጣል፡፡ የወጣው ተመን ለሁሉም ወረዳዎች ባለን የማህበራዊ ሚድያ ግንኙነት አማካኝነት እንዲደርሳቸው ተደርጎ በእያንዳንዱ አቅራቢ ድንኳን ላይ ዋጋው እንዲለጠፍ ይደረጋል፡፡ በተለጠፈው ዋጋ መሸጥ የአቅራቢው ግዴታ ነው፡፡” ብለዋል፡፡ አሁን ላይ ችግር የሆነውን ነገር ሲገልጹም፣ “መንግስት ዋጋ ተምኖ ይለጥፋል፡፡ ነገር ግን ሸማቹ ማህበረሰብ ዋጋ ስንት ነው? ብሎ የመጠየቅ አዝማሚያ በስፋት አለ፡፡ ይህ ደግሞ ሻጩ ዋጋ ጨምሮ እንዲናገር እድል ይፈጥራል። መንግስት ህግን ለማስከበር በሚሰራው ልክ ማህበረሰቡም ማገዝ አለበት፡፡ ዋጋ ከመጠየቅ ይልቅ የተፃፈውን አይቶ መክፈል ቢችል የተሻለ ነው” ሲሉ አስረድተዋል፡፡

እንደ የንግድ የግብይት ማስፋፊያ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ እስከ ወረዳ ድረስ ባለው መዋቅር የተጠናከረ የስራ ክንውን እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ባለሙያዎችም በተጠናከረ አግባብ ክፍተቶች እንዳይፈጠሩ፣ ህገ ወጥነትም እንዳይፈፀም እየተሰራ ይገኛል፡፡ ህግ ተላልፈው በተገኙ የምርት አቅራቢዎች ላይ ደረጃ በደረጃ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ እንደ ጥፋቱ ሁኔታ የቃል ማስጠንቀቂያ፣ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ከትስስር እንዲወጡ በማድረግ በተመደቡበት ቦታ ምርት እንዳያቀርቡ የሚደረግበት አግባብ አለ፡፡

ከእርምጃ በፊት ህብረተሰቡም፣ ምርት አቅራቢውም ስለተቀመጡ ህጎች ጠንቅቆ እንዲያውቅ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በመጠቀም ተገቢውን እውቀት እንዲያገኙ የማስቻል ስራ መሰራቱንም አክለዋል፡፡

በያዝነው 2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ውስጥ ወደ 26 የሚደርሱ በተለያዩ ጥፋቶች ላይ የተገኙ አቅራቢዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል። ሚዛን የቀሸቡ፣ ከተለጠፈው የዋጋ ዝርዝር ውጪ ሲሸጡ የተገኙ፣ የምርት ጥራት ጉድለት ያለባቸውን አካላት እንደየ እርከኑ ተጠያቂ የማድረጉ ስራ ተሰርቷል። በዚህም መሰረት 15 ምርት አቅራቢ ነጋዴዎች ላይ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 6ቱ ላይ የቃል ማስጠንቀቂያ እንዲሁም 5ቱ ላይ ከትስስር እንዲወጡ በማድረግ በተመደቡበት ቦታ ምርት እንዳያቀርቡ የተደረገበትን አግባብ አስረድተዋል፡፡

ኢኮኖሚ

# በልኩ ያልተጠቀምንበት ሀብት

- በመዲናዋ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ 60 በመቶው ለኮምፖስት መዋል የሚችል መሆኑ ተጠቁሟል
- እንደከተማ ለኮምፖስት መዋል ከሚችለው ቆሻሻ ውስጥ ወደ 0 ነጥብ 9 በመቶ የሚሆነው ብቻ ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሚገኝ ተመላክቷል




ግራፊክስ፡- በዳንኤል ተስፋይ

ቆሻሻን በየመልኩ በማደራጀት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የማድረጉ ተግባር ከሁሉም ይጠበቃል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ወጣት ብሩክ ፀሐይ በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን እየተከታተለ እያለ ነበር ወደፊት የሚሰማራበትን ስራ ማለም የጀመረው፡፡ በባዮቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፍ ሲማር ቆሻሻን በማከም መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል የተረዳውን ሀሳብ ወደ አዲስ አበባ ከተማ በማምጣት ወደ ተግባር ለመቀየር ተነሳ። ከዩኒቨርሲቲ ሲመረቅም በሚሰማራበት ስራ ዙሪያ መጠየቅ ሀሳብ (ፕሮፖዛል) አዘጋጅቶ ነበር የወጣው፡፡

ወጣት ብሩክ በ2011 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪውን ካገኘ በኋላ በቀጣዩ ዓመት ህልሙን እውን ለማድረግ በሰላም ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ በመግባት በከተማ ግብርና ዘርፍ ስልጠና ወሰዷል፡፡ በዚያ አጋጣሚም ተደራጅተው አብረውት የሚሰሩ ጓደኞችን አገኘ፡፡ በ2013 ዓ.ም አስር አባላትን በማቀፍ ደረቅ ቆሻሻን በመጠቀም የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) ለማምረት ተደራጅተው ወደ ስራ እንደገቡ አብራርቷል፡፡

የብሩክ፣ ሰላማዊትና ጓደኞቻቸው ኮምፖስት ማምረት ሽርክና ማህበር መስራችና ስራ አስኪያጅ ወጣት ብሩክ እንደሚናገረው፣ ማዳበሪያ ለሀገራችን ኢኮኖሚ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን በመረዳት የተፈጥሮ ማዳበሪያ በማምረት ራሳቸውን ለመለወጥና ለሀገር እድገትም የበኩላቸውን ድርሻ ለመወጣት በኮምፖስት ዘርፍ ተሰማርተዋል። ስራውን ሲጀምሩም ከስኬት ባንክ (የቀድሞ አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም) 30 ሺህ ብር ብድር ወስደዋል፤ ከሚኖሩበት ከየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር የስራና ክህሎት ጽህፈት ቤት 500 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው የመስሪያ ቦታ አግኝተዋል፡፡

ይሁን እንጂ ስራው አዲስ ከመሆኑ አኳያ ወደ ገበያ ለመግባት የተለያዩ ፈተናዎችን ማለፍ ግድ ብሏቸዋል፡፡ የማህበሩ አባል እና ኦዲተር ወጣት በቀለ ረጋና እንደሚናገረው፣ ስራውን ከጀመሩ በኋላ ለወራት ያለምንም ደመወዝና ገቢ ግብአት ለማሰባሰብ በእግራቸው ረጅም ርቀት ይጓዙ ነበር፡፡ ሆኖም ነገን ተስፋ በማድረግ ጠንክረው በመስራታቸው ምርቱን በጥራትና በስፋት በማምረት ውጤታማ መሆን ችለዋል፡፡

እነብሩክ ኮምፖስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) ለማምረት የተለያዩ ሂደቶችን ይከተላሉ፡፡ ግብአት ከመሰብሰብ ጀምሮ የተሰበሰበውን የመቀላቀል፣ ወደ ሼድ በማስገባት አየር እንዲያገኝ የማድረግ እንዲሁም ጠፈፍ ያለውን በወንፊት በማጥራት ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ወጣት ብሩክ እንደገለፀው፣ ለኮምፖስት ምርት የሚሆነውን ግብአት በዋናነት የሚያገኙት ከገበያ ማዕከላት ነው፡፡ የካራ የቁም እንስሳት የገበያ ማዕከል፣ ኩዊንስ ሱፐር ማርኬት፣ የአትክልት የገበያ ማዕከሎች፣ ጭማቂ ቤቶች፣ የከብትና ዶሮ እርባታ ላይ ከተሰማሩ በግዥና በነፃ ያገኛሉ፡፡ የምግብ ተረፈ ምርቶች፣ የሙዝ ልጣጭ፣ ጥቅል ጎመን፣ ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ ሰጋቱራና የተለያዩ መበስበስ የሚችሉ ምርቶች ለኮምፖስት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

"ቆሻሻ ቆሻሻ እንጂ የሀብት ምንጭ ተደርጎ አይወሰድም ነበር" የሚለው የማህበሩ አባል ወጣት በቀለ፣ ዘርፉ ትልቅ አቅምና ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያለው መሆኑን በመረዳት የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸው ምርታቸውን በስፋት እያቀረቡ እንደሚገኝ ይናገራል፡፡ አንድ ኪሎ ኮምፖስት ለተጠቃሚዎች በ4 ብር ሲያቀርቡ መንግስት የሶስት ብር ድጎማ በማድረግ 7 ብር ያገኛሉ፡፡ በኩንታል ደግሞ 700 ብር ያቀርባሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ 400 ኩንታል የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) የማምረት አቅም ላይ ደርሰዋል፡፡

የምርቱ ተጠቃሚዎችም በዋናነት በአረንጓዴ ልማት፣ ችግኝ በማፍላት፣ የመንገድ አካፋዮችን ዕፅዋት በመንከባከብ የሚሰሩ ማህበራት፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ፓርኮች እንዲሁም የግል ተቋማት ናቸው፡፡ ከእነብሩክ ኮምፖስት ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል በመንገድ አካፋይ የተተከሉ ዕፅዋትን በመንከባከብ እየተሳተፉ የሚገኙት ጀማል፣ ፀሐይነሽና ጓደኞቻቸው የአረንጓዴ ልማት ማህበር አንዱ ነው፡፡

የማህበሩ ስራ አስኪያጅ አቶ ጀማል በየነ እንደሚናገሩት በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 የሚገኝ 4 ሺህ 800 ስኩዌር ካሬ ሜትር የሚሸፍን ቦታ ላይ የሚገኙ ዕፅዋትን እየተንከባከቡ የሚገኙ ሲሆን፤ ለዕፅዋት የሚያስፈልገውን ማዳበሪያም እነብሩክ ከሚያዘጋጁት ማዳበሪያ በዓመት አራት ጊዜ እየገዙ ይጠቀማሉ፡፡ በአንድ ጊዜ 72 ኩንታል ማዳበሪያ የሚገዙ ሲሆን ማዳበሪያው ዕፅዋት ፋፍተው እንዲያድጉ እያስቻለ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት የብሩክ፣ ሰላማዊትና ጓደኞቻቸው ኮምፖስት ማምረት ሽርክና ማህበር ካፒታል ከ1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በላይ ደርሷል፡፡ በተጨማሪም የራሱ የሆነ መስሪያ ቦታና መፍጫ ማሽኖች አሉት። የማህበሩ አባላት ከራሳቸው ባለፈ ለአራት ወገኖች በቋሚነት እና ለአምስቱ ደግሞ በጊዜያዊነት የስራ ዕድል መፍጠር እንደቻሉ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ወጣት ብሩክ ተናግሯል፡፡

አዲስ አበባ በ2013 ዓ.ም የበካይ ጋዝን በሚያስቀር ዘመናዊ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት በመዘርጋት በC40 የከንቲባዎች ፎረም ዓለም አቀፍ ውድድር ላይ አሸናፊ መሆኗ ይታወቃል፡፡ ከተማዋን ለእውቅና ያበቃትም ለበካይነት የተጋለጠ የነበረውን የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት በማስቀረት ደረቅ ቆሻሻ በመልሶ መጠቀም ለአረንጓዴ ልማትና የጓሮ አትክልት ልማት ስራ የሚውልበትን ስርዓት በመዘርጋቷ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ደረቅ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀምና ለኮምፖስት በማዋል የተሻለ እንቅስቃሴ እያሳየ ያለውን የእነብሩክ ማህበር የስራ እንቅስቃሴ በአካል መጥተው እንደጎበኙና እንዳበረታቷቸውም ወጣት በቀለ ያነሳል።

እነብሩክ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ከ50 በላይ ለሚሆኑ ወገኖች የስራ ዕድል የመፍጠር ዕቅድ አላቸው፡፡ በረጅም ጊዜ ደግሞ በአፍሪካ ትልቁ የተፈጥሮ ማዳበሪያ አምራች ኩባንያ የመሆን ርዕይም አላቸው፡፡

ደረቅ ቆሻሻን በስፋት ወደ ሀብት ወይም ኮምፖስት ምርት ለመቀየር የመንግስትና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ወጣት ብሩክ ያነሳል፡፡ የፋይናንስ፣ የማምረቻ ቦታ፣ ማሽን ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡ ስራው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን፣ የተማረ የሰው ሀይል በዘርፉ እንዲሰማራ፣ የገበያ ትስስሩም ከከተማ ባሻገር ገጠር ድረስ አርሶ አደሮች ላይ መድረስ የሚችልበት ዕድል እንዲፈጠር ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች በምርምር ጥራትን ለማሳደግ የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችን በማምጣት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ችግር ፈቺ ማሽኖችን በመፈብረክ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መንግስት አሁን እያደረገ ያለውን ድጋፍ የበለጠ ቢያጠናክር ዘርፉ ውጤታማ መሆን ይችላል፡፡

## እንደ ከተማ ምን እየተሰራ ነው?

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የመልሶ መጠቀምና ዑደት ማድረግ ቡድን መሪ አቶ በላይ አለማየሁ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፤ ተቋሙ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው ስራዎች መካከል ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሀብት መቀየር አንዱ ነው። በዚህ ረገድም ቁርጥራጭ ብረታ ብረት፣ ወረቀት፣ ካርቶን፣ የውሃ መያዥያ ፕላስቲኮችና የመሳሰሉ የቆሻሻ ዓይነቶች ለመልሶ መጠቀም እየዋሉ ይገኛሉ። እነዚህም በከተማዋ ከሚመነጨው ቆሻሻ 18 በመቶ አካባቢ ድርሻ አላቸው። 60 በመቶ የሚሆነው ደረቅ ቆሻሻ የሚበሰብስና ለተፈጥሮ ማዳበሪያ ምርት (ኮምፖስት) መዋል የሚችል ሲሆን፤ ቀሪው ደግሞ አደገኛና ልዩ ልዩ ቆሻሻዎች ናቸው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አንድ ሰው በነፍስ ወከፍ በቀን 0 ነጥብ 45 ኪሎ ግራም ቆሻሻ ያመነጫል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በከተማ ደረጃም በቀን ከ3 ሺህ ቶን በላይ ደረቅ ቆሻሻ እንደሚመነጭ ይገመታል፡፡ የሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት በመቀየር ስራ ላይ 55 ማህበራት ተደራጅተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት እንደከተማ ለኮምፖስት መዋል ከሚችለው ቆሻሻ ውስጥ ወደ ዜሮ ነጥብ 9 በመቶ የሚሆነው ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት ከደረቅ ቆሻሻ 5 ሺህ ቶን ኮምፖስት በማህበራት አማካይነት በማምረት ለገበያ ለማቅረብ ዕቅድ ተይዞ፤ 5 ሺህ 460 ቶን በማምረት ማቅረብ ተችሏል፡፡ ከተመረተው ኮምፖስት በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ከ38 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ አግኝተዋል፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የመዲናዋ የኪነ ጥበብ ማእድ

በጊዜው አማረ

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ። ከተሰናዱ ዋና ዋና ዝግጅቶች መካከል የንባብ አውደ ርእይ፣ የህጻናት ፌስቲቫል፣ የሥዕል አውደ ርዕይ ተጠቃሾች ናቸው። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የተወሰኑትን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## መጽሐፍት

በዛሬው እለት ከደራሲ ሮማን ተወልደብርሃን ጋር የመወያየትና መጽሐፍት የማስፈረም መርሃ ግብር ይካሄዳል፡፡ ሮማን ከሰሞኑ "ዮዲታ" የተሰኘ የግለታሪክ መጽሐፍ ለንባብ ማብቃቷ ይታወሳል፡፡ መርሃ ግብሩ ከ8:00 ሰዓት እስከ 10:00 ሰዓት ለገሃር ተወልደ ህንፃ በሚገኘው ጃዕፈር መጽሐፍት ቤት እንደሆነ ተነግሯል። ደራሲዋ ከዚህ ቀደም "Reflections" በሚል ርዕስ የመጀመሪያ የግጥም ስራዋን ለህትመት አብቅታለች፡፡ ባለፈው ዓመት ደግሞ ደና'ደን በሚል ርዕስ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ያተኮረ መጽሐፏን ለልጆች አሳትማለች።

በሌላ የመጽሐፍት መረጃ የኢትዮጵያን የዘመናት ጥያቄን የመለሰውን "መሬት ላራሹ" አዋጅ ከማጥናት እስከ ህግ ማውጣት ተሳትፎ በነበራቸው ፕሮፌሰር ዓለምአንተ ገብረሥላሴ የተፃፈው "ትውስታዎቼ ስለመሬት ይዞታና የተለያዩ ፓለቲካዊና አገራዊ ጉዳዮች" የተሰኘው አዲስ መፅሐፍ ከሰሞኑ ለንባብ በቅቷል። መጽሐፉ በአሜሪካን ሐገር የታተመ ሲሆን ለኢትዮጵያውያን አንባቢያን ደግሞ በዚህ ሳምንት ታትሞ ለንባብ በቅቷል:: መፅሐፉ ስምንት ምዕራፎች እና 268 ገጾች አሉት፡፡

## የኪነ ጥበብ አውደ ርዕይ

በአዲስ አበባ የተለያዩ ቦታዎች ሲካሄድ የቆየው "አዲስ ሊትሬቸር ፌስቲቫል" የተሰኘ የንባብና ኪነ ጥበብ አውደ ርእይ በነገው እለት ይጠናቀቃል፡፡ በመርሃ ግብሩ ላይ የኪነ ጥበብ፣ የውይይት፣ የመጻሐፍ አውደ ርእይ እና ሌሎችም ፕሮግራሞች እየተካሄዱ ነው፡፡ ዛሬ እና ነገም የንባብ ውይይት፣ የመጽሐፍ ሽያጭ፣ ከደራሲዎች ጋር የመገናኘትና መጽሐፍ የማስፈረም መርሃ ግብር ተሰናድቷል፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን 75 ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ "Ignite Your Love For Words!" በሚል መሪ ሀሳብ ያዘጋጀው አዲስ ሊትሬቸር ፌስቲቫል ከህዳር 23 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ስፍራዎች ሲዘጋጅ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

## የስዕል አውደ ርዕይ

"የራስ መንገድ" የተሰኘ የስእል አውደ ርእይ በእይታ ላይ ይገኛል፡፡ በዮሴፍ ሰቦቅሳ (ሰናይት) የቀረበው ይህ አውደ ርዕይ ታህሳስ 1 ቀን 2018 ዓ.ም በይፋ የተከፈተ ሲሆን እስከ ታህሳስ 27 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ በእይታ ላይ ይቆያል። አውደ ርዕዩ መስቀል አደባባይ አጠገብ በሚገኘው በሃያት ሬጀንሲ ሆቴል ውስጥ ባለው በፈንድቃ የባህል ማዕከል ውስጥ እየታየ ይገኛል፡፡

## ሙዚቃ

የአንጋፋው ሙዚቀኛ አረጋኸኝ ወራሽ ሙዚቃ በቅርቡ እንደሚለቀቅ ተገለጸ። "የዘመን እንቆቅልሽ" በተሰኘው አዲስ ነጠላ ሙዚቃ በግጥም መሰለ ጌታሁን፣ በዜማ እና ቅንብር ደግሞ አማኑኤል ይልማ ተሳትፈውበታል።

በሌላ መረጃ የለምለም ሃይለሚካኤል የመድረክ ስራዎች ለአድማጭ ተመልካች ሊደርሱ ነው፡፡ የድምጻዊቷ የተመረጡ 5 የመድረክ ስራዎች በናሆም ሪከርድ አማካኝነት ለህዝብ እንደሚደርሱ ተገልጿል፡፡

## ቴአትር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቅዳሜ ሁለት ቴአትሮች ለእይታ ይበቃሉ፡፡ ቀን 8፡30 ሰዓት ላይ 12ቱ እንግዶች እንዲሁም 11፡30 ሰዓት ባሎችና ሚስቶች ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8፡30 ሰዓት ንጉሥ አርማህ እንዲሁም በ11፡30 ሰዓት እምዩ ብረቷ፣ ማክሰኞች 11፡30 ሰዓት ሶስቱ አይጦች፣ ረቡዕ በ11፡30 የቅርብ ሩቅ፣ ሃሙስ በ11፡30 ሰዓት ሽምጋይ እንዲሁም አርብ በተመሳሳይ ሰዓት ዴጊያ የተሰኙ ቴአትሮች በዚሁ ቴአትር ቤት ለእይታ ይቀርባሉ፡፡ በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ደግሞ እሁድ በአሉ ግርማ (ቤርሙዳ) ቴአትር ለተመልካች ይቀርባል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው 9-6=3 እንዲሁም 7+7=14 ይሆናል፡፡ እዲሁም 14 x3=42 ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት ሶስተኛውና የመጨረሻው 8-2=6 እንዲሁም 3+2=5 ይሆናል፡፡ ውጤቱ ደግሞ 6x5=30 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **30** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል። በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የባለቅኔው የምጥቀት አክናፍ

በአብርሃም ገብሬ

በባለቅኔ ጸጋዬ ገብረ መድህን ህይወትና ሥራዎች ዙርያ ከተጻፉ መጽሐፍት መካከል 'ምጥቀት በቅኔ አክናፍ' የተሰኘው መጽሐፍ በእጅጉ ይለያል። የመጽሐፉ ደራሲ ፋሲል ይትባረክ ውብ በሆነ አተራረክና የቋንቋ አጠቃቀም ከሽኖ ያቀረበው መጽሐፍ መሆኑ፤ የሎሬቱ የፈጠራ ሥራዎች ከህይወቱና ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር እያናበበ መተርጎሙ ብቻ አይደለም ለየት የሚያደርገው፡፡ በዋናነት የህይወት ታሪክ መጽሐፉ እንዲጻፍ የደራሲ ፋሲል መሻት ብቻም ሳይሆን የሎሬቱም መሻት ያለበት መሆኑ፣ ጸጋዬም ሳይሰስት ስለ አስተዳደጉና ህይወቱ የተረከበት መሆኑ መጽሐፉን ለየት ያደርገዋል፡፡

'ምጥቀት በቅኔ አክናፍ' የህይወት ታሪክ መጽሐፉ በራሱ በጸጋዬ ጠያቂነትና ፍላጎት የተጀመረ ነው፡፡ ጸጋዬ ከልጅነቱ አንስቶ እስከ 1966ቱ አብዮት ድረስ ስለነበረው ልጅነቱ፣ ስለአስተዳደጉ፣ ስለትውልድ ስፍራው፣ ስለቤተሰቦቹ፣ ስለ ትምህርት ቤት ህይወቱ፣ ስለ ከያኒነቱ፣ ስለ ትዳር ህይወቱ... በራሱ አንደበት፣ ራሱ ባለበት ሪከርድ ተደርጎ በኋላም በመጽሐፍ መልክ የተሰናዳ ድንቅ መጽሐፍ ነው፡፡

እዚህ'ጋ ግን መጽሐፉን አንብበን ስንጨርስ በአንድ ነገር ማዘናችን አይቀርም፤ ጸጋዬ በወርሃ የካቲት 1998 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ በተለይ በአብዮቱ ሰሞን፣ ከአብዮቱ በኋላ ያሉ የህይወትና የጥበብ ስራዎቹ ሁናቴ በራሱ አንደበት ተተርኮ ለማንበብ አልታደልንም፡፡ ደራሲው ፋሲል በየሳምንቱ ኒውዮርክ በሚገኘው የጸጋዬ ቤት ሪከርደሩን ይዞ እየጠየቀ በነበረበት ሂደት ነው ሥራው ሳይቋጭ ጸጋዬ ህይወቱ ያለፈው፡፡ በዚህ ምክንያት ጸጋዬ ከአብዮቱ በኋላ ስለነበረው ሁናቴ ከአንደበቱ ለመስማት አለመታደላችን ትንሽ ቁጭት ነገር ይፈጥራል፡፡ ይሄም ሆኖ ግን ደራሲው ይህን ክፍተት ለመሙላት ያደረገው ጥረት የሚደነቅ ነው፡፡

ገና በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ፀጋዬ ለልጆቹ ምን አይነት አባት እንደነበር በልጆቹ አንደበት ይነገረናል፡፡ በጣም ደስ በሚያሰኝ ሁናቴ ጸጋዬ በልጆቹ አንደበት ስለ አባትነቱ፣ እነዚያን አስደናቂ ቅኔዎች በምን አይነት ሁኔታ ላይ ሆኖ ይጽፍ እንደነበር፣ በአደባባይ የሚታወቀው ጸጋዬ ቤት ውስጥ ምን አይነት አባት እንደሆነ ከልጆቹ አንደበት እናነባለን፡፡

እዚህ'ጋ ማስታወስ የሚያስፈልገው አንድ ጉዳይ 'ምጥቀት በቅኔ አክናፍ' ትርጉም ስራ መሆኑ ነው፡፡ ደራሲ ፋሲል ይትባረክ ጸጋዬ ባረፈ ማግስት 'Soaring on Winged Verse' በሚል ርዕስ የጸጋዬን የህይወት ታሪክ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጽፎ እዚያው አሜሪካ ሀገር አሳትሞ ለንባብ እንዲበቃ አድርጓል፡፡ ነገር ግን መጽሐፉ ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈልጎ የሚገኝ መጽሐፍ አልነበረም፡፡ ታዲያ ከሁለት አስርት ዓመታት በኋላ በራሱ በደራሲው ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለንባብ መብቃቱ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ትልቅ አበርክቶ ነው፡፡




ፎቶ-ከገፀ ድር

የሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህንን የህይወት ታሪክ የሚዳስሰው መፅሐፍ

## ታምረኛዋ ጎሮምቲ

ከአምቦ በስተምዕራብ ሃያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ቦዳ በምትባለው መንደር ውስጥ ነው ጸጋዬ የተወለደው። የተወለደበት ሰሞን (የካቲት 11 ቀን 1928 ዓ.ም) ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ከባድ ጦርነት የሚካሄድበት ወቅት ነበር፡፡ ፋሺስት ጣሊያን ኢትዮጵያን ወርሮ ኢትዮጵያውያንን በግፍ እያሳደደ የሚገድልበት አስጨናቂ ጊዜ ነበር፡፡ የእነጸጋዬ መንደር ቦዳ በተለይ በባንዳዎች ዝርፊያና ጥፋት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቂ ሆነች፡፡ ጥቃቱ ወደ ጨቅላው ጸጋዬ ቤትም ደረሰ፡፡ ባንዳዎች የእነ ጸጋዬን ቤት ከመዝረፍ የተሻገረ ጥቃት ፈጸሙ። የእነ ጸጋዬን ቤት ከዘረፉ በኋላ እሳት ለቀቁበት፡፡ ወይዘሮ ፈለቀችም የጨቅላው ልጃቸውን ህይወት ለማትረፍ እየተጣደፉ ቤታቸው ዶግ አመድ ሲሆን በቁጭት ተመለከቱ፡፡

የቤቱ አባወራ አቶ ገብረ መድህን ደግሞ በዚህ ጊዜ ከከሃዲ ባንዳዎች መሳሪያ በመግዛት በድብቅ ለአርበኞች የማስተላለፍ ሥራ ይሰሩ ነበር። ከቤታቸው ርቀው በመሄድ ነበር ይሄን ተግባር የሚከውኑት፡፡ ጨቅላው ልጃቸውና ሚስታቸውን ትተው የሄዱት አቶ ገብረ መድህን ቦዳ ውስጥ ምን እየተከሰተ እንዳለ አያውቁም። ነገር ግን ርቀው ከመሄዳቸው በፊት ለሚስታቸው ለወይዘሮ ፈለቀች የፋሺስት ወታደሮችና ባንዳዎች ቦዳ ድረስ ከዘለቁ፣ ጠላት ለመግባት ወደ ማይደፍራት ወደ ገጠራማዋ ጎሮምቲ እንድያመሩ አስቀድመው አስጠንቅቀዋቸዋል፡፡ ጎሮምቲ የአቶ ገብረ መድህን ወንድሞች የሚኖሩባት የገጠር መንደር ነች፡፡ ወይዘሮ ፈለቀችም ጨቅላው ልጃቸውን አዝለው ወደ ገጠራማዋ ጎሮምቲ ተሰደዱ፡፡

ጸጋዬ ቦዳ ቢወለድም ልጅነቱና የልጅነት ትውስታው ሁሉ ከጎሮምቲ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ጎሮምቲን እንደ "የምድር ገነት" አድርጎ ይመለከታታል፡፡ አስደናቂ መልክዓ ምድርና ተፈጥሮ የታደለች ሥፍራ ነች፡፡ ጸጋዬም የጎሮምቲን አፈር ፈጭቶ፣ ጭካ አቡክቶ አድጓል፡፡ የጎሮምቲ እረኞችን እየተከተለ ተጫውቷል፡፡ ከሾላ ዛፍ ላይ እየተንጠለጠለ በጣፋጩ የሾላ ፍሬ ሆዱን ሞልቷል፡፡ ሕጻኑ ፀጋዬ "የምድር ገነት" ብሎ በሚጠራት ጎሮምቲ ውስጥ ልጅነቱን አሳልፏል፡፡

በዚህ መሃል ግን አንድ ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ፡፡ ክስተቱ ህጻኑ ጸጋዬ ብዙም አልወደደውም፡፡ የምድር ገነት ከምትባለው ጎሮምቲ ህይወቱን የምትነጥለው መስሎ ስለተሰማው አጋጣሚው አልተመቸውም፡፡ ከወደ መንዝ የመጡ ሦስት ሰዎች በድንገት የጎሮምቲን ህይወቱን እንደነጠቁት ተሰምቶታል፡፡ እነዚህ ከመንዝ የመጡት ሶስቱ ሰዎች ከፋሽስት ጣሊያን ወታደሮች ግድያ አምልጠው ከመንዝ ወደ ጎሮምቲ የመጡ ናቸው፡፡ ሶስቱ ሰዎች የሚያገለግሉባት የነበረችው አንኮበር ከተማም በጣሊያን ወታደሮች መቃጠሉን ተከትሎ ነው የጸጋዬ የትውልድ መንደር የዘለቁት፡፡

እነ ጸጋዬ ቤት የመጡት ሶስቱ እንግዳ ሰዎች የእናቱ የወይዘሮ ፈለቀች ዘመዶች ናቸው፡፡ አንኮበር ላይ የታወቁ ካህናትና ሊቅ ናቸው፡፡ ወይዘሮ ፈለቀችም ዘመዶቻቸውን በቻሉት ሁሉ ተንከባክበው ያዙዋቸው፡፡ እንግዶቹም ፈለቀችን ለማስደሰት አንድ ውለታ ለመዋል አሰቡ፡፡ በአስጨናቂ ጊዜ የወለዱት ተወዳጁ ልጃቸው ጸጋዬን የግዕዝ ቋንቋና ቅኔን ለማስተማር ወሰኑ። ሕጻኑ ጸጋዬም በታምረኛዋ ጎሮምቲ መንደር ውስጥ በአባቱ ዘመዶች በኩል የኦሮሞን ባህልና እሴቶች በእናቱ ዘመዶች በኩል ደግሞ የግዕዝ ቋንቋና ቅኔን መማሩን ቀጠለ፡፡ ይሄም ሆኖ ግን ህጻኑ ጸጋዬ ከሚወደው ጨዋታ መነጠሉ በጣም አናድዶታል፡፡ ትንሹ ጸጋዬም ገና ትምህርት ቤት ደጃፍ ሳይረግጥ በጎሮምቲ ቤቱ ውስጥ በግዕዝ ቋንቋ መንፈሳዊ ምንባቦችን በቃሉ ከማነብነብ የተሻገረ ዕውቀት ገበየ፡፡ ከኦሮምኛ ቋንቋ ውጭ በማይነገርባት ጎሮምቲ ውስጥ አማርኛና ግዕዝ ገና ትምህርት ቤት ደጃፍ ሳይረግጥ በህጻን ዕድሜው ለማወቅ ቻለ፡፡

## የጎሮምቲው ትንሹ ልጅና ጃንሆይ የተገናኙ ዕለት

ጸጋዬ ኋላ ላይ ከትውልድ መንደሩ ርቆ አምቦ አስኳላ ትምህርት ቤት ሲገባም በልጅነቱ የተማረው የግዕዝ ቋንቋና ቅኔ በድርሰት የትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ ጎልቶ መታየት ጀመረ፡፡ በተለይ የሚጽፋቸው ግጥሞች ከእድሜው እጅግ የተሻገሩ በመሆናቸው በመምህራኑ ሳይቀር የሚደነቅ ልጅ ሆነ፡፡ ከሥነ ጽሑፍ ባሻገር በተውኔት አዘጋጅነትና ተዋናይነት ጭምር ትንሹ ጸጋዬን የሚተካከል ሌላ ተማሪ አልነበረም፡፡

ይሄ የተዋናይነትና አዘጋጅነት ጥልቅ መሻቱ ግን አንድ አስገራሚ ክስተት ይዞ መጣ፡፡ አምቦን አዘውትረው የሚጎበኙት ንጉሰ ነገሥት አጼ ኃይለ ሥላሴ ወደ ከተማዋ የመጡበት ሰሞን ነው ክስተቱ የተፈጠረው፡፡ ንጉሱ ጸጋዬ የሚማርበት የአምቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሊጎበኙ እንደሆነ አስቀድሞ ተሰማ። የ13 ዓመቱ ጸጋዬም አንድ ነገር አሰበ። "ሪደር ሲክስ" የተባለው የእንግሊዘኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚያውቀው "ኪንግ ዲዮናስየስ ኤንድ ሂዝ ቱ ብራዘር" የተሰኘ ቴአትር ለዚያን ሰዓት በሚያመች መንገድ አድርጎ ለማቅረብ አሰበ፡፡ ከዚያ በፊት ተውኔት ጽፎም ሆነ መድረክ ላይ ተውኖ የማያውቀው ጸጋዬ በተውኔቱ ላይ የሚተውኑ ጓደኞቹን መረጠ። አንዱ የክፍል ጓደኛው ደሬሳ ነበር። ነገር ግን ጓደኞቹ የጸጋዬን ሃሳብ እንደ እብደት ቆጠሩት፡፡ ጸጋዬ ግን ተከራክሮ አሳመናቸውና አዳራቸውን ሲለማመዱ አድረው በማግስቱ በጃንሆይ ፊት ለማቅረብ ወሰኑ፡፡ ይሄ ሁሉ ዝግጅት ሲያደርጉ ግን ተውኔቱ መድረክ ላይ መቅረብ አለመቅረቡን የሚወስኑት የትምህርት ቤቱ መምህራንና ኃላፊዎች ስለ ተውኔቱ አንዳችም ነገር አያውቁም፡፡ ጸጋዬ ግን "እሱን እኔ አሳምናለሁ" በማለት ቁርጠኛ አቋም ያዘ፡፡

በማግስቱ ጠዋት፤ የእንግሊዝኛ ትምህርት እንደተጀመረ "እኔና ጓደኞቼ ለጃንሆይ የሚቀርብ ቴአትር አዘጋጅተናል" ሲል ጸጋዬ ለመምህሩ ለሚስስ ኸቺንግስ አስታወቀ፡፡

"የምን ቴአትር ነው ጸጋዬ?" ስትል ጠየቀችው፡፡

"ንጉስ ዲያኖስየስና ሁለቱ ወንድማማቾች"

ሚስስ ኸቺንግስ ጉዳዩ ብዙም አላጓጓትም፡፡ እምቢ ያለች ባትመስልም በዘዴ ጥያቄያቸው ችላ ለማለት ወስናለች። ጸጋዬ እሷን ለማሳመን ከቴአትሩ ለቅምሻ የሚሆን ነገር ለማሰማት እንደሚችሉ ነገራት፡፡ አስተማሪዋ በመፍቀድ ባለመፍቀድ መሃል እየዋለለች፣ ጸጋዬ ጓደኞቹን በጥቅሻ እንዲነሱ አዘዛቸው። ሶስቱም ተነስተው አዳር ካጠኑት ተውኔት ውስጥ ቀንጭበው ክፍል ውስጥ በመነባንብ መልክ ማቅረብ ጀመሩ፡፡ የክፍል ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ችሎታ ተደምመው በተመስጦ ይመለከታሉ፡፡ ሚስስ ኸቺንግስም እያየችው ባለው ነገር እጅግ ተገረመች፡፡

በልቧ 'ይሄ ቴአትርማ መቅረብ አለበት' ብላ ወሰነች፡፡ እነ ጸጋዬ ቴአትሩን እያቀረቡ ከፊት የተቀመጠውን ተማሪ በጀሮው የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር የሆነው ባሏን "በፍጥነት ና በለው" አለችው፡፡ ዳይሬክተሩ ሳይቆይ መጣና በሥጋት "ምን ሆነሻል?" በማለት አንድ ጊዜ የሚስቱን አንድ ጊዜ የእነ ጸጋዬን ቴአትር በግራ መጋባት ስሜት ውስጥ ሆኖ ይመለከት ጀመር፡፡

በመሃል "ጸጋዬና ጓደኞቹ አንድ አስገራሚ ነገር ይዘውልን መጥተዋል" አለችውና ጸጋዬ ትርዒቱን እንዲቀጥል ነገረችው፡፡ ዳይሬክተሩ መጀመሪያ በማመንታት፣ ዘግይቶ ግን በአድናቆት ቴአትሩን ተመለከተ፡፡ ባየው ነገር የተገረመው ዳይሬክተሩ ቴአትሩ በጃንሆይ ፊት እንዲቀርብ ሙሉ ፈቃድ ሰጠ፡፡

በማግስቱ ጃንሆይ ወደ ትምህርት ቤቱ የስብሰባ አዳራሽ ከመንግስት የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ባለስልጣናት ጋር በመሆን ከፊት ለፊት ቁጭ አሉ። አዳራሹ ትንሽ ጨለምለም ተደርጎ የትርኢቱ መጀመር ተበሰረ፡፡ ከዚያ በፊት ማንም የማያውቃቸው ሶስቱ ጓደኞች የተለማመዱትን ቴአትር ጢም ብሎ በሞላው አዳራሽ መድረክ ላይ ማቅረብ ጀመሩ፡፡ ተመልካቹም በትዕይንቱ መገረሙን አላቆመም። ጃንሆይና ሌሎች ባለስልጣናትም የወጣቶቹን ቴአትርና ትወና በመገረም ይመለከታሉ፡፡ ተመልካቹን ሰቅዞ የያዘው የእነ ጸጋዬ ቴአትር ካለቀ በኋላ አዳራሹ በፉጨትና በጭብጨባ ተደበላለቀ። ጃንሆይም በተመለከቱት ትርዒት ተደሰቱ፡፡ እርካታቸውን ለመግለጽ ያህል ጭንቅላታቸውን ላይና ታች ከነቀነቁ በኋላ ለዋና ተዋናዩ ለጸጋዬ ወገግ ያለ ፈገግታ አሳዩት፡፡ ከዚያ ጣታውቸውን በማንቀሳቀስ አንደኛው ጠባቂያቸውን ጠሩትና ጭንቅላቱን ዝቅ አድርጎ ሲቀርብ ንጉሰ ነገስቱ አንዳች ነገር በጆሮው ሹክ አሉትና ፈጥኖ ወደ መድረኩ መጣ። ፈርጣማው አንጋች ሰውዬ ወደ ትንሹ ጸጋዬ ቀርቦ፣ "ጃንሆይ ምን እንዲያደርጉህ ትሻለህ?" ሲል ጠየቀው፡፡

"ማ? እኔ?" ሲል መልሶ ጠየቀው ጸጋዬ።"አዎ አንተ! ጃንሆይ ምን እንዲያደርጉልህ ትፈልጋለህ?"

ወደ ገጽ 19 ዞሯል

# የአገልጋዩ አድራሽና መላሾች

- **477 አውቶቡሶች የፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ**
- **በመጪው 3 እና 4 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ቁጥራቸው 90 የሚሆኑ ተጨማሪ አውቶቡሶች ወደ አገልግሎቱ እንደሚገቡ ተጠቁሟል**

**በሄለን ጥላሁን**

አንድም ቀን ካለምንም በቂ ምክንያት ከስራ ገበታቸው ቀርተው አያውቁም፤ ወይዘሮ መብራት ነጋሽ፡፡ ወይዘሮዋ ቦሌ አራብሳ በተለምዶ ሰፈራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሳይት ሶስት ነዋሪ ናቸው፡፡ ሁልጊዜ ከእንቅልፋቸው ሌሊት 9፡00 ሰዓት ላይ ይነሳሉ፡፡ ለዚህ ምክንያታቸው ለቀን ውሏቸው አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ ነው፡፡ ታድያ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት ሰልፍ መያዣ ሰዓት ደረሰ አልደረሰ በማለት በጥድፊያ ከቤታቸው መውጣት የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ሆኗል፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
የመንግስት ሰራተኞች የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት ሲጠቀሙ


ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሪት ቤዛይት ተሾመ

መነሻውን ቦሌ አራብሳ ሰፈራ አድርጎ እስከ ፒያሳ የሚወስደውን የፐብሊክ ሰርቪስ አውቶቡስ ለመያዝ ቢያንስ ሰልፍ ቦታው ላይ 10፡20 ሰዓት መድረስ እንደሚጠበቅባቸው የሚናገሩት ወይዘሮ መብራት፤ ከቤት እስከ ሰርቪስ ቦታ ለመድረስ የሚጓዙት የእግር ጉዞ ጭንቅ ነው የሚሆንባቸው፡፡ "ጨለማው ለተለያዩ ችግሮች ያጋልጠን ይሆን" በሚል በስጋት ስሜት ውስጥ ሆነው ነው የሚጓዙት፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ "ሃይላንዶችን በቆሻሻ ማዳበሪያ እንለቅማለን" በሚል ዝርፊያ እና ድብደባ የሚያከናውኑ አካላት መኖራቸውን ተከትሎ ነው፡፡ ይህንን መሰል ለአደጋ ያጋለጠ ክስተት ከዕለታት በአንዱ ቀን በእርሳቸውና በጓደኛቸው ላይ ሊደርስ አንዣቦ እንደነበረ አስታውሰው፤ የድረሱልን ጥሪ በማሰማታቸው ሰዎች መጥተው እንዳዳኗቸው ገልፀዋል፡፡

የወይዘሮ መብራት ነጋሽ እና የጓደኛቸውን ስጋት በመረዳት የቤተሰብ አባላት ሌሊት ላይ ወደ አውቶብሱ መቆሚያ ድረስ እንደሚሸኟቸው የተናገሩ ሲሆን፤ እዚያ ከደረሱ በኋላ ሸኚዎች በሰላም ገቡ አልገቡ የሚለው በአንፃሩ ሌላ ስጋት እንደሚሆንባቸው ጭምር ገልፀዋል፡፡

ኮሎኔል ደምሴ ተሰማ ይባላሉ፡፡ ቦሌ አራብሳ (ሰፈራ) እስከ ፒያሳ የሚወስደውን የፐብሊክ ሰርቪስ አውቶብስ ትራንስፖርት ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ሰርቪሱን መጠቀም ከጀመሩ አንድ ዓመት አስቆጥረዋል፡፡ ሰፈራ አካባቢ ያለው የትራንስፖርት ችግር እንዲቀረፍ ፊርማ በማሰባሰብ ቅሬታዎችን ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ተወክለው በአካል ሄደው እንዳመለከቱ ያነሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ፤ ያስገቡት የቅሬታ ማመልከቻ መፍትሔ ማግኘት አልቻለም፡፡ የእነሱን መስመር ይዘው የሚጓዙ የፐብሊክ ሰርቪስ አውቶብሶች ከመነሻቸው ሞልተው እና በተሳፋሪ ተጨናንቀው ስለሚወጡ በየፌርማታው የሚገቡትን ለማስገባት ይቅርና ውስጥ ያለውን የተሳፋሪ ደህንነት የጠበቀ ጉዞ ለማድረግ አስቸጋሪ ስለመሆኑ ይናገራሉ፡፡

የችግሩን መጠን ኮሎኔል ደምሴ እንዳስረዱት፤ "ጠዋት ሰርቪስ ለመያዝ በሚል ሌሊት መነሳት፣ የመውጫ ሰዓት ላይ ቀድሞ ከሥራ ወጥቶ መሰለፍ፣ አልፎ አልፎ በተፈጠረው መተፋፈግ በቀላሉ እንደ ጉንፋን ላሉ በሽታዎች ተጋላጭ መሆን የተለመደ ነው" በማለት ነው፡፡ ይህንን መሰል የሠራተኛውን ችግር የሚመለከተው አካል በማየት መፍትሔ ቢሰጥበት መልካም እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሪት ቤዛይት ተሾመ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፤ ላለፉት 11 ዓመታት የመንግስት ሠራተኛውን በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ላይ አገልግሎት ሲሰጥ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ የመንግስት ሠራተኞች በአግባቡ በሥራ ገበታቸው ላይ እንዲገኙ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ሲሆን፤ ከወጪ አንፃርም በነፃ ለማጓጓዝ መቻሉ ትልቅ እፎይታን ስለመፍጠሩ አብራርተዋል፡፡

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተደራሽነቱን በማስፋት የትራንስፖርት ተጠቃሚውን እርካታ ከመጨመር ባሻገር የተጠቃሚውን ቁጥር ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በየጊዜው አገልግሎቱን ከማስፋት ባሻገር የልማት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ትርፋማ የሚያደርጉ የተለያዩ በርካታ ሥራዎችን ይሠራል፡፡ ታድያ በዋናነት ለተቋቋምንበት ዓላማ (የመንግስት ሠራተኛውን ጠዋትና ማታ ማጓጓዝ የሚለውን) ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ የተሻለ አቅም ለመፍጠር በጎን ደግሞ ሌሎች ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን እንደሚሠራ ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ አስረድተዋል፡፡

"ተደራሽነቱን ከማስፋት አንፃር አሁን ላይ 477 አውቶቢሶችን ለዚሁ ዓላማ እየተጠቀምን እንገኛለን፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ደግሞ የመንግስት ሠራተኛው የሥራ ቦታ በመቀየር ከመሀል ከተማ ወደ ማስፋፊያ ቦታ እየኖረ ይገኛል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በየጊዜው ተለዋዋጭ የሆኑትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት በየጊዜው መስመሮችን የመጨመር እንዲሁም የማራዘም ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡ ከዚህ ቀደም 50 የጉዞ መነሻዎች የነበሩ ሲሆን መዳረሻዎቻችንም ከ30 የማይበልጡ ነበሩ፡፡ በየጊዜው አውቶብሶቹ እየተጨመሩ 'የመንግስት ሰራተኛው የት ነው የሚኖረው?' የሚለውን ቦታ በመከታተል ስራችንን በስፋት ለመከወን ችለናል፡፡ በዚህ መሰረትም አሁን ላይ 113 የጉዞ መነሻዎች፤ 83 መዳረሻዎች አሉ" ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት በማስፋፊያ አካባቢዎች በተለይ ለጽሑፋችን እንደ መነሻ ቅሬታዎች በተነሱበት አካባቢ ያለውን የትራንስፖርት እጥረት በተመለከተ ወይዘሪት ቤዛይት ሲናገሩ፣ "ባሉት አራት ቅርንጫፎች በተለይ በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅ እንዲሁም በምዕራብ የሚገኙ መስሪያ ቤቶቻችን በየጊዜው ያሉ ችግሮች ምንድን ናቸው? ስንል ሪፖርቶችን እንቀባበላለን፡፡ ለመፍትሔውም አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በተለይ ከ2016 ዓ.ም በኋላ የትራንስፖርት ስምሪት አለመረጋጋት መፈጠር የጀመረበት ጊዜ ነው፡፡ ለዚህ የነዋሪዎች ቁጥር መጨመር እንዲሁም የተቋማት የስራ ቦታ መቀያየር ከምክንያቶቹ መካከል ናቸው" ሲሉ አንስተዋል፡፡

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ገለፃ፤ በምስራቅ ቅርንጫፍ ስር የሚገኘው ቦሌ አራብሳ በተለምዶ ሰፈራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የተጀመረው በአንድ አውቶቢስ ነበር፤ አሁን ላይ ቁጥሩ ጨምሮ አራት ደርሷል፡፡ ይህ ማለት ግን ከተደራሽነት አንፃር በቂ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ተደራሽነትን ከማስፋት አንፃር ጊዜያዊ መፍትሔ ለማበጀት ያክል ስምሪት የበዛባቸውና ያነሰባቸውን የአውቶቢስ ስምሪቶችን በማጤን አስፈላጊ ወደሆኑ ስፍራዎች የመመደብ አግባብ አለ፡፡ ቆጠራ በማድረግ መዳበል የሚችሉ መስመሮችን በማንሳት ችግሩ ወደባሰባቸው አካባቢ አውቶብሶችን የመመደብ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በየሦስት ወሩ ተጠቃሚዎቻችንን በምናዘጋጀው መድረክ ላይ የማግኘት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ችግሮች አሉ በሚሏቸው ቦታዎች ላይ ጥያቄያቸውን በማንሳት እዩልን ይላሉ፡፡ በቀን በቀንም የሱፐር ቪዥን ሰራተኞች ታች ድረስ በመውረድ ተጠቃሚዎችን ያነጋግራሉ፡፡

"ብዙ ተሳፋሪ የሌላቸውን መስመሮች እያየን እየቆጠርን ብዙ ስምሪት በሚበዛባቸው አካባቢዎች ላይ ደግሞ የአውቶብሶችን ቁጥር የመጨመር ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን፡፡ እነዚህን ሁሉ ስራዎች ስንሰራ የተገልጋዩን እርካታ ሙሉ ለሙሉ ለማሳካት ችለናል ብሎ ለማለት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ባለን ውስን ሃብት መሰረት አስፈላጊውን መፍትሔ ለመስጠት እየሰራን እንገኛለን" ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እንደ ወይዘሪት ቤዛይት ገለፃ፤ በዘላቂነት ችግሮችን ለመፍታት አውቶቡሶችን ገዝቶ ማምጣት ሁነኛ መፍትሔ መሆኑን በመረዳት ዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የማውጣት ስራ ተሰርቷል፡፡ ህጋዊ ሂደቱን አልፎ አሁን ላይ ከጨረታው አሸናፊ ጋር ከ2 ነጥብ 2 ቢሊየን ብር በላይ በማውጣት ግዢ ለመፈጸም ውል ገብተናል፡፡ ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠትም ከ3 እስከ 4 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ 90 አውቶቡሶች የሚገቡ ይሆናል፡፡ ይህ በትንሹም ቢሆን ያለውን መጨናነቅ ለመቅረፍ የሚቻልበት አግባብ ይፈጥራል፤ የተገልጋይን ቅሬታም ይፈታል፡፡ በቀጣይም የገቢ ምንጩን በማሳደግ ተጨማሪ አውቶቡሶችን በየዓመቱ የመግዛት እቅድ አለ፡፡ አሁን ካለውም በላይ የመንግስት ሰራተኛውን የሚመጥን ስራ ይሰራል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ስራውን በሚፈለገው ልክ ለመስራት እንዳይቻል እንቅፋት የሆኑትን ሲዘረዝሩ፣ "ለቁጥጥር ሲወጣ ህገ ወጥ መታወቂያዎችን የሚጠቀሙ ተሳፋሪዎች በብዛት ይገኛሉ፡፡ ለዚህም እንደ መፍትሔ የተወሰደው ከሸገርና ከአዲስ አበባ ፖሊስ ጋር በመሆን ድንገተኛ ፍተሻዎችን ማድረግ ነው፡፡ በቀን ውስጥ ከ50 እስከ 60 ህገ ወጥ መታወቂያዎች የያዙ ተሳፋሪዎች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ደግሞ ትክክለኛውን የመንግስት ሰራተኛ ተጠቃሚ ለማድረግ አስቸጋሪ ሆኗል፡፡

ለዚህም እንደመፍትሔ የተወሰደው የዲጂታል መታወቂያን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ የወረቀት መታወቂያን ማስቀረት ዋነኛ ዓላማችን በማድረግ ህገ ወጥነትን መከላከል ላይ ትኩረቱን ያደረገ ስራ መስራት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ቁጥራቸው ወደ 90 ሺህ የሚሆኑ የመንግስት ሰራተኞች መረጃዎቻቸው ተሞልቷል" ብለዋል፡፡ ቁጥራቸው 27 ሺህ የሚሆኑ የአዲስ አበባ እና ከ96 ሺህ በላይ የፌደራል ተቋማት ሰራተኞች የፐብሊክ ሰርቪስ ተጠቃሚ መሆናቸውን አክለዋል፡፡

# ልጆች እና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎቻቸው

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? ስፖርት የመስራት ልምዳችሁ ምን ይመስላል? ዛሬ ልጆች በስፖርት ማዘውተሪያዎች እንቅስቃሴ ማድረጋቸው የሚያስገኝላቸው ጥቅም ምንድን ነው? የወደፊት ህልማቸውን ለማሳካትስ ምን ያህል ያግዛቸዋል? ለዚህ ምቹ ሁኔታ አላችሁ ወይ? የሚሉት ጉዳዮች ላይ መረጃ እንለዋወጣለን፡፡ የእናንተን የልጆችን አስተያየትም አካትተናል፡፡ ያነጋገርናቸው ልጆች በተለምዶ "ኒኮላ ሜዳ" በሚባለው የስፖርት ማዘወተሪያ ሲጫወቱ ያገኘናቸውን ነው፡፡



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

ከግራ ወደ ቀኝ ናሆም ፍቅሩ፣ አልአዛር እንዳልካቸው፣ ፋሪስ ዘሪሁን እና ዮናታን ማሙሽ

ዮናታን ማሙሽ እባላለሁ። ኳስ ጨዋታ በጣም ያስደስተኛል፡፡ በሰፈራችን ከጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ። በፊት ሜዳው ያልተስተካከለ በመሆኑ ጠጠሩና ድንጋዩ እግሬን ይመታኝ ነበር። በመሆኑም መጫወት ብፈልግም ለአደጋ አጋላጭ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የስፖርት ሜዳ ተሰርቶልን በሳምንት ሁለት ጊዜ እንሰለጥናለን፡፡ ለመጫወትም ምቹ ነው፡፡ ከበፊቱ በተሻለ በስርዓት ኳስ የመጫወት እድሉንም ፈጥሮልኛል፡፡ ነገ ጎበዝ ኳስ ተጨዋች እንደምሆን እርግጠኛ ነኝ፡፡

ፋሪስ ዘሪሁን እባላለሁ፡፡ እግር ኳስ መጫወት በጣም ደስ ይለኛል። በአካባቢያችን የነበረው መጫወቻ ምቹ ስላልነበር ከጓደኞቼ ጋር እግር ኳስ ስጫወት በተደጋጋሚ ወድቄ ነበር፡፡ በዚህም የምወደውን ጨዋታ ለማቋረጥ ተገድጄ በጣም አዝኜ ነበር፡፡ ኒኮላ ሜዳ በደንብ ታደሰልን፡፡ ሜዳው ደረጃውን የጠበቀ የስፖርት ማዝወተሪያ ሆኗል። ከተሰራም አንድ ዓመት ሆኖታል፡፡ አሁን ከጨዋታ ውጪ ዳር ላይ ሆኜ በመቀመጥ ኳስ ከማቀበል፤ መሀል ሜዳ ገብቼ መጫወት ጀምሬያለሁ፡፡

በሜዳው ስጫወት ጉዳት ይደርስብኛል ብዬ አልሰጋም፡፡ ሜዳው በጣም ምቹ ነው፡፡ በመሆኑም ኳስ የመቆጣጠርና ጎል የማግባት ጥበብን ተምሬያለሁ፡፡ ብዙ ጊዜም ጎል አስቆጥራለሁ፡፡ እንደ ትልልቅ ኳስ ተጫዋቾች ቤተሰቤንና ሀገሬን ማስጠራት ነው የምፈልገው፡፡ ህልሜንም አሳካለሁ፡፡ እንደ እኔ ኳስ መጫወት የምትወዱ ልጆች ህልማችንን ለማሳካት ልምምድ ማድረግና ጊዜያችንን በአግባቡ መጠቀም አለብን፡፡

ናሆም ፍቅሬ እባላለሁ፡፡ ስፖርት መስራት ያስደስተኛል፡፡ እግር ኳስም እጫወታለሁ፡፡ ስፖርት መስራቴ ቅልጥፍናዬ እንዲጨምር አድርጎኛል፡፡ በተመቻቸው የስፖርት ሜዳ መጫወት መቻሌ የኳስ ተጨዋች የመሆን ፍላጎቴን የበለጠ ጨምሮልኛል፡፡ ለወደፊቱም ታዋቂ እግር ኳስ ተጨዋች እሆናለሁ። በሳምንትም ከትምህርቴ ጎን ለጎን ተገቢውን ልምምድ እያደረኩ ነው፡፡

አልአዛር እንዳልካቸው እባላለሁ። እግር ኳስ የመጫወት ፍላጎት አለኝ። በፊት እግር ኳስ መጫወት ብፈልግም መጫወቻ ቦታው ምቹ አልነበረም፡፡ የተመቻቸም ባለመሆኑ ስንጫወት የአፈሩ ሽታ ለሳይነስ ይዳርግ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በተሰራልን የስፖርት ማዘውተሪያ ስጫወት አንድ ዓመት ሆኖኛል። ከትምህርት ቤት መልስ በሳምንት ሁለት ቀን ልምምድ አደርጋለሁ። የኳስ ችሎታዬን እንዳሳይ ጠቅሞኛል። ጤነኛና ጠንካራም ሆኛለሁ። ኳስ ጨዋታ ከጨዋታ ባለፈ ስነ ምግባርንም አስተምሮኛል፡፡ የወደፊት ህልሜም እግር ኳስ ተጫዋች መሆን ነው። ይህንን ለማሳካት ደግሞ ትምህርቴን በማይጋፋ መልኩ ጊዜዬን እየተጠቀምኩ እገኛለሁ፡፡

ልጆች ዋና ኢንስፔክተር ጌቱ ጉማይዴ እባላለሁ፡፡ የእግር ኳስ አሰልጣኝ ነኝ። ኒኮላ ሜዳ በዘመናዊ መንገድ በመሰራቱ ለልጆች የተመቸ ሆኗል። በመሆኑም ከትምህርታችሁ ጎን ለጎን እናንተም ጊዜያችሁን አልባሌ ቦታ ከማሳለፍ ስፖርት መስራት አለባችሁ። ስፖርት መስራታችሁ አካላችሁን እና አዕምሯችሁን ከማዳበር በተጨማሪ ነገ ራሳችሁንና ሀገራችሁን የምታስጠሩ እና ከፍ የምታደርጉ ሀገር ተረካቢ ስፖርተኞች ትሆናላችሁ፤ በርቱ፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**እግር የላትም ትሄዳለች፤ አፍ የላትም ትናገራለች።**

**መልስ፡-** ሐ. ሰዓት

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**እንደ አህያ ዱላ፤ እንደ ድመት ወተት፤ እንደ ውሻ እሳት፤ እንደ ነብር ስጋ የሚወድ**

ሀ. ክትፎ

ለ. ቆጮ

ሐ. እርጎ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

# ተጠያቂነትን በማስፈን ሙስናን በተሟላ መልክ ለመከላከል እንደሚሰራ ተገለፀ

- **አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ መዲናዋ በፀረ ሙስና እንቅስቃሴ የተሻለ ውጤት እንድታስመዘግብ ባበረከተው አስተዋፅኦ እውቅና አግኝቷል**

**በመለሰ ተሰጋ**

መንግስታዊ አገልግሎትን በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በማድረግና ተጠያቂነትን በማስፈን ሙስናን በተሟላ መልክ ለመከላከል እንደሚሰራ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገልፀዋል፡፡

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ይህንን ያሉት ትናንት 22ኛው ዓለም አቀፍ የፀረ ሙስና ቀን "ትውልድን በስነ-ምግባር፣ ተቋምን በአሰራር" በሚል መሪ ሀሳብ በተከበረበት ወቅት ነው፡፡

መንግስታዊ አገልግሎትን በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በማድረግና ተጠያቂነትን በማስፈን ለሙስና አጋላጭ አሰራሮችን ለመዝጋት እና ከምንጩ ለማድረቅ የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎች እንደሚጠናከሩ የጠቆሙት ከንቲባ አዳነች፣ ሂደቱ የሁሉንም ተቋማት ትግል እና የሕብረተሰቡን ከፍተኛ ርብርብ እንደሚጠይቅ ገልፀዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በ22ኛው ዓለም አቀፍ የፀረ ሙስና ቀን መልዕክት አስተላልፈዋል

ከንቲባ ወይዘሮ አዳች አክለውም ቤተሰብ፣ ማህበረሰቡ፣ የኃይማኖት ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ የመንግስት ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበራት ወዘተ ሙስናን የሚጠየፍ ማህበረሰብ ለመፍጠር የማይተካ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

የፀረ ሙስና ትግላችን ይበልጡን ውጤታማ እንዲሆን የተጀመሩ የሪፎርም ተግባራትን ማጠናከር አስፈላጊ እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

ከንቲባዋ በዕለቱ ባደረጉት ንግግር፣ ባለፉት የለውጥ ዓመታት ሙስናን የብልፅግናችን ፀር፣ የኢፍትሐዊነት ምንጭ በመሆኑ ብሔራዊ አጀንዳ አድርገን ያፋፋምነው ትግል ከዚህ ቀደም የነበረን አስከፊ መንግስታዊ የተደራጀ ሌብነትን ማስቀረት አስችሏል ብለዋል።

በዚህም እንደ ሀገር ብሎም እንደ ከተማ የህዝብና የመንግስትን ሀብት በተገቢው የልማት ስራዎች ላይ በማዋላችን አስደናቂ የልማት ውጤቶች ማሳየት ችለናል ሲሉ አክለዋል፡፡

22ኛውን ዓለም አቀፍ የፀረ ሙስና ቀንን "ትውልድን በስነ-ምግባር፣ ተቋምን በአሰራር" በሚል መሪ ሀሳብ ስናከብር ሙስናን ለመዋጋት ያለንን ቁርጠኝነት እና የገባነውን ቃል በማደስ ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ ስርዓታዊ የተደራጀ ሌብነትን ማስቀረት ብንችልም፣ በግለሰብ ደረጃ የሚታይ በመንግስት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የሚፈፀመው ሌብነት እና ጉበኝነት ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው ብለዋል፡፡

አክለውም፣ ሙስና ፀያፍ የሆነ፣ የሀገርን ገፅታ የሚገታ፣ ትውልድን የሚጎዳ እና ኢ-ፍትሐዊነትን የሚያነግስ ተግባር በመሆኑ የመላው ማህበረሰብን እና የሁሉንም ተቋማት ትግል የሚጠይቅ ቀዳሚ ጉዳይ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

> **"ቤተሰብ፣ ማህበረሰቡ፣ የኃይማኖት ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ የመንግስት ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበራት ወዘተ ሙስናን የሚጠየፍ ማህበረሰብ ለመፍጠር የማይተካ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል"**

በየዘመናቱ በነበሩ የየስርዓቱ መሪዎች የሀገር ሀብት ወደ ውጪ በማሸሽና በማከማቸት፣ ከባለሃብቶች ጋር ከሀገር ውጪ በመስራት የሀገራችንን ልማት እና እድገት የሚያቀጭጭ ተግባር በዚህ ዘመን ታሪክ ሆኖ አልፏል ብለዋል፡፡

ይህን ጅምር ስራ የበለጠ ለማጠናከር በእያንዳንዱ ስራችን ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ በማፍራት ረገድ ኃላፊነት ያለብን ተቋማት አቅደን መስራት እና ለውጥ ማምጣት ይጠበቅብናል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ የሀሳብና የተግባር አንድነቱን በማፅናት በግለሰቦች ደረጃ ሳይቀር በመንግስት ኃላፊዎችና በሠራተኞች የሚታዩ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ላይ ሁላችንም እጅለ ለእጅ ተያይዘን መስራት እና ትውልድ ላይ የሞራል ልዕልና እንዲበለፅግ ስር የሰደደውን ኢፍትሐዊ አካሄድ መዋጋት ይጠበቅብናልም ብለዋል፡፡

የበለጠ የፀረሙስና ትግሉን በማጠናከር ተጠያቂነትን ለማስፈን ቃል የምንገባበትና የገባነውን ቃል የምናድስበት ስለሆነ ኃላፊነታችንን በአግባቡ በመወጣት፣ አሰራራችንን ግልፅ በማድረግ፣ ከሰው ንክኪ ነፃ ሆነን ህዝባችንን እናገልግል የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረጂ በዕለቱ በአቀረቡት ፅሑፍ፣ ባለፉት ሶስት ዓመታት ከፀረ ሙስና እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ በርካታ ለውጦች መምጣታቸውን አመላክተዋል፡፡

በለውጡ ዓመታት ውስጥ 10 ከቢሊዮን ብር በላይ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ ማዳን መቻሉን የጠቆሙት ኮሚሽነሩ፣ 73 ሺህ ካሬ ሜትር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ ከ100 ሺህ በላይ አመራሮች፣ ፈፃሚዎች እና ደላላዎች ላይ እርምጃ መወሰዱን አስታውቀዋል፡፡

በተያያዘ ዜናም የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን 22ኛውን የፀረ ሙስና ቀን ባከበረበት ዕለት የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እውቅና አግኝቷል፡፡

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ መዲናዋ በፀረ ሙስና እንቅስቃሴ የተሻለ ውጤት እንድታስመዘግብ ባከናወነችው ውጤታማ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አበርክቶው ላቅ ያለ እንደነበርም ተገልጿል። ተቋሙ ብልሹ አሰራርን የሚያጋልጡ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ወደ ህዝብ እያደረሰ እንዳለም ተገልጿል።

የፌዴራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከአሁን ቀደም ባዘጋጀው የእውቅና መርሃ ግብር ላይ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ጨምሮ ሙስናን እና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አንፃር ከፍተኛ አበርክቶ ለነበራቸው ሶስት የሚዲያ ተቋማት እውቅና መስጠቱ ይታወሳል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የበርካቶችን ህይወት ያቃና ማዕከል

- በማዕከሉ በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የተፈናቀሉ 518 አርሶ አደሮች እና ልጆቻቸው በ104 ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ መሆናቸው ተገልጿል



ፎቶ- ከፋይል
የእንስሳት ልማት እና ልህቀት ማዕከል ከፊል ገፅታ

**ማዕከሉ 10 የወተት ከብት እርባታ ሼዶች፣ 10 የዳልጋ ከብት ማድለቢያ ሼዶች፣ 11 የእንቁላል ጣይ ዶሮ እርባታ ሼዶች፣ 2 ዘመናዊ የመኖ ማቀነባበሪያ ሼዶች፣ 32 የምርት የማሳያና የመሸጫ ሱቆች እንዲሁም 2 የእንስሳት ክሊኒኮች እና 1 የአስተዳደር ህንፃን ያካተተ ነው**

## በይግለጡ ጓዴ

አርሶ አደር ዳኜ ጌታሁን በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የነበረ የእርሻ መሬታቸውን በልማት ሰበብ አጥተው ለበርካታ ዓመታት በችግር ኖረዋል። ይህን ሁኔታ በከተማዋ ዳርቻ የሚገኙ በርካታ አርሶ አደሮች አልፈውበታል፡፡ ችግሩን የተገነዘበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንስሳት እርባታና የልህቀት ማዕከል በመገንባት የቀድሞ የልማት ተነሺዎችን መልሶ ማቋቋም ችሏል፡፡

ማዕከሉ በቀደሙት ጊዜያት የእርሻ መሬታቸውን ለአጡ የአካባቢው አርሶ አደሮች ድጋፍ እና ስልጠና በመስጠት ህይወታቸውን እያቀናላቸው እንደሚገኝ አርሶ አደር ዳኜ እና ሌሎችም ይናገራሉ፤ በማዕከሉ የዶሮ እርባታ ሼድ እና ብድር ተመቻችቶላቸው ወደ ስራ የገቡት አርሶ አደር ዳኜ እና 15 ጓደኞቻቸው "አንድነት የዶሮ እርባታ እና እንቁላል ሽያጭ የህብረት ስራ ማህበር" የተሰኘ ማህበር መስርተው ወደ ስራ ከገቡ ሰነባብተዋል፡፡

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በተገነባው የእንስሳት ልማት እና ልህቀት ማዕከል በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የተፈናቀሉ 518 አርሶ አደሮች እና የአርሶ አደር ልጆች በ104 ማህበራት ተደራጅተው የተለያዩ ስራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በወተት ከብት እርባታ ማህበር ከተደራጁ ተጠቃሚዎች መካከል አርሶ አደር በቀለ መርጋ አንዱ ናቸው፡፡ ማህበሩ 15 አባላት ያሉት ሲሆን፣ አባላቱ በሚያገኙት ገቢ ህይወታቸውን ማሻሻላቸውን ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ተናግረዋል፡፡

ማህበሩ በወተት ላሞች እርባታ ተደራጅቶ ወደ ስራ ከገባ ሁለት ዓመታት ማስቆጠሩን የሚናገሩት አርሶ አደር በቀለ፣ አሁን ማህበሩ 15 ላሞች ያለው ሲሆን፣ በቀን እስከ 60 ሊትር ወተት ያገኛል። በማዕከሉ ውስጥ በሚገኙ የወተት መሸጫ ሱቆች አንድ ሊትር ወተት በ75 ብር ሂሳብ ያስረክባል፡፡ በዚህም የአባላቱ ኑሮ ተሻሽሏል፡፡

የእንስሳት እርባታና የልህቀት ማዕከሉ ከወተት ላም እርባታ ውጪ ሌሎች ስራዎችም ይከናወኑበታል፤ ለአብነትም የዶሮ እርባታ ስራ ተጠቃሽ ነው። በማዕከሉ 11 የዶሮ እርባታ ሼዶች ይገኛሉ። በዚህም በቀን ወደ 35 ሺህ እንቁላል ይመረታል፡፡

ከ11ዱ ሼዶች አንዱ የእነ አቶ ዳኜ ማህበር ሲሆን፣ 3 ሺህ 200 እንቁላል ጣይ ዶሮዎች አሏቸው፡፡ በከተማዋ በሚገኙ በ11ዱም ክፍለ ከተሞች እና በየወረዳዎቹ በተዘጋጁ የመሸጫ ሱቆች እና ባዛሮች ላይ እንቁላል በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም የዶሮ መኖ ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ እንደሚገኝ አርሶ አደሩ ገልጸው፣ ይህን ታሳቢ በማድረግ የእንቁላል ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደሚለያይ ጠቁመዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ለማቋቋምና ዘላቂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በእንስሳት ሀብት ልማት ትግበራ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የሚከናወንበት ዘመናዊ ማዕከል ነው። በማዕከሉ ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ የዋጋ ንረት ሚዛን በመጠበቅና ገበያን በማረጋጋት ምቹ ሁኔታ የሚፈጠርበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

በስፍራው ተገኝተን ባደረግነው ቅኝት የልህቀት ማዕከሉ ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ የልምድ ልውውጥ፣ የምርምርና የስርፀት ስራዎችን በመስራት የእንስሳት እርባታ ዘርፎችን በማስፋትና እሴት የተጨመረባቸው የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ ላይ እንደሚገኝም ነው ለመታዘብ የቻልነው፡፡

ልክ እንደነ አርሶ አደር ዳኜ በልህቀት ማዕከሉ የስራ እድል የተፈጠረላቸው አርሶ አደር ጥላሁን ጴጥሮስ እና ጓደኞቻቸውም ማዕከሉ ህይወታቸውን በመቀየር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑን ነው የሚመሰክሩት፡፡

አርሶ አደር ጥላሁን በማዕከሉ 10 አባላትን ይዘው በመደራጀት በእንስሳት ተረፈ ምርት ኮምፖስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) እንደሚያዘጋጁ ገልፀው፤ ሂደቱን ጠብቆ የተዘጋጀውን ኮምፖስት በከተማ ግብርና እና በአረንጓዴ ልማት እንክብካቤ ስራ ለተደራጁ ማህበራት እንደሚያስረክቡ ነግረውናል። በኮምፖስት ዝግጅት የስራ እድል ተጠቃሚ በመሆን ገቢአቸውን ማሳደግ መቻላቸውንም ገልፀዋል፡፡

በማዕከሉ ምንም የሚባክን ተረፈ ምርት የለም የሚሉት አቶ ጥላሁን፣ በየጊዜው ሂደቱን ጠብቀው ኮምፖስት በማዘጋጀት አንድ ኩንታል ኮምፖስት በ700 ብር ለክፍለ ከተሞች በማቅረብ ላይ ናቸው። በዚህም በአንድ በኩል የማዕከሉን ንጽህና ይጠብቃሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢኮኖሚያቸውን በማሳደግ ቤተሰባቸውን በተሻለ ደረጃ ያስተዳድራሉ፡፡

በእንስሳት እርባታና ልህቀት ማዕከል ረዳት የእንስሳት ሀኪም አብዲሳ ለገሰ በእንስሳት ማድለብ ዘርፍ ሙያዊ እገዛ በማድረግ የህክምና አገልግሎት ይሰጣል። ወደ ማዕከሉ የሚገቡ በሬዎችን ከመምረጥ እና ከመግዛት ጀምሮ በአግባቡ በመለየት ሙያዊ ድጋፍ እንደሚሰጡ ባለሙያው ያስረዳል፡፡ ወደ ማዕከሉ የሚገቡ በሬዎችን እንዴት በፍጥነት ማደለብ እንደሚቻል፣ የእንሰሳት ንጽህናና ጤና መጠበቅ ብሎም አድልቦ ወደ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል ሙያዊ እገዛ ያደርጋሉ። ከአዳማ፣ ከቦረና እና ባሌ አካባቢዎች በሬዎችን በመግዛት ለማድለብ ወደ ማዕከሉ ያስገባሉ፡፡ አንድ በሬ ለመድለብ እስከ 120 ቀናት እንደሚወስድ በሳይንስ የተቀመጠ መስፈርት ሲሆን፣ የማዕከሉ በሬዎችን በ90 ቀናት በማድለብ ወደ ገበያ እንደሚቀርቡም ገልፀዋል፡፡

እንደ ረዳት የእንስሳት ሀኪም አብዲሳ ገለጻ፣ በማዕከሉ ከ60 በላይ በሬዎች በመድለብ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ በሬዎቹ ደልበው ለሽያጭ እስኪደርሱ ድረስ አመጋገባቸውን እንዲሁም ሙሉ የጤና ምርመራ ክትትል ያደርጋሉ፡፡ እንስሳት ለተለያዩ የመተንፈሻ አካላት እና ለሌሎች በሽታዎች ተጋላጭ ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህንንም ለመከላከል የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

አቶ አብዮት ጫላ በልህቀት ማዕከሉ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል አዳቃይ ቴክኒሻን ናቸው፡፡ የወተት ምርት ጭማሪን ታሳቢ በማድረግ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራሉ፡፡ የደረሱ ጊደሮች ምልክት ሲያሳዩ በአርቴፊሻል ቴክኖሎጂ ዘዴ እንስሳትን እንደሚያዳቅሉ ገልጸው፣ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው የወተት ላሞች ካልተዳቀሉት ላሞች እስከ 30 ሊትር ወተት እንደሚጨምር ይናገራሉ፡፡

የወተት ምርት እንዲጨምር የእንስሳት አመጋገብ ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ የእንስሳት ባለሙያው በመጠቆም ለእንስሳት መኖ ዝግጅት የሚውል እንደሳስፓኒያ ዓይነት ችግኞችን እና ሳርን በግቢው ውስጥ በመትከል ለመኖ ግብዓት ጥቅም ላይ ያውላሉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ልማት እና ልህቀት ማዕከል ስራ አስኪያጅ አቶ አሌክስ ደመቀ ማዕከሉ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ስራ የገባ መሆኑን አውስተው፣ የተቋቋመበት ዋና ዓላማም በተለያዩ ምክንያቶች በከተማዋና በዙሪያዋ በልማት የተነሱ አርሶ አደሮችን እና የአርሶ አደር ልጆችን መልሶ በማቋቋም የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ ለማስቻል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በማዕከሉ የተመረተውን የእንስሳት እና እንስሳት ተዋጽኦ ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ገበያን በማረጋጋት ረገድ የራሱን ሚና እየተጫወተ ያለ ማዕከል ነው ብለዋል፡፡

አክለውም፣ በእንስሳት እርባታ ዘርፍ የበሬ ማድለብ፣ የወተት ከብት እና የዶሮ እርባታ እንዲሁም የመኖ ማቀነባበር ልማት ስራ እየተሰራ መሆኑን አቶ አሌክስ አስታውቀዋል፡፡

እንደ አቶ አሌክስ ገለጻ፣ በአንደኛና በሁለተኛ ምዕራፍ የተገነባው የማዕከሉ ክፍል 10 የወተት ከብት እርባታ ሼዶች፣ 10 የዳልጋ ከብት ማድለቢያ ሼዶች፣ 11 የእንቁላል ጣይ ዶሮ እርባታ ሼዶች፣ 2 ዘመናዊ የመኖ ማቀነባበሪያ ሼዶች፣ 32 የምርት የማሳያና የመሸጫ ሱቆች እንዲሁም 2 የእንስሳት ክሊኒኮች እና 1 የአስተዳደር ህንፃ ያካተተ ነው፡፡ ሶስተኛው የግንባታ ምዕራፍም ይካሄዳል።

ማዕከሉ ትልቅ የምርት እና የተሞክሮ የልህቀት ማካፈያ ማዕከል መሆኑን አቶ አሌክስ ገልጸው፣ ምርት ከማምረትም በላይ የከተማ ግብርና ከተማ ውስጥ ሆኖ መስራት ይቻላል የሚለውን አስተሳሰብ በተግባር ልምድ የሚወሰድበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የእንስሳት የእርባታ እና የልህቀት ማዕከሉ ከአዲስ አበባ ከተማ አልፎ ለሌሎች ክልሎችም ተግባር ተኮር የቴክኖሎጂ የእውቀት ሽግግር ተሞክሮ እያካፈለ ያለ ማዕከል መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ማዕከሉ በዶሮ እርባታ፣ በወተት ልማት እና እንስሳት ማድለብ ዘርፍ ለሚሰማሩ አካላት የእውቀት፣ የምርምር፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ አጋዥ ሆኖ ማህበረሰቡን በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# መዲናዋ በታዳሽ ኃይል መንገድ

በለይላ መሀመድ

የምድራችን ስጋት የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል አማራጭ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋት ወሳኝነት አለው፡፡ ለዚህ ደግሞ ቴክኖሎጂውን ማስተዋወቅና ማስረጽ አስፈላጊ ነው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ከሚያስችሉ አማራጭ ቴክኖሎጂዎች መካከል የፀሐይ ሀይል (የሶላር ኢነርጂ) አንዱ ነው። ቴክኖሎጂው የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል ምቹ አካባቢን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በከተማዋ ያለውን የአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሆነውን የፀሐይ ሀይል (የሶላር ኢነርጂ) ቴክኖሎጂን ለመተግበርና ለማስፋት ዘርፈ ብዙ ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡



ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እየተጠቀመበት ካለው የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ በከፊል

## የፀሐይ ሀይል (የሶላር ኢነርጂ) ቴክኖሎጂ ምንነት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአየር ንብረት ለውጥ እና አማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የኢነርጂ ኦዲት እና ፍቃድ ቡድን መሪ አቶ መላኩ ጋሪ እንደሚያብራሩት፣ የኢነርጂ ወይም የሀይል ምንጮች ታዳሽ እና ታዳሽ ያልሆነ ሀይል በሚል በሁለት ይከፈላል። ታዳሽ ኢነርጂ ወይም ሀይል ሲባል በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሳቸውን መተካት የሚችሉና የማያልቁ የሀይል አይነቶች ናቸው፡፡ ሌላው የታዳሽ ሀይል ባህሪ ለአካባቢ ተስማሚና የአየር ብክለት የማያመጡ ናቸው፡፡ ታዳሽ ሀይል የሚባሉት የውሀ፣ የፀሐይ፣ የንፋስ፣ ባዮማስ ማለት ስነ ህይወታዊ (ከእንስሳት ስብና ከእጽዋት ዘይት የሚገኝ)፣ ባዮዲዝል (የእጽዋትና እንስሳት ውጤቶች እና ተረፈ ምርት) ኤሌክትሪክ ያመነጫል። ሙቀት ይሰጣል፡፡ ከዲዝል ጋር ተቀላቅሎ ሞተር ማንቀሳቀስ ይችላል። ባዮጋዝ (ከእንስሳት አዛባ የሚመረት) ኤሌክትሪክ የሚሰጠውን አገልግሎት ይተካል፡፡ እንዲሁም የጂኦተርማል ሀይል ናቸው፡፡ ታዳሽ ኢነርጂ ያልሆኑት ደግሞ ራሳቸውን ለመተካት በሚሊየን የሚቆጠሩ ዓመታት የሚፈጅባቸውና የሚያልቁ ናቸው። እነዚህም ከቅሪት አካል ክምችት (Fossil fuel) የሚገኙ ናቸው፡፡ የነዳጅ ውጤቶች፣ የተፈጥሮ ጋዝ እና የድንጋይ ከሰል በማሳያነት ይጠቀሳሉ፡፡

ቡድን መሪው አቶ መላኩ እንደሚገልፁት፤ የፀሐይ ሀይል (የሶላር ኢነርጂ) ቴክኖሎጂ አንዱ ታዳሽ ኢነርጂ ወይም ሀይል ምንጭ ነው፡፡ የፀሐይ ሀይል (የሶላር ኢነርጂ) ምንጭ ፀሐይ ነው፡፡ ዋና ዋና የፀሐይ ሀይል (የሶላር ኢነርጂ) አይነቶች አሉ፡፡ አንደኛው የፀሐይ ሙቀት ኃይል ነው፡፡ ይህም በቀጥታ ከ ፀሐይ የሚመጣውን ብርሀን ወደ ሙቀት በመቀየር ሙቅ ውሀ ወይንም እንፋሎት ለማምረት ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ የውሀ ማሞቂያ ሶላር ቴክኖሎጂ ለዚህ ተጠቃሽ ነው፡፡

ሁለተኛው ፎቶቮልቲክ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ የፀሐይ ብርሃንን በሶላር ፓኔል (PVC) ወደ ኤሌክትሪክ በመቀየር ኤሌክትሪክ ያመርታል፡፡ በፎቶቮልቲክ ስርዓቶች አማካኝነት የፀሐይ ብርሃንን ወደ ኤሌክትሪክ የሚቀይር ወይም በቀጥታ ከፀሐይ ኤሌክትሪክ የሚያመርት ስርዓት ማለት ነው፡፡ ይህ ብርሃንን (ፎቶዎችን) ወደ ኤሌክትሪክ (ቮልቴጅ) የመቀየር ሂደት የፎቶቮልታይክ (PV) ተጽዕኖ ይባላል። በሌላ አገላለጽ ቀጥታ የፀሐይ ብርሀንን በማጠራቀምና ወደ ኤሌክትሪክ በመቀየር ለተለያዩ አማራጮች ማለትም ለአምፖል፣ ቴሌቭዥን፣ ኮምፒዩተር እና ሌሎች በኤሌክትሪክ ለሚሰሩ እንደ ፕሪንተር፣ ኮፒ ማሽን ለመሳሰሉ መገልገያዎች መጠቀሚያነት እንድንገለገልበት ያደርጋል፡፡ ብዙ የፀሐይ ብርሀን ካጠራቀምን ደግሞ ለምግብ ማብሰያነት መጠቀም እንደሚቻል ቡድን መሪው ገልጸዋል፡፡

## በአዲስ አበባ ከተማ የፀሐይ ኃይል አጠቃቀም ተሞክሮ

እንደ ቡድን መሪው አቶ መላኩ ገለጻ፤ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አሁን ላይ ቢሮ ውስጥ ለመብራትና ለሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎች እንደ ሰርቨር፣ ኮፒ ማሽን፣ ኮምፒውተርና ተያያዥ ነገሮች የሚጠቀመው የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂን ነው፡፡ በተለይም አስቸኳይ ስራ በሚሰራባቸው እንደ ፋይናንስ፣ ግዥ፣ የሰው ሀብት ልማት ባሉ የስራ ክፍሎች እንዲሁም የመሰብሰቢያና የስልጠና መስጫ አዳራሾች መብራት በሚጠፋበት ወቅት ያለምንም የሀይል መቆራረጥ ስራቸውን እንዲያከናውኑ የሚያስችል በድጋፍ 10 ኪሎ ዋት መሰብሰብ የሚችል የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ተገጥሟል፡፡ እነዚህ የሶላር ኢነርጂ የተገጠመላቸው የስራ ክፍሎችና አዳራሾች የመብራት ሀይል ባይኖርም በሀይል እጥረት አገልግሎት መስጠታቸውን አያቋርጡም፡፡

ከተቋማት አንጻርም በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የሚገኘው የሊደትኮ ፒ ኤል ሲ(Lydetco PLC) የሶላር ኢነርጂ አስመጪ ካምፓኒ ህንጻውን ሙሉ እየተጠቀመ ያለው የፀሐይ ብርሀን በሚያገኘው 34 ኪሎ ዋት ሀይል ነው፡፡ ህንጻው ላይ ምንም አይነት የኤሌክትሪክ ሀይል አይጠቀምም፡፡ በተመሳሳይ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር 110 ኪሎ ዋት አካባቢ ሀይል ከፀሐይ ብርሀን ይጠቀማል። የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ጽህፈት ቤት 5 ኪሎ ዋት የሚሆን ሀይል ከፀሐይ ብርሀን እየተጠቀመ ነው፡፡ በጀነሬተር ይጠቀሙ የነበረውን አገልግሎት በሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ተክተዋል፡፡ በግለሰብ ደረጃም በተለይም በከተማ ግብርና ዘርፍ የውሃ ፓምፕ የሚጠቀሙ አርሶ አደሮች የነዳጅና የአካባቢ ብክለትን ለማስቀረት በፀሐይ ብርሀን የሚሰሩ ፓምፖችን ወደ መጠቀም እየገቡ ነው፡፡ የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ውሃ የሚያሞቁ ተቋማትም እየመጡ ነው፡፡ ለምሳሌ መቄዶኒያ የበጎ አድራጎት ድርጅት በምሳሌነት ይጠቀሳል፡፡

ይህም ወጪ ከመቆጠብና የአገልግሎት መቆራረጥ እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ የአካባቢ ብክለት እንዳይከሰት አግዟል፡፡ ይህ የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ በሌሎች ተቋማትም እንዲስፋፋ ምን እየተሰራ እንደሆነ የዝግጅት ክፍሉ ለቡድን መሪው አቶ መላኩ ላነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂን ማስፋት ከተፈጥሮ አማራጭ የሀይል ኢነርጂን በመጠቀም ለዚህ የሚወጣውን ወጪ ከመቆጠብ በተጨማሪ የአካባቢ ብክለት በመከላከል ረገድ ፋይዳው የላቀ ነው።

የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማስፋት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለተቋማት እና ለግለሰቦች በየጊዜው ተከታታይነት ባለው መልኩ ስልጠና ይሰጣል፡፡ በተለይም በሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የህክምና አገልግሎቶችን በሚሰጡ ተቋማት ቴክኖሎጂውን እንዲጠቀሙ ጥናቶች ተሰርተዋል፡፡ ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ምን ያህል ፍላጎት እንዳላቸውና “አስፈላጊነቱ እስከ ምን ድረስ ነው?” የሚለውን ለማወቅ በየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ እና በተወሰኑ ጤና ጣቢያዎች ላይ ጥናት ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክፍለ ከተሞች ጀነሬተር ከሚጠቀሙ ይልቅ ሶላር ኢነርጂ ቢጠቀሙ ያለውን ልዩነት የሚያሳይ ጥናትም ተካሂዷል፡፡ ጥናቱም ጀነሬተር በነዳጅ የሚሰራ ከመሆኑ አንጻር ለነዳጅ የሚወጣውን ወጪና ከጀነሬተሩ የሚወጣው ጭስም አካባቢን በመበከል ምን ያህል ለጤና ጎጂ እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡ በተገኘው ውጤትም ከጀነሬተሩ የሚወጣው ጭስ የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ከሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ ባለፈ የድምጽ ብክለት በማስከተል ረገድም ጫናው ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ የጤና ተቋማት የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂን በተገቢው መልኩ መጠቀም ከቻሉ በመብራት መቆራረጥ ችግር መስጠት ያለባቸው አገልግሎት እንዳይስተጓጎልና ህሙማንን ለመርዳት እገዛው የላቀ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

የተለያዩ የመንግስት ተቋማትም ሆኑ የግል ተቋማት እንዲሁም ግለሰቦች የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂን ቢጠቀሙ የመብራት ሀይል በሚቆራረጥበት ወቅት የነዳጅ ወጪያቸውን ከመቀነሳቸውም በተጨማሪ ስራ እንዳይስተጓጎል በማድረግ ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ ለአካባቢ ተስማሚነት አለው፡፡ የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስም ፋዳይው የላቀ እንደሆነም አክለዋል፡፡

## ቴክኖሎጂውን ለማስፋት ያሉ ፈተናዎች

የፀሐይ ሀይል (ሶላር ኢነርጂን) ቴክኖሎጂን በመተግበር ረገድ የተጀመሩ ስራዎች አሉ፡፡ ይህንን ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነውን ቴክኖሎጂ ለማስፋፋትና ለመጠቀም አንዱ ፈተና በቴክኖሎጂ አጠቃቀሙ ላይ የክህሎት ክፍተት መኖሩ እና ቴክኖሎጂዎችን ለማወቅ የሚደረግ ጥረት በቂ አለመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው የፀሐይ ኃይል ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ውድ መሆናቸው ነው፡፡ ቴክኖሎጂው ከውጭ የሚገባ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በቀላሉ መግዛት አይቻልም። ለቴክኖሎጂው አለመስፋፋት ሌላው ፈታኝ የሆነው በከተማ ደረጃ የአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀምና ቁጥጥር ዙሪያ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ህጎች፣ መመሪያዎችና ስትራቴጅዎች አለመኖራቸው ነው፡፡ እነዚህና መሰል ነገሮች ቴክኖሎጂውን ለማስተግበር አስቸጋሪ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

## ቴክኖሎጂውን ለማስፋፋት ምን እየተሰራ ነው?

እንደ ቡድን መሪው ገለጻ፣ ዘርፉ ቢስፋፋ ጠቀሜታው ሰፊ ነው፡፡ የኢኮኖሚ እድገትን ያፋጥናል የአካባቢ ብክለትን በማስቀረት ረገድ ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ባለስልጣኑ አንዱ የትኩረት መስክ አድርጎ እየሰራ ነው፡፡ ለዚህም የባለሙያና የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማስፋት ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡ የባለሙያዎችን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክህሎት እና በታዳሽ ኢነርጂ ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ የታዳሽ ኢነርጂ ምንጭና ቴክኖሎጂን ማስፋፋትም ሌላው የትኩረት መስክ ነው፡፡ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ዘርፎች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማሻሻልም ታቅዷል። ከአስመጪዎችና ተጠቃሚዎች ጋር ተቀናጅቶ ለመስራትም እቅድ ተይዟል። በከተማ ደረጃ በአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀምና ቁጥጥር ዙሪያ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ህጎች፣ መመሪያዎችና ስትራቴጂዎች እንዲዘጋጁና ከተማዋን የሚመጥን የኢነርጂ አደረጃጀት እንዲዘጋጅ ማድረግም ሊተገበሩ የተቀመጡ የትኩረት መስኮች ናቸው፡፡

እንደ ሀገር ቴክኖሎጂው በስፋት እየተሰራበት ነው፡፡ የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ መብራት በሌለባቸው አካባቢዎች ላይ የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂን በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል እየሰራ ነው፡፡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የሶላር ኢነርጂ ቴክኖሎጂን በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

## “ወደ ኋላ... ከገጽ 6 የዞረ

ይገባናል፡፡ አዳዲስ ፈጠራዎችን ጥቅም ላይ ማዋል ይገባናል፡፡ ብዝሃ ኢኮኖሚ ትግበራን አጠናክሮ መተግበር አለብን። ግብርናን፣ ቱሪዝምን፣ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን፣ ማዕድንን፣ ኢንዱስትሪውንና ሌሎችን የኢኮኖሚ ዘርፎች በጥናት ላይ በተመሰረተ አግባብ ለፈጣን የሀገር ዕድገትና ብልፅግና ጥቅም ላይ የማዋሉ ጅምር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

አያይዘውም፤ “መፍጠን የሚለውን እሳቤ እንዴት መተግበር እንችላለን?” ለሚለው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤“የኛ ዕድገት በጣም የዘገየ፣ መሀል ላይም ተንሸራተን የጠፋንበት ወቅት እንደነበር ይታወቃል፡፡ በፈጣኑ እና በውስብስቡ የዓለም ዕድገት ግስጋሴ ውስጥ ተወዳዳሪ እና ተፎካካሪ ሆኖ ለመገኘት ተግባራትን በፍጥነትና በውጤታማነት ማከናወን ግድ ይላል፡፡ ፍጥነታችን በፈጠራ እና በዓላማ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡

ፍጥነታችን አንዳንዴ የዝላይ አካሄድንም የሚጠይቅበት ጊዜና ሁኔታ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ አውሮፓዊያን አሁን የደረሱበት የዕድገት ደረጃ ላይ ለመገኘት ብዙ መቶ ዓመታትን አልፈዋል፡፡ እኛ እነሱ የደረሱበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ መቶ ዓመታትን መጠበቅ አይኖርብንም። በሃያ፣ በአሥር እና ከዚያም ባነሰ ጊዜ ውስጥ ለማሳካት መዘለል ያለባቸውን የዕድገት ሂደት ደረጃዎች መዝለል ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ያሉንን ሃብቶች ለይቶ ማወቅ እና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ወሳኝ ነው” የሚሉት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላምና ደህንነት ተመራማሪ ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር)፣ የመፍጠንን እሳቤ ከሀገራዊ ቁልፍ አጀንዳዎች ጋር በማስተሳሰር በሰጡት ማብራሪያ፤ “ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የነበሩበትን በርካታ ጫናዎች በመቋቋም ለማጠናቀቅ እና ጥቅም ላይ ለማዋል የተሄደበት መንገድ እንደ ሀገር ለተያዘው የመፍጠን መርህ በማሳያነት የሚጠቀስ ስለመሆኑ ምሁሩ አንስተዋል። ኢትዮጵያ ለዓመታት ያለባህር በር እንድትቆይ ያደረጋትን እና ከቀይ ባሕር ጫፍ ገፍቶ ያራቃትን ችግር ለመቅረፍ የምታደርገው የዲፕሎማሲና ተያያዥ የመፍትሔ ጉዞ መፍጠን ይኖርበታል፡፡ የባሕር በርን የማግኘት ጉዳይ በመፍጠን ብቻ ሳይሆን፤ አንዳንድ ሂደቶችን ዘለን ማለፍ ሁሉ ይጠበቅብናል፡፡”

በመጨረሻም ለሀገር ዕድገት እና ብልፅግና ወሳኝ የሆነውን የመደመር መንግስት አስተሳሰብ በህብረተሰቡ ዘንድ ለማስረጽ እንዲቻል መከናወን ስለሚገባቸው ተግባራት ምክረ ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት፤ የመደመር መንግሥት እና ከዚያ በፊት ለንባብ የበቁት የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መጽሐፍትን ማንበብ ከሁሉም ዜጋ ይጠበቃል፡፡ ይህንን የምለው ለፖለቲካ ድጋፍ አይደለም፡፡ የሀገራችንን ዘመናት የተሻገረ፣ ጥልቅ እና ውስብስብ ችግር ለመፍታት በመጽሐፍቱ ላይ የተተነተኑ ጥልቅ ሃሳቦች መፍትሔ ይሰጣሉ፡፡ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት የመፍትሔ አማራጮችን ያመላክታሉ፡፡ ስለዚህ ማንበብ የሚችል ሁሉ ማንበብ ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪም፤ የመገናኛ ብዙሃን አማራጮች በተለያዩ አግባቦች የመጽሐፍቱን ይዘትና ጭብጥ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዘመኑ የፈጠራቸውን የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች ይህንን ለመሰለ ሀገራዊ ፋይዳ ላለው ዓላማ ማዋል መለመድ ይኖርበታል፡፡

በርካታ ሕዝብ በሚሰባሰብባቸው የማህበራዊ እሴት መሰረቶቻችን ላይ ሃሳቦቹ እየተነሱ ውይይቶችን ማካሄድም ያስፈልጋል፡፡ መጽሐፍቱ ለፖሊሲ፣ ለስትራቴጂ መነሻዎች በመሆናቸው፤ የየዘርፉ ምሁራንና ሊሂቃን ከዚህ ዓላማ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመጽሐፍን ዳሰሳ (ቡክ ሪቪው) መሥራት፣ ፓናል ውይይት የማሰናዳትና ሙግት (ክርክር) የማድረግ ... ምሁራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ተቋማት “ወርቃማ ሰኞ” በሚል በሚያሰናዷቸው ሳምንታዊ አጫጭር የውይይት እና የመማማሪያ መድረክ ላይ ከመጽሐፍቱ ጭብጥ መካከል ንዑስ ጉዳዮችን በማንሳትና በመዘጋጀት የወርቃማ ሰኞ መድረካቸው አካልም ማድረግ ይችላሉ፡፡

## በልኩ... ከገጽ 9 የዞረ

በተያዘው የ2018 በጀት ዓመት ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ 7 ሺህ ቶን ኮምፖስት ለማምረት እቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዘንድሮ ሩብ ዓመትም 1 ሺህ 750 ቶን ኮምፖስት ለማምረት ታቅዶ 1 ሺህ 67 ቶን ኮምፖስት በማምረት ከ7 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡ ከእቅድ አኳያ አፈፃፀሙ 65 በመቶ ሲሆን፤ ይህም የሆነበት ምክንያት በዘርፉ የተሰማሩ ማህበራት ሼድ የሌላቸውና የክረምት ወቅትም ስለሆነ ብዙ ምርት ባለማምረታቸው እንዲሁም የተጠቃሚው ፍላጎት አነስተኛ በመሆኑ ነው፡፡ በበጋ ወራት ማህበራቱ የሚያመርቱት ምርት እየጨመረ ይሄዳል። ለምሳሌ በጥቅምት ወር 583 ቶን ለማምረት ታቅዶ 612 ቶን በማምረት ከእቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

አቶ በላይ እንደሚገልጹት፤ በከተማዋ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ 60 በመቶ የሚሆነው የሚበሰብስ እና ወደ ኮምፖስት መቀየር የሚችል ነው፡፡ ይህ ቀላል ቁጥር አይደለም፡፡ አቅም ኖሮ በሙሉ ወደ ኮምፖስት መቀየር ቢቻል በዘንድሮ ዓመት ይመነጫል ተብሎ ከታቀደው (856 ሺህ 135) ደረቅ ቆሻሻ ወደ 513 ሺህ 681 ቶን ኮምፖስት ማምረት ይቻላል፡፡ ይህም በገንዘብ ሲተመን ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ማስገኘት ያስችላል ማለት ነው፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ የሚበሰብስ ቆሻሻ ወደ ቆሻሻ መጣያ ቦታ (ላንድፊል) በማጓጓዝ እየተወገደ ይገኛል፡፡ ቆሻሻን ወደ ሀብት መቀየር ላይ በሰፊው ቢሰራ ወደ ላንድፊል የሚሄደውን መጠን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ፣ ብክለትን መከላከል፣ ለበርካቶች የስራ ዕድል መፍጠርና ገቢ ማስገኘት ይቻላል፡፡ በዘንድሮው ዓመት መበስበስ ከሚችለው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ አንድ በመቶ የሚሆነውን ወደ ኮምፖስት ለመቀየር ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

አቶ በላይ እንደሚገልፁት፣ ከደረቅ ቆሻሻ ኮምፖስት ማምረትን በስፋት ከመተግበር አኳያ የተለያዩ ፈተናዎች አሉ፡፡ አንደኛ ኮምፖስት ማምረት ረጅም ጊዜ የሚፈልግ መሆኑ ነው፡፡ የመጨረሻውን ምርት ለማግኘት ቢያንስ የሁለት ወር ጊዜ ይወስዳል፡፡ ሌሎች ለመልሶ መጠቀም የሚውሉ ቆሻሻዎች ግን ወዲያው ተሰብስበው በቶሎ ገቢ ማግኘት ያስችላሉ፡፡ ሁለተኛ የኮምፖስት ዝግጅትና ማምረት ሰፊ የመስሪያ ቦታ ይፈልጋል፡፡ ስራውን ለማከናወን የራሱ የሆነ እንደ አልባሳት፣ አካፋና የተለያዩ የስራ መሳሪያዎች ያስፈልገዋል። ከዚህም ባሻገር ኮምፖስቱን በዋናነት የሚጠቀሙት በከተማዋ በአረንጓዴ ልማትና እንክብካቤ የተሰማሩ አካላት ናቸው፡፡

በአዲስ አበባ ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሀብት የመቀየር ስራ በተለይ ኮምፖስት ማምረት የተጀመረው ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ነው። በወቅቱም ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ በመልሶ መጠቀምና ኮምፖስት እየዋለ የነበረው 6 ነጥብ 4 በመቶ ድርሻ ነበረው፡፡ በ2013 ዓ.ም በዘርፉ የተሰማሩ ማህበራት 1 ሺህ 560 ቶን ኮምፖስት በማምረት ለገበያ አቅርበዋል፡፡ በ2017 ዓ.ም 5 ሺህ 460 ኮምፖስት ማምረት ተችሏል፡፡ ይህም በየጊዜው የኮምፖስት ምርት እያደገ መምጣቱን የሚያሳይ መሆኑን እንደሚያሳይ አቶ በላይ ያስረዳሉ፡፡

የኮምፖስት ምርትን ለማሳደግ በማዕከል ደረጃ ኮምፖስት የሚመረትባቸው ማዕከላት ግንባታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ አንደኛው የመልሶ መጠቀምና ኮምፖስት የሚመረትበት ማዕከል ግንባታ በቦሌ አራብሳ አካባቢ እየተከናወነ ሲሆን፤ ይህም ደረቅ ቆሻሻን በመለየት ለመልሶ መጠቀምና ኮምፖስት በስፋት የሚውልበትን ዕድል የሚፈጥር ነው፡፡

ሌላው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ያለውን የግብርና ምርቶችና የእንስሳት ተረፈ ምርቶችን ለመጠቀም የኮምፖስት ማዕከል ለመገንባት የቦታ ልየታ ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 እንዲሁ ሼድ በመገንባትና በቴክኖሎጂ በመታገዝ ኮምፖስት በስፋት ለማምረት እቅድ ተይዞ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

ከዚህም ባሻገር በተያዘው በጀት ዓመት በከተማዋ በሁሉም (በ119) ወረዳዎች አንድ አንድ በኮምፖስት ማምረት የተሰማሩ ማህበራትን ለማቋቋም ጊዜያዊ የቦታ ልየታ ስራ ተጀምሯል፡፡ ይህም በዘርፉ የሚሰማሩ ማህበራት ቁጥርና የሚመረተውን ኮምፖስት መጠን በእጥፍ ማሳደግ የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ከስራ እና ክህሎት ቢሮ፣ ከመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ እና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ጋር እየተሰራ እንደሚገኝ አቶ በላይ ጠቁመዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በኮምፖስት ማምረት ለተሰማሩ ማህበራት የክህሎት ድጋፍ፣ የስራ መሳሪያዎች (አካፋ፣ አልባሳት፣ ቴርሞሜትርና የተለያዩ ግብአቶች) እና የገበያ ትስስር በማመቻቸት ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ ማህበራቱ የሚያመርቱት ምርት ዋነኛ ተጠቃሚ የአዲስ አበባ ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ሲሆን፤ ከቢሮው ጋር ትስስር ተፈጥሮላቸው አንድ ኪሎ ግራም ኮምፖስት በ4 ብር ዋጋ ሲያቀርቡ መንግስት ደግሞ ዘርፉን ለማበረታታት የ3 ብር ድጎማ በማድረግ በድምሩ በ7 ብር እየሸጡ እንደሚገኙ አብራርተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የአረንጓዴ ቦታዎች አያያዝ፣ ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ አጥናፉ ለዝግጅት ክፍላችን እንደተናገሩት፤ በከተማዋ በቢሮው አማካኝነት የለሙ 730 ሄክታር ስፋት ያላቸው አረንጓዴ ስፍራዎች እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ ለአረንጓዴ ዕፅዋት እድገትና እንክብካቤ ከሚያስፈልጉ ግብአቶች መካከል ኮምፖስት አንዱ ሲሆን በአረንጓዴ ልማትና እንክብካቤ የተሰማሩ 560 የሚሆኑ ማህበራት፣ ኮምፖስት ከሚያመርቱ ማህበራት የገበያ ትስስር ተፈጥሮ ኮምፖስት እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡

ከተማዋ የምታመነጨውን ቆሻሻ ለመልሶ መጠቀም እንዲውል ከማድረግ አኳያ አሁንም ብዙ ስራ እንደሚጠይቅ ያነሱት አቶ ሲሳይ፣ ለአረንጓዴ ስፍራዎች የሚያስፈልገው ኮምፖስት ወይም ማዳበሪያ ፍላጎት ሰፊ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት በመቀየር በስፋት በማምረት ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

እየተመረተ ያለው ኮምፖስት ለአረንጓዴ ልማት እንዲውል ከማድረግ ባሻገር በከተማዋ ዙሪያ ለሚገኙ አርሶ አደሮችም ለማቅረብ እንዲቻል ምቹ የመስሪያ ቦታ በማመቻቸት ረገድ እየተሰራ ነው፡፡ በዘርፉ የሚሰማሩ ማህበራት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። በከተማዋ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ሊበሰብስ የሚችለውን ወደ ኮምፖስት መቀየር ከተቻለ ትልቅ ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ ስራው በቴክኖሎጂ ተደግፎ የሚከናወንበት ሁኔታ ለመፍጠር እንደ ጃፓንና ጋና ከመሳሰሉ ሀገራት ልምድ በመውሰድ እየተሰራ እንደሚገኝ አቶ በላይ ተናግረዋል፡፡

ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሀብት በመቀየር በተለይ የሚበሰብሰውን ቆሻሻ ለኮምፖስት በማዋል ረገድ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ሆኖም በዘርፉ ካለው አቅም አኳያ ብዙ ስራ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ረገድ ከመንግስት ባሻገር የግል ዘርፉንና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማጠናከር ይገባል፡፡

ከአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# አካዳሚው ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ምን እየሰራ ነው?

- በአካዳሚው አማካኝነት ያገኙት ስልጠና የግል ህይወታቸውንም ሆነ ስራቸውን እንዳሻሻለላቸው ሰልጣኞች ተናግረዋል

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

በሀገራችን የአገልግሎት አሰጣጥ ክብደትና ዋጋ በተገልጋዮች እርካታ ልክ ይመዘናል፤ ‘ደንበኛ ንጉስ ነው’ ይሉት የአበው አባባልም ከዚሁ እሳቤ የሚመነጭ ይመስላል። ነገር ግን በዛሬው ዓለም አገልግሎት ጥልቅ ትርጉም እና ግዙፍ ዋጋ ያለው ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ‘ስማርት ሲቲስ አይደንቲቲ’ (Smart Cities Identity) የተሰኘ ገፀ ድር 25 ምርጥ መንግስታዊ ግልጋሎት የሚሰጡ የዓለም ሀገራት በሚል ርዕስ ለንባብ ባበቃው ጽሑፍ፣ ዘመናዊና ቀልጣፋ መንግስታዊ ግልጋሎት የተገልጋይን እርካታ ከማረጋገጥ ያለፈ አንድምታ እንዳለው ያትታል።

ዴንማርክ፣ ኤስቶንያ፣ ሲንጋፖር፣ ፊንላንድ እና ዩናይትድ ኪንግደም መንግስታዊ ግልጋሎቶችን በተሻለ ደረጃ ከሚሰጡ ሀገራት ተርታ ይሰለፋሉ። ሀገራቱ ግልጋሎቶቻቸውን ዲጂታላይዝ ከማድረጋቸውም ባለፈ ተከታታይነት ያለው የአመራርና የባለሙያ ስልጠና መስጠታቸው ለዚህ ውጤት አብቅቷቸዋል፡፡ በዘመናዊ አሰራራቸው ሳቢያ የወረቀትና ተያያዥ ወጪዎችን አስቀርተዋል፤ ምርታማነትን ጨምረዋል፤ የሰራተኞቻቸውን የፈጠራ ችሎታና ክህሎት አሳድገዋል፤ ምቾት እና ውበት ያለው የስራ ከባቢ ፈጥረዋል፤ የተገልጋዮችን ጊዜ ቆጥበዋል፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ህዝባዊ የአስተዳደር ስርዓትን እውን አድርገዋል።

ለመሆኑ በሀገራችን የተቋማትን አመራሮችና ባለሙያዎች አቅም በማሳደግ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝና ህዝቡ የሚደሰትበት ግልጋሎት የሚሰጥ አገልጋይ እንዲፈጠር በምን ልክ እየተሰራ ነው? የሚለው ነጥብ መፈተሽ አለበት፡፡ በእርግጥ የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ በዚህ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ አካዳሚው ለስልጠና፣ ምርምርና ማማከር አገልግሎት የሚውሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም የመንግስትና የግል ተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎችን አቅም መገንባት ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ በተለይም በየስራ ሂደቶች የሚስተዋሉ ክፍተቶችን መሰረት ያደረገ ስልጠና፣ የማማከር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር በማካሄድ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን የማጎልበት ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

አካዳሚው አሁን ባለንበት የዲጂታል ዘመን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካው መስክ ተወዳዳሪ ሆኖ የሚዘልቅ እውቀት፣ ክህሎት እና ባህሪይ ያለው አመራርና ባለሙያ የማፍራት ግብ አለው፡፡ እንዲሁም በመልካም ስነ ምግባር የታነፀ፣ ተነሳሽነት ያለው፣ ከአዳዲስ አሠራሮች ጋር ተዋህዶ ሥራውን መከወን የሚችል፣ የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅሙ የጎለበተ አገልጋይን ለማፍራት እየሰራ እንደሚገኝ ነው የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች የሚናገሩት፡፡



ፎቶ- ከፋይል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራር አካዳሚ የከተማ አመራር ልማት ዘርፍ ምክትል ፕሬዝዳንት ተስፋዬ ኤባ (ዶ/ር)



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ሰልጣኞች በከፊል

በተቋሙ የሰለጠኑ አመራሮችና ባለሙያዎችም ይህንኑ ይመሰክራሉ፤ በአካዳሚው የአመራር ክህሎት ስልጠና ሲወስዱ ያገኘናቸው የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 የንብረት አስተዳደር ግምጃ ቤት ኃላፊ አቶ ብርሃነ ሃጎስ በአገልግሎት አሰጣጥ ፅንሰ ሃሳብ፣ ከህብረተሰቡ ጋር የሚደረገው ተግባቦት ምን መምሰል እንዳለበት እና የባለጉዳይ አያያዝ ጽንሰ ሃሳቦች ምን መምሰል እንዳለባቸው መሰልጠናቸውን ጠቁመው፣ ይህም ስራቸውን በተቀላጠፈ መልኩ ለመከወን እንዳገዛቸው ተናግረዋል፡፡

በቀጨኔ ደብረ ሰላም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሰረታዊ መምህራን ማህበር የስርዓተ ጾታ ተጠሪ የሆኑት መምህርት እመቤት ምትኩ በበኩላቸው፣ በየትምህርት ቤቱ ላሉ የመምህራን ማህበር ተጠሪዎች የተዘጋጀው የአመራር ስልጠና በተለይ ለቦታው አዲስ ለሆኑ አመራሮች ጠቃሚ ነው ብለው፣ አንድ ሰው ለከፍተኛም ሆነ መካከለኛ ኃላፊነት ሲታጭ ለተመደበበት ቦታ ብቁ መሆንና የአመራር ክህሎት መኖር የግድ አንደሆነ ተናግረዋል፡፡ የአካዳሚው ስልጠናም በዚሁ ልክ እንዳበቃቸው ገልፀዋል፡፡

ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ የመምህራን ማህበር አመራሮች የተዘጋጀው ስልጠናም መሪነት ማለት ምን ማለት ነው? በምን መልኩስ ሰዎችን መምራት ይቻላል? የሚለውንና አጠቃላይ ስለ አመራር ክህሎት ጥልቅ እውቀት የሚያስጨብጥና በቀጥታም ከሚሰሩት ስራ ጋር የሚገናኝ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

በልደታ ክፍለ ከተማ መምህራን ማህበር ሂሳብ ሹም የሆኑት ሌላው ሰልጣኝ መምህር አሸናፊ ምንዳዬ በበኩላቸው፣ በስልጠናው ለስራቸው የሚያግዝ እውቀት ማግኘታቸውን ጠቅሰው፣ መሪነት ምን እንደሆነ፣ የአመራር ብቃት እና ስለግንኙነት ምንነት እንዲሁም መሪ ሲኮን ከተማሪዎች እና ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዴት መነጋገርና መግባባት እንደሚቻል እንዲሁም ከስር ያሉትን በምን መልኩ ማብቃት እንዳለባቸው መገንዘባቸውን ገልፀዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራር አካዳሚ የከተማ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይዘሮ ነፃነት የምሩ፣ አካዳሚው የከተማ አስተዳደሩ በሰጠው ተልዕኮ መሰረት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና በመስጠት የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ማጎልበት ላይ አተኩሮ እየሰራ እንደሆነ ተናግረዋል።

ለመምህራን ማህበር አመራሮች ‘የአመራር ክህሎት’ በሚል ርዕስ የተሰጠው ስልጠናም የዚሁ አካል መሆኑን ጠቅሰው፣ በስልጠናው ከመላው አዲስ አበባ ለተወጣጡ 300 አመራሮች በሁለት ዙር መሳተፋቸውን ገልፀዋል፡፡ ስልጠናው የመምህራንን አቅም በማጎልበት የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮ እንዲወጡ በማድረግ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው አስረድተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራር አካዳሚ የከተማ አመራር ልማት ዘርፍ ምክትል ፕሬዝዳንት ተስፋዬ ኤባ (ዶ/ር) አካዳሚው በዋናነት በሦስት ዘርፎች ላይ አተኩሮ እንደሚሰራ ይገልፃሉ፤ እነዚህም ስልጠና፣ የምርምርና የማማከር አገልግሎት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም የሰው ሀብት ብቃት ማረጋገጥ ናቸው፡፡ አካዳሚው ሲቋቋም ከተሰጡት ተልዕኮዎች አንዱ በከተማ ደረጃ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ማጎልበት ነው፡፡ አቅም የሚያጎለብተውም በምርምር፣ በማማከርና በማሰልጠን ነው፡፡

እንደ ተስፋዬ (ዶ/ር) ገለፃ፣ ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ በተቋሙ ሪፎርም ተደርጎ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ለማጎልበት በተለይ ስልጠና ዘርፍ በሁለት ዳይሬክቶሬቶች እንዲመራ ተደርጓል። ቀደም ሲል በአንድ ዳይሬክቶሬት የነበረው የመፈፀምና የማስፈፀም ግቡን ለማሳካት የስራ አመራር ስልጠና ዳይሬክቶሬትና የከተማ አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት በሚል በሁለት እንዲመራ መደረጉም ስራዎችን በተናጠልና ተቀናጅቶ ለማከናወን አስችሎታል፡፡

በእርግጥ ዳይሬክቶሬቶች የተለያየ የስራ ድርሻ ያላቸው ሲሆን፣ የስራ አመራር ስልጠና ዳይሬክቶሬት በከተማ ደረጃ ያሉ ባለሙያዎችን፣ ቡድን መሪዎችንና ዳይሬክቶሬቶችን በስልጠና የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡

የከተማ አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት ደግሞ ተሿሚ እና ተተኪ አመራሮችን ማብቃትና ተተኪ አመራሮች የመገንባት ተልዕኮዎች አሉት፡፡ የአካዳሚው ተልዕኮ በመንግስት ተቋማት ብቻ የተገደበ ሳይሆን የግል ተቋማትንም የሚመለከት በመሆኑ ከተለያዩ ሲቪል ማህበራት፣ አደረጃጀቶችና በግሉ ዘርፍ ላሉትም ስልጠና ይሰጣል፡፡

ስልጠናዎች በሁለት መንገድ የሚሰጡ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ተቋማት ክፍተታቸውን ለይተው ይህ ስልጠና ይሰጠን ብለው በራሳቸው ጥያቄ በቀረበው መሰረት የሚከወን ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ አካዳሚው በራሱ እቅድ በከተማ ደረጃ የክፍተት ዳሰሳ ጥናት ሰርቶ በዳሰሳ ጥናቱ ምልከታ መሰረት አቅዶ የሚሰጠው ስልጠና ነው፡፡ በዚህ መሰረት በ2017 በጀት ዓመት በሁለቱም ዳይሬክቶሬቶች የእቅዱን መቶ በመቶ ተግባራት ማሳካት መቻሉን ተናግረዋል፡፡

የከተማ አመራር ልማት ስልጠና ከእቅድ በላይ 105 በመቶ ማሳካት መቻሉን ያስታወሱት ተስፋዬ (ዶ/ር)፣ በ2017 በጀት ዓመት በየደረጃው ለሚገኙ 5 ሺህ ተሿሚ አመራሮች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ5 ሺህ 300 በባህሪ ቀረፃ፣ የትግበራ ክህሎት እና ሌሎች የስልጠና ርዕሶች ማሰልጠን ተችሏል ብለዋል፡፡

በስራ አመራር ስልጠና ዳይሬክቶሬትም በ2017 በጀት ዓመት በየደረጃው የሚገኙ 5 ሺህ 834 ዳይሬክተሮች እና ቡድን መሪዎችን ለማሰልጠን ታቅዶ 4 ሺህ 975 ዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች እንዲሁም ለ2 ሺህ 708 ባለሙያዎች ለማሰልጠን ታቅዶ ለ2 ሺህ 693 በማሰልጠን የእቅዱን 99 ነጥብ 4 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ እስከ ግንቦት ወር መጨረሻ ድረስ 7 ሺህ 668 ዳይሬክተሮች፣ ቡድን መሪ እና ባለሙያዎችን ማሰልጠን ተችሏል፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በመንግስትም ሆነ በግል ደረጃ ያለው አገልግሎት አሰጣጥ የዘመነ አይደለም ያሉት ተስፋዬ (ዶ/ር)፣ በአንዳንድ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ያለው አገልግሎት አሰጣጥ ብልሽት የሚስተዋልበት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ተገልጋይን የማመናጨቅ፣ በአግባቡ ያለማስረዳትና ያለማስተናገድ ብሎም ማጉላላትን የመሳሰሉ የፈፃሚ ባህሪ ጉድለቶች በስፋት ይታያሉ ያሉት ተስፋዬ (ዶ/ር)፣ እንደዚህ አይነት ጉድለቶችን ለማረም የአቅምና የባህሪ መገንባት ስራ መከናወን አለባቸው ከሚል አንፃር ስልጠናዎች አንደሚሰጡ አብራርተዋል፡፡

በተለይ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ሁሉም አገልጋይ በተሰማራበት ዘርፍ ትዕግስትና ቅንነትን ከመላበስ ባሻገር፣ “እኔ የህዝብ አገልጋይ ነኝ” የሚል ስሜት ይዘው ህዝብን ማገልገል ይኖርባቸዋልም ብለዋል፡፡ በአካዳሚው ደረጃም የስልጠናውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ከስልጠና በኋላ በተለያየ መልኩ ግብረ መልስ የሚሰበሰብበትና ጥናት የሚደረግበት አግባብ ሂደቱን እያጠናከሩ ለመሄድ ያስችላል ሲሉም አክለዋል፡፡

የ2017 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም በስራ ክፍሉ በተሰጡ ስልጠናዎች ተገልጋዮች የእርካታ ደረጃ የተሻለ መሆኑ፣ የስልጠና ተደራሽነትን ለማስፋት ከአካዳሚው የማሰልጠኛ ክፍሎች በተጨማሪ በየክፍለ ከተማውና በወረዳዎች የሚገኙትን የወጣት ማዕከላት እና ሌሎች ተቋማትን የስልጠና ፋሲሊቲ መጠቀማችን ረድቶናል ብለዋል፡፡

የሚሰጡ ስልጠናዎች በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ በመደረጉ እና በከተማ አስተዳደሩ የተቋማት ስልጠና ፍላጎት ተሰብስቦ የስልጠና ፍኖተ ካርታ በመዘጋጀቱ ለስልጠናው ስራ መሳካት ጉልህ ድርሻ ማበርከቱን የገለፁት ተስፋዬ (ዶ/ር)፣ ለአመራሮች እና ለባለሙያዎች በተለያዩ ርዕሶች ላይ ከእቅድም በላይ ስልጠና ለመስጠቱ የተቻለበት አካሄድ የመነጨው በዚሁ የተቀናጀና የተጠናከረ ቅድመ ዝግጅት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የአቶ በሪሁን ወንድይፍራው ፋንታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የካርታው ቁጥር AA0000610072881290006 የሆነው ሰርተፍኬት በፅህፈት ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው በቤት ባለቤትነት ካርታ በሴሪ ቁጥር 0348282 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቸዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት እነ መ/አ/አሣዬ መንበሩ ረታ የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ቀበሌ --- ወይም በቀድሞው ወረዳ --- ቀበሌ 18 የቤት ቁጥር 757 የካርታ ቁጥር 42/961/00/680 ሴሪ ቁጥር 009222 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ማክሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ካርታ ቁጥር ቦሌ የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ AA00006080790201 ሴሪ 010242 ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በመርከብ የማነ ገብረመስቀል ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር 111 የመሬት ይዞታ ካርታ ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000040402587 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን /ዘጠና ቀን/ ድረስ ጽ/ቤታችን ቀርበው እንዲያሳውቁ ካልቀረቡ ግን በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቂርቆስ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት እንስተ መመኪያ እና ገብረአምላክ የሺጥላ የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ቀበሌ ወይም በቀድሞው ወረዳ --- የቤት ቁጥር የካርታ ቁጥር የካ/86/176733/05/93/13/1 ሴሪ ቁጥር 0242872 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር MK-B35-03-1387 ወ/ሮ ሀና ጌታቸው ጎሹ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር (ካርታ ቁጥር) AA00009130000935031387 ሴሪ ቁጥር 177847 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 25/02/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ(አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እነ ኤርሚያስ ተሰማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የሚገኘው የይዞታ ካርታ ቁጥር AA000061007291320321 የሆነው ሰርተፊኬት ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት ባለቤትነት ካርታ ሴሪ ቁጥር C. 0321640 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቸዋለሁ የሚል ግለሰብ ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካላቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት/ካርታ ተዘጋጅቶ እንደምንሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ዴቢ ወልደልዑል ሀሽም በቀን 17/03/2018 ዓ/ም ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት በቀድሞው ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ከአያት ኃ/የተ/የግ ማህበር የገዙ ሲሆን በአሁኑ በለሚ ኩራ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/23/6/5/2756/54537/01 ዴቢ ወልደልዑል ሀሽም እና ለማ ደስታ በልሁ የተመዘገበ ሲሆን የመኖሪያ ቤት ካርታ ስለጠፋብኝ ለፖሊስ ጣቢያ እና ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንዲፃፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም ማህደራቸው ወጦልን በማንዋል ባጣራነው መሰረት በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 10 ዴቢ ወልደልዑል ሀሽም እና ለማ ደስታ በልሁ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/23/6/5/2756/54537/01 ሴሪ ቁጥር 102053 የሆነ ይዞታ ቤት ስፋት 300 ካ.ሜ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ ማረጋገጫ ካርታቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱ በዕዳ አስዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት ጥሪ የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ማህደሩን የማናደራጅ እና ኃላፊነቱን የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 13 በእልፍነሽ ሁሉቃ ስም የተመዘገበ የይዞታው ካርታ ቁጥሩ የካ13/15194/08 የተሰጠበት ቀን 02/01/08 ዓ.ም እና ሴሪ ቁጥር 105733 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/18/7032/18 በቀን 29/03/2018 ዓ.ም የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች በምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በውብቴ አየለ አለምነህ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090102938 ሴሪ ቁጥር R 0123800 የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 29/03/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን እያልን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ የሚገኘው የቦሌ ገርጂ ደብረ ገነት ቅ/ጊዮርጊስና ቅ/ገብርኤል ካቴድራል ለዘላቂ ማረፊያ የሚጠቀምበት መካነ መቃብር 7 ዓመት የሞላቸውን አጽሞች በማንሳትና የከተማዋን ውበት በጠበቀ መልኩ ለቀብር ቦታውን ለማዘጋጀት ጥናቱን ጨርሷል፡፡

ስለሆነ በዚሁ የገርጂ ደብረ ገነት ቅ/ጊዮርጊስና ቅ/ገብርኤል ካቴድራል መካነ መቃብር የወገኖቻችሁን አጽም ያሳረፋችሁ በሙሉ ይህ ማስታወቂያ ከተነገረበት ዕለት አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አጽሞቹን እንድታነሱና በተዘጋጀው ቦታ እንድታሳርፉ እየገለጽን በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልተነሳ ግን የሰበካ ጉባዔው በራሱ ወጪ አጽሞቹን የሚያስነሳ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የቦሌ ደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ጉብርኤል ካቴድራል ሰ/ጉ/ጽ/ቤት**

---

## የባለቅኔው... ከገጽ 11 የዞረ

ምን ምላሽ መስጠት እንዳለበት ትንሹ ጸጋዬ ግራ ገባው፡፡ አጠገቡ ለነበረውና ለሚወደው የጂኦግራፊ መምህሩ “ምን ልበል?” ሲል ጠየቀው፡፡

መምህሩም አሰብ አደረገና “ለትምህርት ቤቱ ትንሽ በጀት እንዲለቀቅ...” ጠይቅ አለው

እንደተባለው ለአንጋቹ ነገረው፡፡ አንጋቹም ሄዶ ለጃንሆይ ነገራቸው፡፡

ጃንሆይም “ለራሱ ለልጁ ተጨማሪ ነገር ምን እንድናደርገለት ይፈልጋል? ሂድና ጠይቀው” አሉት፡፡

አንጋቹ ተመልሶ ጸጋዬን ጠየቀው፡፡

አሁንም ትንሹ ጸጋዬ ግራ በመጋባት ስሜት ጂኦግራፊ መምህሩን ተመለከተው፡፡“ለእያንዳንዱ ተማሪ የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) እንዲሰፋላቸው ልትጠይቅ ትችላለህ” አለው፡፡

ጸጋዬ መምህሩ እንዳሉት መልሶ ለአንጋቹ ነገረው፡፡

አንጋቹም ሄዶ ለጃንሆይ ነገራቸው፡፡

“ፈቅደናል!” በማለት ጃንሆይ መለሱ፡፡

አዳራሹ በጭብጨባ ተናጋ፡፡ ጸጋዬም በኢትዮጵያ የቴአትር መድረክ ለመንገስ የሚያስችለውን የመጀመሪያ ጉዞ አንድ ብሎ መጀመሩን ያስመሰከረበት አጋጣሚ ሆነ፡፡ ጸጋዬም በንጉሰ ነገስቱና በባለስልጣኖቻቸው የተጨበጨበለት፣ የአምቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያኮራ እና ያሸለመ በማለት ዝናው በከተማው ናኘ፡፡ ይሄ ነው የጸጋዬ ጉዞ! ይሄ ነው የጸጋዬ ተሰጥዖ! ይሄ ነው የጸጋዬ ዳና! በዚህ መንገድ አልፎ ነው፤ የኋላ ኋላ አፍሪካዊ ባለቅኔነቱንና ጸሐፌ ተውኔትነቱን ያስመሰከረው፡፡ ‘ዛሬም ድረስ እሱን የሚተካከል ሌላ ጸሃፌ ተውኔትና ገጣሚ የለም!’ እስከሚባል ድረስ በታወቁ ከያኒያን የተጨበጨበለት ጸጋዬ የህይወት ዳራ መነሻው ይሄ ነው፡፡

### ጸጋዬን በልጆቹ አንደበት

ጸጋዬ ከልጆቹ ጋር ጥብቅ ትስስር እንደነበረው መጽሐፉን ያነበበ ሰው የማይስተው እውነታ ነው፡፡ ጸጋዬ የሶስት ሴቶች አባት ነው፡፡ በጣም የሚወዳት ሚስቱ ላቀች ከቀድሞ ባሏ የወለደቻቸው ሁለት ወንድ ልጆች፣ እንደ ራሱ አብራክ ክፋይ አድርጎ እንደ አባት ሆኖ አሳድጓል። ወጣቱ ጸጋዬ ሚስቱ ወይዘሮ ላቀች አግብታ የፈታች፤ የሁለት ልጆች እናት መሆኗን ከመጤፍ ሳይቆጥር በሙሽራ ደንብ አግብቷት እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ድረስ በፍቅር አብሯት ኖሯል፡፡ መጽሐፉ ውስጥ እንደሰፈረው ጸጋዬ ለፈጠራ ሥራዎቹ መቃናትና በተመስጦ እንዲሰራ ካስቻሉት ነገሮች አንዱ የሚስቱ ሚና ትልቅ ድርሻ ይወስዳል፡፡

እንደ ባለቅኔ ሳይሆን እንደ አባት ጸጋዬን በልጆቹ አንደበት ልጁ ዮዲት ጸጋዬ እንዲህ ስትል ስለ አባቷ መጽሐፉ ውስጥ አስፍራለች፤ “አባታችን እንደ ጓደኛ የቆርኪ ቡናችንን እየጠጣ፤ ስንዘል እንደ አጫዋችም እንደ ተጫዋችም ሆኖ በኪሱ የያዛቸው ሳንቲሞች እስኪዘረገፉ አብሮን ይዘል ነበር፡፡ ከፍ ካልንም በኋላ ፓርቲ ለመውጣት (ከጓደኞቻችን ጋር ለመዝናናት) ከእናታችን ቁም ሳጥን ያለ ፈቃድ ልብስ ስንወስድ ከእኛ ጋር ተባብሮ ምስጢራችንን ይደብቅልናል፡፡

“በየዓመቱ በትንሳዔ በዓል ሌሊት ከተኛበት ውሃ አርከፍክፎ ከእንቅልፋችን ቀስቅሶን እንደ ልጅ መደሰቱ ሌላ የልጅነት ትውስታችን ነው፡፡ አንዳንዴ የለመደውን ለማድረግ ከመኝታ ቤታችን ሲገባ ነቅተን ካገኘን ተንኮሉ ባለመሳካቱ ይቆጭና የያዘውን ውሃ ቸልሶብን ከእኛ ጋር አብሮ ይስቃል” በማለት ዮዲት (በገጽ፣2) ከአባታቸው ጋር የነበራቸው መስተጋብር አስፍራለች፡፡

# ባህላዊ ስፖርቶችን ወደ ዓለም አቀፉ መድረክ ለመውሰድ ምን ይሰራ?







ፎቶ- ከገፀ ድር

በኢትዮጵያ ከ294 በላይ ባህላዊ ስፖርቶች ያሉ ቢሆንም፣ ከዘመናዊ ስፖርቶች ጋር ሲነፃፀር ተገቢውን ትኩረት አላገኙም

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የዓለም ቴኳንዶ ፌዴሬሽን መረጃ እንደሚያሳየው በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ወደ 10 የሚደርሱ የቴኳንዶ ስፖርት ዓለም አቀፍ ውድድሮች ይካሄዳሉ፡፡ በእነዚህ ውድድሮች ላይ ታዲያ ባህላዊ ስፖርቱ ተጸንሶ ከተወለደበት ጃፓን በተጨማሪ በርካታ ሀገራት የአሸናፊነት ሜዳልያ የሚያጠልቁበት ጭምር ነው፡፡ ከእነዚህ ሀገራት መካከል እንደ ኢራን፣ ሳኡዲ አረቢያ፣ ፈረንሳይ፣ ብራዚል፣ ጀርመን፣ ቱርክዬና አዘርባጃን ያሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ከአህጉረ አፍሪካም እንደ ግብጽ፣ ሞሮኮ እና አልጄሪያ የመሳሰሉ ሀገራት በስፖርቱ ውጤታማ ናቸው፡፡

በጃፓናውያኑ ተጠንስሶ ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘው የቴኳንዶ ስፖርት በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደዚህ አይነት እውቅና ከማግኘቱ አስቀድሞ ግን ዓመታትን የፈጀ በርካታ ሂደቶችን ማለፍ ነበረበት፡፡ በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር በ1922 በጃፓን ትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው ስልጠና በየትምህርት ቤቱ እንዲሰጥ ተደርጓል። ውድድሮች እንዲካሄዱ ደንቦችን በማዘጋጀት እ.ኤ.አ በ1957 በቶኪዮ የመጀመሪያውን የጃፓን ዩኒቨርሲቲ የካራቴ ውድድር አካሂደዋል። በ1964 እንደዚሁ የጃፓን ካራቴ ፌዴሬሽን መመስረቱን ተከትሎ በ1970 የዓለም ካራቴ ፌዴሬሽን ተቋቁሟል። እንዲ እንዲህ እያለ እ.ኤ.አ በ2016 ስፖርቱ በ2020 የቶኪዮ ኦሎምፒክ ጨዋታዎች ውስጥ በሁለቱም ጾታ እንዲካተት ተመርጧል።

ልክ እንደጃፓን ሁሉ የተለያዩ ሀገራት የራሳቸው የሆኑና ባህላቸውን፣ እሴቶቻቸውንና ማንነታቸውን የሚገልጡባቸው ባህላዊ ስፖርቶች አሏቸው፡፡ የበርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ የሆነችው ኢትዮጵያም ከታሪክና ከባህል ጋር የተቆራኙ ልዩ ልዩ ስፖርታዊ ክንውኖች አሏት። እነዚህ ስፖርቶች እንደ የፈረስ ጉግስ፣ የጦር ውርወራ፣ የገና ጨዋታ፣ ገበጣ እና ትግልን የመሳሰሉት የማንነት፣ ወግና ልማድ መገለጫዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ የሚዘወተሩ ባህላዊ ጨዋታዎች በትክክል መቼ እንደተጀመሩ በጽሑፍ የተደገፈ መረጃ ባይገኝም ከክርስቶስ ልደት በፊት ይዘወተር እንደነበር በአፈ ታሪክ ይነገራል፡፡ በዚህም የክርስቶስ ልደት (የገና በዓልን) ምክንያት በማድረግ ከታህሣሥ ጀምሮ እስከ ጥር እና ከዚያም እስከ ክረምቱ መግቢያ ድረስ በብዛት ይጫወቱት እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያመላክታሉ፡፡

እነዚህ ባህላዊ ስፖርቶች ታዲያ ከስፖርታዊ ውድድርነት ባለፈ ትርጉማቸው ከፍ ያለና የታሪክና የባህል ማስረጃዎችም ጭምር ናቸው፡፡ የማኅበራዊ ትስስር ማዕከሎች ሆነውም ያገለግላሉ፤ እነዚህ ጨዋታዎች ሕዝብ ከሕዝብ የሚገናኝባቸው፣ ልምድ የሚለዋወጥባቸው እና የአንድነት ስሜት የሚጎለብትባቸው መድረኮች ናቸው፡፡

ይሁንና፣ እነዚህን ሀገራዊ ሀብቶች በዘመናዊ መንገድ አልምቶ፣ በሕግ ማዕቀፍ አስደግፎ እና ለዓለም አስተዋውቆ ለኢኮኖሚና ለዲፕሎማሲያዊ ጥቅም ለማዋል እየተሰሩ ያሉት ሥራዎችና የሚፈለገው ደረጃ ምን ይመስላል? የሚለው ጉዳይ ደግሞ ወሳኝ ይሆናል። ባለሙያዎች እንደሚገልጹት፣ በኢትዮጵያ ከ294 በላይ ባህላዊ ስፖርቶች ያሉ ቢሆንም፣ ከዘመናዊ ስፖርቶች ጋር ሲነፃፀር ተገቢውን ትኩረት አላገኙም ማለት ይቻላል።

በ1977 ዓ.ም የተመሰረተው የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን የኢትዮጵያዊያን ልዩ መለያ የሆኑ ባህላዊ ስፖርቶች እና ጨዋታዎች በጥናት እና ምርመር በመታገዝ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይዘታቸውን ጠብቀው እንዲተላለፉ የማልማት፣ የማሳደግ፣ የመጠበቅ እና የማስተዋወቅ ስራዎችን በስፋት እየሠራ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ባህላዊ ስፖርቶች ፌዴሬሽን በጥናት አረጋግጨዋለሁ ባለው መረጃ መሰረት በመላው ኢትዮጵያ ከ200 በላይ ባህላዊ የስፖርት ጨዋታዎች አሉ፡፡ እነዚህ ባህላዊ ጨዋታዎች ታዲያ የተለያዩ አካባቢዎችና የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማንነት የሚንጸባረቅባቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ ባህላዊ ስፖርቶች መካከል ደግሞ ህግና ደንብ ወጥቶላቸው በውድድር መልኩ እየተካሄዱ ያሉት አስራ አንዱ ብቻ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ዋነኛ ስራው ባህላዊ ስፖርቶችን ማስተዋወቅ፣ ማሳደግና ማበልጸግ ሲሆን፣ በተለያዩ አካባቢዎች የሚዘወተሩ ባህላዊ ስፖርቶችን ወደ አንድ መድረክ እያመጣ በውድድር መንፈስ እንዲዘወተሩ ማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን ባህላዊ ስፖርቶች ከሀገር ውስጥ አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲተዋወቁ ብዙ መሰራት ያለበት ነገር አለ ይላሉ የባህላዊ ስፖርቶች ባለሙያው አቶ ይገረም ባየልኝ፡፡

በኢትዮጵያ ባህላዊ ስፖርቶች ፌዴሬሽን መረጃ መሰረት በየዓመቱ በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ ዓመታዊ የባህል ስፖርት ውድድሮች እየተካሄዱ ሲሆን፣ የባህል ስፖርቶች ይበልጥ እንዲዘወተሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች፣ እንዲሁም የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ሥልጠናዎች በፌዴሬሽኑ እየተሰጡ ነው። በየዓመቱ የሚደረጉት ውድድሮች ባህልና ወጉን ከማሳደጉም ባሻገር ለስፖርቶቹ ተተኪ ትውልድ ለማፍራት ዓላማ ይዘው የሚከወኑ ናቸው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ የባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን መረጃ ከሆነም ውድድሩ ወጥነት እንዲኖረውና ዘመናዊነቱን እንዲጠብቅ የተሰራው ትልቁ ነገር ወጥ በሆነ ህግ እንዲመራ መደረጉ ነው፡፡ የባህል ስፖርት ውድድሮች የነጥብ አያያዝ ወጥነት እንዲኖረውና ለዳኝነት እንዲመች ዳኞችን በማሰልጠን ህጎቹ እንዲታወቁ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በየዓመቱ በፌስቲቫል መልክ በሚደረጉ ውድድሮች እስከ አንድ ሺህ የሚደርሱ ተወዳዳሪዎች ይሳተፋሉ፡፡

በውድድር መልክ ካልሆነ ባህላዊ ስፖርቶችን ለማሳደግ አዳጋች ነው የሚሉት ባለሙያው አቶ ይገረም ባህላዊ ስፖርቶቹን ለማሳደግና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ በፌስቲቫል መልክ ብቻ ሳይሆን ወጥነት ባለው መልኩ ዓመታዊ ውድድሮች መሰናዳት እንደሚኖርባቸው ይገልጻሉ፡፡

የዜጎችን የባህል ስፖርት ተሳትፎ ለማሳደግ እና ስፖርቱን ለማስፋፋት እንዲረዳ ታስቦ በ1990 ዓ.ም የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ የወጣ ቢሆንም የሚጠበቅበትን ውጤት ማምጣት አልቻለም የሚለው ደግሞ የብዙዎች አስተያየት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ህይወት መሐመድ የባህል ስፖርቶችን በአፍሪካ ደረጃ ለማስተዋወቅ የአፍሪካ የባህል ስፖርቶች ኮንፌዴሬሽን ጋር ጠንካራ ግንኙነት ተፈጥሯል ያሉ ሲሆን፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በአዳጊዎች እና በትምህርት ቤቶች ስፖርታዊ ውድድር ላይ የባህል ስፖርት እንዱ የውድድር አካል ሆኖ እየተካሄደ ነው ብለዋል።

ይህም ለባህል ስፖርቶች ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ ዩኒቨርስቲዎች የባህል ስፖርቶችን ለማሳደግ በጥናት፣ በምርምር እና በትምህርት እንዲሁም በስልጠና ትልቅ ሥራ እየሠሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በቀጣይ የባህል ስፖርቶችን ለማሳድግ እና ለማስተዋወቅ የክልልና ከተማ አስተዳደር የባህል ስፖርት ፌዴሬሽኖችን ማጠናከር፤ የባህል ስፖርቶች ውድድርና ፌስቲቫል ፕሮግራሞችን በማብዛት በስኬት ማጠናቀቅ፤ የ2026 የመጀመሪያውን የአፍሪካ ሀገራት የባህል ስፖርቶች ፌስቲቫል በሀገራት ለማዘጋጀት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን መስራት እንደሚገባ ያነሳሉ፡፡

እንደዚሁም የአርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ውድድር ማዘጋጀት፤ ለሁሉም ክፍት የሆነ የባህል ስፖርቶች ውድድር ማዘጋጀት፤ የውድድር ማቴሪያሎችን ስታንዳርድ ማዘጋጀት፤ ዘርፉን ለማዘመን እና ለማሳደግ ከፍተኛ የሆኑ የጥናት እና ምርምር ስራዎችን መስራት እና ሌሎችም ስራዎች ተጠቃሽ ሲሆኑ፣ ለዚህም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር እና በተቻለ ፍጥነት ወደስራ በመግባት አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

ወይዘሮ ሕይወት የባህል ስፖርቶች የማኅበረሰብ የፍልስፍና ውጤቶች ናቸው ያሉ ሲሆን፣ እንዲለሙ፣ እንዲተዋወቁ እና የቱሪዝም ግብዓት እንዲሆኑ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በካሪኩለም ተካትተው በትምህርት እንዲሰጡ ከፍተኛ ስራዎች እየተሠሩ ይገኛል ብለዋል። በተለይም ተተኪ ስፖርተኞችንና ባለሙያዎችን ማፍራት ከተቻለ ስፖርቱ ከውድድሩ ባለፈ የሀገሪቷን ባህል የሚያስተዋውቅና ለቱሪዝም እድገቱ አስተዋጽኦ የሚያበርክት በመሆኑ ትኩረት እንደሚያሻው እሙን ነው።

ባለሙያዎች እንደሚገልጹት ባህላዊ ስፖርቶችን ወደ ዓለም መድረክ ለማውጣት እና ከጥፋት ለመታደግ የሕግ ማዕቀፍና ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት ወሳኝ ናቸው። የባህል ስፖርቶች በብሔራዊ ሀብትነት እንዲታወቁና እንዲሁም ቅርጻቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉ በሕግ መደገፍ አለባቸው። ለፈረስ ጉግስና ለጦር ውርወራ በዓለም አቀፍ ደረጃ ውድድሮችን ለማካሄድ እንዲቻል የቴክኒክ ሕጎች፣ የዳኝነት መስፈርቶችና የደህንነት ደረጃዎች በሕግ ማዕቀፍ ተቀርፀው መደራጀት አለባቸው። እንደዚሁም የስፖርቱን ልማት በዘላቂነት ለመደገፍ በጀት እንዲመደብና የፋይናንስ ምንጭ እንዲፈጠር ሕጋዊ መሠረት መጣል ያስፈልጋል።

ባህላዊ ስፖርቶቹ 'የስፖርት ቱሪዝም' (Sport Tourism) ተደርጎ ሊታይና በተመረጡ ታሪካዊ ቦታዎች በዓመታዊ ትዕይንትነት ሊቀርብ ይችላል። በሌላም በኩል ዓለም አቀፍ የስፖርት ሕጎች በማካተት ለምሳሌ የጦር ውርወራ (Javelin Throw) ዘመናዊ ቅርፅ እንዳለው ሁሉ የኢትዮጵያ ባህላዊ የጦር ውርወራም በልዩ የሕግ ማዕቀፍ ለአፍሪካና ለዓለም አቀፍ ውድድሮች ሊቀርብ የሚችልበት ዕድል ዝግ አይደለም።

የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ማስፈጸም፣ የባህል ስፖርቶችን በብሔራዊ ሀብትነት የሚጠብቅ፣ የሚያለማና የማስተዋወቂያ ሥርዓት የሚያስቀምጥ ሕግ በአስቸኳይ ማውጣት እና የቱሪዝም ሚኒስቴርን፣ የባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽንን እና የኢንቨስትመንት ተቋማትን በማቀናጀት ባህላዊ ስፖርቶችን ከቱሪዝም ፓኬጆች ጋር ማስተሳሰር እንደሚገባም ባለሙያው አቶ ይገረም ያስረዳሉ። አክለውም ስፖርቶቹን በዘመናዊ መንገድ መመዝገብ፣ ዲጂታል ማኅደሮች ማዘጋጀት እና በማኅበራዊ ሚዲያዎች በዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ማስተዋወቅ ይገባል ይላሉ።

የባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን አደረጃጀት በባለሙያ እንዲደግፍ ማድረግና ባለሀብቶች በፈረስ ጉግስና መሰል ስፖርቶች ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ማበረታቻ መስጠትም ሌላኛው መፍትሔ ስለመሆኑ ባለሙያው ተናግረዋል፡፡ ባህላዊ ስፖርት ከስሜት ተሻግሮ በሳይንሳዊ መንገድና በሕግ ማዕቀፍ ተደግፎ ከተሰራበት እንደ ጃፓን 'ሱሞ' ወይም እንደ ስፔን 'ሮዲዮ' የዓለምን ትኩረት መሳብ ብቻ ሳይሆን፣ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥቅሞች ማግኘት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ለአህጉር አቀፉ የአፍሪካ የባህል ስፖርቶች እና ጨዋታዎች ኮንፌዴሬሽን (African traditional sports and games confederation) ያቀረበው የአባልነት ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱ ይታወሳል።